## የቴዲ አፍሮ

# የታላቅነት ምስጢር

በአቤል ዘበነ

2002 ዓ.ም

አዲስ አበባ

© የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

ALL RIGHTS RESERVED

የመጀመሪያ እትም - ህዳር 2002ዓ.ም

ለአስተያየትዎ - ፖ.ሣ ቁ. 2504 ኮድ 1250



ፍቅር እራስን አሳልፎ ከመስጠት ይጀምራል።

ስለሆነም ለሚወዱት ሰው የሚወዱትን ነገር ያበርክቱ!

ከ ........................................................

ለ ........................................................

# ምስጋና

በቅድሚያ የማይቻለውን አስችሎ ለዚህ ላደረሰኝ ለኃያሉ እግዚአብሔር ምስጋናዬ ከምንም በላይ የላቀ ነው። አንዳችም ተራ ነገር ብትሆን በእኔ ኃይል፣ ጉልበትና ችሎታ ዕውን አልሆነችም። አርቲስት አዳነች ወ/ገብርኤል ይህንን መጽሀፍ ለመጻፍ ውጥን እንዳለኝ ሀሳቤን ያካፈልኳት ጊዜ አይዞህ፣ በርታ በማለት ከሞራል ድጋፍ አንስቶ አንዳንድ መረጃ የማገኝባቸውን መንገዶች እስከ ማመቻቸት ድረስ ላደረገችልኝ ከባድ ውለታ ምስጋናዬን የምገልጽበት ቃል የለኝም። በህይወት ዘመንሽ ያለብሽውን ሁሉ ፈጣሪ ከጎንሽ ሆኖ እንዲያሳካልሽ እመኝልሻለሁ።

እንዲሁም ከጎኔ ሆነው በሀሳብና በፀሎት ላገዙኝ ለቴዲ አፍሮ አድናቂዎች በሙሉና ለጓደኞቼም ጭምር በፈጣሪ ስም ከፍ ያለ ምስጋና ይድረሳቸው።

በተጨማሪም ለ33 ዓመታት አሜሪካ ሀገር የሚገኙት የህክምና ባለሙያ ፕሮፌሰር መስፍን ለማ፣ በአጋጣሚ ለእረፍት ወደ ትውልድ ሀገራቸው ኢትዮጵያ መጥተው ሳለ የእረፍት ጊዜያቸውን ሰውተው የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ ጽሑፍ በማንበብና በመጽሐፉ ጀርባ ሽፋን ላይ የለፈረውን ቀና አስተያየት በመስጠት ስለተባበሩኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

ሁሉ በእርሱ ሆነ!

አቤል ዘበነ



------------------------------ የቴዲ አፍሮ የታላቅነት ምስጢር ------------------------------

# ማውጫ

**ክፍል አንድ**
**የቴዲ አፍሮ የልጅነት ሕይወትና**
**ለሙዚቃ የከፈለው ታላቅ መስዋዕትነት------------------------------ 9**
1 ቴዲ አፍሮ ከየት ወዴት?
ቴዎድሮስ ካሳሁን ለምን ቴዲ አፍሮ ተባለ?
2 ለቴዲ አፍሮ ስኬት ከፍተኛውን ሚና የተጫወተው
የአባቱ የሥነ-ልቡና ጨዋታ
3 ቴዲና የትምህርት ቤት ቆይታው

**ክፍል ሁለት**
**ቴዲ አፍሮን ለታላቅነት ያበቁት ዓበይት ምክንያቶች------------------------------ 33**

4 ቴዲ፣ ሥር ነቀል ለውጥ ያመጣ አብዮተኛ
5 ቴዲ ለህገሩ ያለው ስሜት
6 ቴዲና ነፃነት
7 የሰላም እርግብ
8 ቴዲ አፍሮ ከባህሪይ አንፃር ሲታይ
9 ቴዲ አፍሮ ማንን ይፈራል?
10 ታላቅ ሰው ታላላቅ ተግባር የሰሩትን ያከብራል
11 የቴዲ አፍሮ የደግነት መለኪያዎች
12 ቴዲና ኮንሰርቶቹ

**ክፍል ሦስት**
**ቴዲ ከማንም አርቲስት ልቀ የክብር አክሊል**
**እንዲደፋ ያደረጉ ታላላቅ እውነታዎች------------------------------ 81**

13 ሙዚቃ ያኔና ዘንድሮ
14 ከዝነኝነት ወደ ተምሳሌትነት የተመነጠቀ
ኢትዮጵያዊው የሙዚቃ ንጉሥ!

**ክፍል አራት**
**ቴዲ አፍሮ በሌሎች ዓይን**------------------------------------------------------------ 97

15 ቴዲ አፍሮና ሚዲያ
16 ቴዲ አፍሮ ለክብሩ የተቀነቀነለት ብቸኛ አርቲስት
17 ቴዲ አፍሮ በጥቂት ዘፋኞች ዓይን
18 የቴዲ አፍሮና የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ምናባዊ ቆይታ

**ክፍል አምስት**
**የቴዲ አፍሮ ታላላቅ ፈተናዎች**------------------------------------------------------- 129

19 ‹‹እግዚአብሔር በክፉ አይፈትንም››
20 በቴዲ መታሰር ያጋጠመ ታላቅ ክፍተት!!
21 ቴዲ አፍሮ የማን ነው?
22 ማጠቃለያ



# የፀሐፊው መልዕክት

ይህንን «የቴዲ አፍሮ የታላቅነት ምስጢር» የተሰኘውን መጽሐፍ ለመጻፍ ያነሳሳኝ ለቴዲ አፍሮ ያለኝ በቃላት ሊገለጽ የማይችል የማይሞት እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ፍቅር ነው እንጂ በግብዝነት በስም መኖርን ፈልጌ ወይም ጥቅም አገኝበታለሁ ብዬ ተመኝቼ አይደለም።

ከዚህ ሌላ ዋነኛ ምክንያቴ እንድ ታሪክ ሰሪ ግለሰብ ለሀገሩ ላበረከተው ታላቅ ታሪካዊ ተግባር በህይወት እያለ ማሞገስና ከዚህ የላቀ ድንቅ ታሪክ እንዲያስመዘግብ ማበረታታት የሁላችን ሃላፊነት ሊሆን ይገባል ከሚል ቅዱስ ዓላማ ተነሳስቼ ነው። ምክንያቱም በየተሰማሩበት ሙያ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ክቡር ሥራን ሰርተው ህያው ታሪክ ለሚያስመዘግቡ እንደ ቴዲ ያሉ ታሪካዊ ጀግኖች በሞት እስኪለዩን ሳንጠብቅ ለእነሱ ያለን ውዴታና አክብሮት በህይወት እያሉ ብንገልጽላቸው ከአስተማሪነቱም በላይ ሌሎች ታሪካዊ ጀግኖችም እንዲፈጠሩ ማነሳሳት ነው ብዬ ስላመንኩ ነው። ታላቅነታቸውን ለቀጣዩ ትውልድ በታሪክነት ማቆየት መቻልም የተቀደሰ ታላቅ ተግባር ነው።

ከዚህ በተረፈ ማንም አንባቢ ይህን መጽሐፍ፣ ፍቅርና ቅንነትን አብዝታ በምትሻ ንፁህ ልብ እንደተጻፈ ተገንዝቦ በቅንነት እንዲያነብልኝ በትህትና እጠይቃለሁ።

ሌላው ለውድ አንባቢዎቼ ማሳሰብ የምፈልገው ይህ መጽሐፍ ሙሉ ለሙሉ የቴዲ አፍሮ የህይወት ታሪክ የሚገልጽ ግለ-ታሪክ አለመሆኑ ነው። እንዲያውም በአጭሩ ለቴዲ ያለኝን ክብር የገለጽኩበት መጽሐፈ-መወድስ ቢባል ይሻላል። መጽሐፉ ሲጻፍ ቴዲ የሚያውቀው አንዳችም ነገር እንዳልነበረም መግለጽ እወዳለሁ።

በመጨረሻም በመጽሐፉ ይዘት ቅር የተሰኘ አንባቢ ወይም አካል ከተገኘ፣ እኔ እሱን እሱ ደግሞ እኔን መሆን እንደማንችል አበክሬ ከመግለጽ በቀር ሌላ የምለው ነገር የለኝም። ምክንያቱም ዛሬን ባየሁበት አይኔ ነገን አይቼ አልረዳውምና። ነገር ግን በአፃፃፍ ብቃቴ ያልተደሰቱና በቅን ልቦና ሊያርሙኝ ፈቃደኛ የሆኑ አንባቢዎቼ አስተያየታቸውን ለመቀበል ዝግጁ መሆኔን በአክብሮት እገልፃለሁ።

«ፍቅር ያሸንፋል»

አቤል ዘበነ





# ክፍል አንድ

## የቴዲ አፍሮ የልጅነት ሕይወትና ለሙዚቃ የከፈለው ታላቅ መስዋዕትነት

1

### ቴዲ አፍሮ ከየት ወዴት?

**“እኔ ከማንም አላንስም። ወደፊት ምርጥ ዘፋኝ እሆናለሁ!”**

**ቴዲ አፍሮ**

በህፃንነቱ ግጥም ጽፎ፣ ዜማ ቀምሮ ለሚወደው ውሻው የንጉራጉርለት ነበር። ይህ በልጅነት ጊዜ የተጀመረው የሙዚቃ አፍላ ፍቅር ግን በቤተሰቡ ዘንድ አልተወደደለትም። ቤተሰቡ ወደ ሙዚቃ ዓለም እንዲገባ ፍፁም ፈቃደኛ አልነበሩም። ነብሱን ከሙዚቃ

ለመለየት ሲባል ከቤተሰቦቹ በኩል ቁጣ፣ መገረፍ፣ የግጥም ደብተሮቹ እስከመቀደድና የተለያዩ መአቅቦች ደርሰውበታል፡፡ እሱ ግን ሙዚቃን ሊተዋት በጀ አላለም፡፡ እንዲያውም ይበልጥ እልህ ውስጥ ገባ፡፡ እናም ገና ከጠዋቱ ለማንም ጆሮ መስጠት እንደሌለበት ለራሱ ቃል ገባ፡፡ የልቡን ትርታ ብቻ በማድመጥም "ከሙዚቃ ሌላ ህይወት የለኝም" ሲል ለራሱ አወጀ፡፡

እርግጥ ይህ ብላቴና መስታወት ጥበብ ከበብ ውስጥ ተሳትፎ ያደርግ በነበረበት ወቅት ከሙዚቃ ይልቅ ለመድረክ ድራማዎች ጊዜውን ይሰጥ ነበር፡፡ "ኮብራው" የተሰኘና ሌሎች የመድረክ ድራማዎችን በመጻፍ መሪ ተዋናይ ሆኖ ሰርቷል፡፡ ታድያ በዚያን ጊዜም ቢሆን የሙዚቃን ሥራ ጐን ለጐን ያስኬድ ነበር፡፡

"ሙዚቃን መስራት አለብኝ" ብሎ ለህልሙ መሳካት እንቅስቃሴ ማድረግ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ችግሮችና ውጣ ውረዶች፣ ፈፅሞ ሊታሰፉ የማይመስሉ ብዙ ከባባድ ፈተናዎች አጋጥመውታል፡፡ እሱ ግን ለሚያጋጥሙት ችግሮችና ፈተናዎች አልተንበረከከም፡፡ ለሙዚቃ ያለው ፍቅር ሲል ማንም ዘፋኝ ያልከፈለው መስዋዕትነት፣ ያላየው የጥበብ ፈተና አልነበረም፡፡ ከእሱ ቀድመው የዘፈን መድረክ በረገጡ ጥቂት ዘፋኞች ፊት ተገርፏል፡፡ መዝፈን እየቻለ ልክ ማይክ ሲጨብጥ "መዝፈን አትችልም" በሚል የንቀት ንግግር እንዳይዘፍን ተደርጐ በአሳፋሪ ሁኔታ ከመድረክ ተባሯል፡፡ "ስንት ካሴት ያሳተሙ ዘፋኞች እያሉ አንተ ልትዘፍን ነወይ?" የሚሉና ሌሎች ሞራልን የሚነኩ ብዙ አሳፋሪ ኃይለ ቃላት ተሰንዝረውበታል፡፡

የልቡን ህልምና ታላቅ ራዕይ እሱ ራሱ ጠንቅቆ የሚያውቀው ይህ አንድ ፍሬ ብላቴና ግን ለነዚህ ሁሉ መሰናክሎች እጁን አልሰጠም፡፡ እነዚያን መሰናክሎችና ጋሬጣዎች በመፍራት አንድም ቀን ወደ ኋላ በማፈግፈግ የሰነፈበት ወቅት አልነበረም፡፡ እንዲያውም በልበ ሙሉነት "እኔ ከማንም አላንስም፡፡ ወደፊት ምርጥ ዘፋኝ እሆናለሁ" ብሎ ለገዛ ራሱ የትንቢት ቃሉን እስከማወጅ ደርሷል፡፡





እናም ይህ ታላቅ ሥራ ለመስራት ታላቅ ህልም አንግቦ በቆራጥነት የተነሳሳው ብላቴና፣ የትንቢት ቃሉን ዕውን ያደርግ ዘንድ ሌት ተቀን በርትቶ መስራት ጀመረ፡፡ ከአጠገቡ ማንም አይዞህ ባይ እንደሌለ ቢያውቅም፣ ህልሙን ለማሳካት ጉዞውን በጽናት ወደፊት ቀጠለ፡፡ ከጥበብ ምርኩዝ ሌላ ማንም ሊሞረከዝበትና ሊመካበት የሚችል ሁነኛ ደጋፊ እንደሌለው ቢረዳም፣ ሙዚቃን ጠንቅቃ የተረዳችው ነፍሱ ግን አብባ ለፍሬ የምትበቃበትን ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ሁሌም ሹክ ትለው ነበር፡፡

ሆኖም ይህ ትንቢት የተገለጸለት ለእሱ ብቻ ነበር፡፡ ከእሱ ሌላ ብላቴናው ዛሬ ካለበት የገዘፈ ስመ ጥር ደረጃ ይደርሳል ብሎ የገመተ አንድም ሰው አልነበረም፡፡ ምናልባት ያ ወላጅ አባቱ ካሳሁን ግርማዋ ካልሆነ በቀር፡፡

ይህ ብላቴና ቴዎድሮስ ካሳሁን ነው፡፡ በአሁን ሰዓት ሁሉ ሰው በፍቅር የሚወደው፣ የሁሉ ሰው የፍላጐት ምንጭ የሆነ፣ ፍቅርና ሰላምን አብዝቶ የሚሰብክ የጥበብ ሙያ በሚሰራው ምጡቅ ሙዚቃ የኢትዮጵያ ኩራት የሆነ ምርጥ ከያኔ፡፡

ጊዜው ብዙም አልራቀም - በ80ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ነበር፡፡ ይህ ቴዎድሮስ ካሳሁን የተባለው ወጣት ከዕለታት አንድ ቀን ድምጹን ለማስገምገም ወደ ሙዚቃ አቀናባሪው ዳዊት ጽጌ ያመራል፡፡ ዳዊት ከጓደኞቹ ጋር ሙዚቃ በመስራት ላይ ነበር፡፡

ተዋወቁ፡፡ ዳዊት ጽጌ ቴዲን የደስ ደስ ያለው፣ ሳቂታ ወጣት ሆኖ አገኘው፡፡ የደም ግባቱ ማንንም ተመልካች ይማርካል፡፡ ቁምነገረኝነቱና ከዕድሜው ፈጥኖ የበሰለው አዕምሮውስ ቢሆን?

ዳዊት ዕጌ የቴዲን ብስለትና ቁም ነገረኝነት ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ እንግዶቹን ሸኝቶ እሱና ቴዎድሮስ ካሳሁን ብቻቸውን ቀርተው ጨዋታ በጀመሩበት በደቂቃዎች ውስጥ ነው ቴዲ በተለይ ስለ ሙዚቃ ጥልቅ ዕውቀት እንዳለው የተረዳው፡፡

እናም የጋራ ሙያቸውን በተመለከተ አንዳንድ ቁም ነገሮችን ከተጨዋወቱ በኋላ ዳዊት ጽጌ ቴዲን ወደ ሙዚቃ መሳሪያው ተጠግቶ እንዲዘፍን ይጠይቀዋል። የሙዚቃ ባለሞያው ዳዊት ጽጌ ደግሞ የሙዚቃ መሳሪያውን መጫወት ይጀምራል። በዚህ መሀል ቴዲ አፍሮ ከክቡር ዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ገሰሰ አንድ ዘፈን በማስቀደም ከተጫወተ በኋላ ስለ ሀገር የሚያወሳውን የቴዎድሮስ ታደሰን "እምዬ ሀገሬ" የሚለውን ዘፈን አስከተለ። ይኸኔ ነበር ዳዊት ጽጌ በቴዲ የአዘፋፈን ስልት፣ በድምፅ አወጣጡ፣ በመድረክ አቋቋሙ እስከ ማይክ አያያዙ በመገረም በአድናቆት አፉን ከፍቶ የቀረው።

ፊፅሞ ጀማሪ ዘፋኝ አልመስልህ አለው። እንደውም ብዙ ልምድ አለን ከሚሉት ድምፃውያን በልጦ ታየው። በዚያን ወቅት ስለነበረው ሁኔታ ዳዊት ጽጌ ሲያስረዳ "ቴዲ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትልቅ ደረጃ እንደሚደርስ ወዲያውኑ ወለል ብሎ ታየኝ" ይላል።

ዳዊት ፅጌ በቴዲ የፈጠራ ችሎታ እጅግ ተገርሟል። በተፈጥሮ የተለገሰው የታመቀ የጥበብ ክህሎት እንዳለው ወለል ብሎ ታይቶታል። በዚህም የሁለቱ ግንኙነት ከቀን ወደ ቀን እየጨመረና እየጎለበተ መሄድ ጀመረ።

ቴዲም ለዳዊት ፅጌ ወደፊት በሙዚቃ ህይወት እንቱ የተባለ ሰው ለመሆን እንደሚፈልግና የግሉ የሆነ ባንድም ለማቋቋም እንደሚመኝ፣ የሀገሩን የሙዚቃ ዕድገት በአንድ ደረጃ ከፍ የማድረግ እቅድ እንዳለው ያጫውተዋል። ዳዊትም "ያሰብከው ሁሉ ይሆንልሀል። አንተ ብቻ ጠንክረህ ከመስራት አትስነፍ እንጂ" ሲል ይመክረዋል።

ቴዲም "ሁሉንም ነገር ለፈጣሪዬ አሳልፌ እሰጣለሁ። እሱ ደግሞ የሚሳነው ነገር ስለሌለ የኔን የልጁን ሀሳብ እውን ያደርግልኛል" ሲል ይመልስለታል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቴዲና የዳዊት ፅጌ ግንኙነት እየተጠናከረ መጣ። በዚህ ወቅት ቴዲ ከነብሱ ጋር የተቆራኘችውን የጥበብ





ህልሙን ለማሳካት ሌት ተቀን ጠንክሮ ይሰራ ነበር። እርግጥ ከፊቱ ላይ አንድ ወሳኝና ከባድ ችግር ተደቅኖበታል። እርሱም ወደ ሙዚቃ ዓለም ለመቀላቀል በተሰናዳበት ወቅት በርካታ ድምጻውያን በህዝብ ተቀባይነት አግኝተው የተወደዱበት ጊዜ ነበር። እናም እነዚህን ድምጻውያን ጥሶ ማለፍ ይቻለኝ ይሆን የሚል ስጋት ይዞት ነበር። ይሁንና ቴዲ ጠንካራ፣ ደፋርና ወኔያም ነበርና በመጨረሻ በራሱ ግጥምና ዜማ፣ በምርጥ የሙዚቃ ቅንብር፣ በሚጣፈጥ የድምጽ ቃና አንድ ምርጥ አልበም ሰርቶ ጨረሰ። አልበሙም "ተማፀንኲት" ሲል ሰየመው።

ቴዲ ይህንን የሙዚቃ አልበም ሰርቶ ማጠናቀቅ የቻለው ብዙ ፈታኝ መሰናክሎችና እጅግ አልህ አስጨራሽ ጋሬጣዎችን በጽሎትና በትዕግስት አልፎ ነው። ያሰበውን ለመሆን የሚተጋ ጠንካራ አርቲስት ባይሆን ኖሮ እነዚያ ፈታኝ መሰናክሎች በአጭሩ መንገድ ላይ ያስቀሩት ነበር። እሱ ግን የትኛውን ጋሬጣ በድል የመወጣት እምቅ አቅም የታደለ ጠንካራ አርቲስት ስለሆነ የኋላ ኋላ ይህን ምርጥ የበኩር ሥራውን አጠናቅቆ ለአንድ የሙዚቃ አሳታሚ ለማቅረብ በቃ።

አሁንም ቢሆን ሁሉም ነገር እንደጠበቀው አልጋ በአልጋ አልሆነለትም። ምንም እንኳ ይህ የመጀመሪያው ካሴቱ በርካታ ጥልቅና ምጡቅ ሃሳቦችን የተካተቱበት፣ የአዘፋፈን ስልቱም በወቅቱ ከነበረው የሀገራችን ዘፈን ወጣ ብሎ ለጆሮ የሚስማማ ምርጥ ሥራ ቢሆንም፣ ቴዲ ይህንን አልበሙም በቀላሉ ወደ ህዝብ ጆሮ ማድረስ አልተቻለውም ነበር። በዚያም ላይ ካሴቱን ለዚያ አከፋፋይ ሙዚቃ ቤት የሸጠለት እዚህ ግባ በማይባል ገንዘብ ነበር። ቴዲ ሙዚቃን ለገንዘብ ጥቅም ሲል የማይሰራ፣ ሙያውን የሚያከብር ወጣት በመሆኑ በገንዘቡ አነስተኛነት እንዳች ቅሬታ አልተሰማውም። ዋነኛ ምኞቱና ፍላጐቱ አልበሙ ህዝብ ጆሮ ጋ እንዲደርስለት ብቻ ነበር።

ሙዚቃ ቤቱ ግን ካሴቱ አባዝቶ ገበያ ላይ ሊያውለው አልፈቀደም። ጊዜ አልፎ ጊዜ ተተካ። ሆኖም ታታሪው ወጣት

ቴዎድሮስ በዚህ ተስፋ ቆርጦ እጁን አጣምሮ አልተቀመጠም። ገና ነፍስ እውቆ ክፉና ደጉን መለየት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ለሙዚቃ ፍቅር ሲል የማይሆነውን ነገር ሁሉ ለመሆን ቆርጦ የተነሳ መንፈሰ ጽኑ ሰው ነውና ጥበብን ሰንቆ፣ ቅንነቱን በልቡ አንግቦ ፊቱን ወደ ቀጣይ ህልሙ አዞረ - የራሱን ባንድ የማቋቋም ህልም!

## ቴዎድሮስ ካሳሁን ለምን ቴዲ አፍሮ ተባለ?

ቴዲ የ12 ክፍል ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ሰፊ ጊዜ ስለነበረው ከመቼውም በተለየ ሁኔታ የዚያን ጊዜ ነበር በእግር በፈረስ ለሙዚቃ መጋለበና መሮጥ የጀመረው። በ1991ዓ.ም አካባቢ ከያሬድ ሙዚቃ ቤት የተመረቁ ባለሙያዎች እነ ኤሊያስ መልካ (ጊታር)፣ ሁንእንተ ሙሉ (ድራም)፣ ቢኒያም በድሩ (ኪ. ቦርድ)፣ ምስጋና (ቤዝ ጊታር) እየተጫወቱ ላስታስ የተባለ የሙዚቃ ባንድ አቋቁመው ነበር።

በዚያን ጊዜ ደግሞ ቴዲ የራሱ የሆነ የግሉ ባንድ እንዲኖረው የሚመኝበት ሰዓት ነበር። እናም ቴዎድሮስ ካሳሁን፣ ሽዋንዳኝ ሀይሉ፣ ግሩም መዝሙርና ዳዊት ግሩም ስለ ላስታስ ባንድ ይነጋገሩ ጀመሩ። ላስታስ ባንድ በወቅቱ በቂ የሙዚቃ መሳሪያዎችና ልምምድ የሚያደርግበት ሁነኛ ቦታ አልነበረውም። ዳዊት ግሩም በወቅቱ ብር ስለነበረው ለነ ቴዲ፣ ሽዋንዳኝና ወንድሙ ለሆነው ለግሩም መዝሙር መሳሪያ መግዣ የሚሆን ብር ይሰጣቸዋል። ብሩንም ሲሰጣቸው በብድር መልክ ሳይሆን ሰርታችሁ ስታገኙ ትከፍሉኛላችሁ በሚል ቅንነት በተሞላው ፍቅር ነበር።

በተገኘው ብር ላይ ቴዲ የራሱን ብር በመጨመር በወቅቱ የነበሩትን ጥሩ ጥሩ መሳሪያዎች ይገዙና ላስታስ ከተባለው የሙዚቃ ባንድ ጋር አብሮ መስራት እንደሚፈልጉ ገለጹላቸው። የላስታስ ባንድ አባላት እጅግ ደስ ተሰኙ። ምክንያቱም በቂ የሙዚቃ መሳሪያና የልምምድ ቦታ ሊሟላላቸው ነውና። ስለዚህም ኤልያስ መልካ፣





ሁንእንተ ሙሉ፣ ቢኒያም በድሩና ምስጋና የተባሉ የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾች ከቴዲ፣ ከሽዋንዳኝ ሀይሉ፣ ከግሩም መዝሙርና ከዳዊት ግሩም ጋር በመሆን ጥምረትን ፈጠሩ።

እናም እነዚህ የሙዚቃ ባለሙያዎች በፍቅር፣ በመተጋገዝና በመቻቻል መልካም ውህደትን ፈጥረው በስራቸው ውጤት ለማምጣት ቀን ከሌት መሯሯጥ ያዙ። ብዙም ሳይቆዩ የባንዱ ስያሜ ከላስታስ ወደ አፍሮ ሳውንድ ባንድ ቀየሩት። በባንዱ ስም መቀየር አንዳቸውም ቅር አልተሰኙም። ምክንያቱም የነዚህ ባለሙያዎች ትኩረት ምርጥ ስራን መስራት ብቻ ነበር። ቴዲና ሽዋንዳኝ በዚህ ባንድ ውስጥ ይዘፍኑ ነበር።

ቴዲ፣ በወቅቱ የቴዎድሮስ ታደሰን፣ የንዋይ ደበበንና የክቡር አርቲስት ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠን ዘፈኖች ይጫወት ነበር። ባንዱንም በበላይነት በመቆጣጠርና በመምራት ቴዲ ትልቅ ድርሻና ሀላፊነት ነበረው። ቴዲ ዘወትር ጓደኞችን በተለያዩ ቀልዶች ያዝናናቸውም ነበር። በአፍሮ ሳውንድ ባንድ ውስጥ የሥራ ባልደረቦቹ በሙሉ "በቴዲ ቀልድ ሁሌ እንደሳቅን ነበር" በማለት ዛሬ ድረስ ይመሰክሩለታል።

መሳሪያ ተጫዋቾቹ በሙሉ እንደሚሉት ከሆነ ቴዎድሮስ ካሳሁን፣ ሽዋንዳኝ ሀይሉና ግሩም መዝሙር የአፍሮ ሳውንድ ባለቤቶች ተብለው የሚጠቀሱ ሲሆን፣ "ቴዲ ግን እንደ ባንዱ ባለቤት ብቻ ሳይሆን እንደ ቅርብ ወንድማችን ነበር የምናየው" ይሉታል። አክለውም "ራሱን እየጎዳ ለእኛ ብዙ ነገር ያደርግልን ነበር። በየትኛውም ቦታና ስፍራ ለፍቅር ትልቅ ቦታ የሚሰጥ ሩህሩህ ሰው ነው" በማለት እማኝነታቸው ይሰጡታል።

አፍሮ ሳውንድ ባንድ ሲቋቋም ብዙ መዋዕለ ንዋይ ፈሰስ ያደረገው ዳዊት መዝሙር ስድስት ኪሎ አካባቢ ኮፊ ሀውስ /Coffee House/ ሲከፍት እሁድ እሁድ በዚያ ውስጥ የሙዚቃ ስራዎችን ያቀርቡም ነበር። በኮፊ ሀውሱ ውስጥ ሊዝናኑ የሚመጡ ሰዎች

በሙሉ ቴዎድሮስ ካሳሁን በሚዘፍናቸው ዘፈኖች እጅግ በጣም ደስተኞች ነበሩ። ቴዲም በተደጋጋሚ ለመሸለም በቅቷል። አፍሮ ሳውንድ ባንድ በተለያዩ የሰርግ ዝግጅቶች ላይ በመገኘትም ዕድምተኞቹን ያዝናና፣ ድግሱንም ያደምቅ ነበር። የሚገኘውንም ገቢ ለመሳሪያ ተጫዋቾቹ የሚገባቸውን ክፍያ ከተሠጠ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ በባንዱ ባለቤቶች በነቴዲ፣ ሸዋንዳኝና ግሩም በኩል ለምን እንደሚውል የሚወስን ይሆናል።

መሳሪያ ተጫዋቾቹ በሙሉ የዘወትር ጥረታቸው አዲስ ነገርን መፍጠር ስለነበር፣ በዚህ ለሙያው ያላቸው ታላቅ ፍቅር የተነሳ ቴዲ ልዩ ፍቅርና አክብሮት ይሰጣቸው ነበር። ዘወትርም ከጎናቸው በመቆም ምርጥ ስራን ለመስራት ይጣጣር ነበር።

እንግዲህ በዚህ ጊዜ ነበር ቴዎድሮስ ካሳሁን የሚለው ስሙ በቴዲ አፍሮ ተተክቶ ዋነኛ መጠሪያ ስሙ ለመሆን የበቃው። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ማንም ሰው ቴዎድሮስ ብሎ የሚጠራው ጠፋ። ሁሉም ሰው በአንድ ድምፅ "ቴዲ አፍሮ" እያለ ይጠራው ጀመር። "አፍሮ" የሚለው ቅፅል መጠሪያ ለቴዲ ባንዱን ከማስታወሻነቱ በተጨማሪ ሙዚቃን ይበልጥ ያጣጣመበት ጊዜ በመሆኑና ባንድ ለማቋቋም የነበረው ህልም እውን የሆነበት ወቅትም ስለሆነ ነው። ከአፍሮ ሳውንድ ባንድ ውስጥ አፍሮ የምትለዋን ቃል በመውሰድ ነው ቴዲ አፍሮ የተባለው። ይህ ደግሞ የሚያሳየው ቴዲ፣ ለአፍሮ ሳውንድ ባንድ ከመስራችነትና ከባለቤትነትም በተጨማሪ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳበረከተ ነው።

የባንዱ አባላት በአንድ ዕለተ ሀሙስ የሆነ ሰርግ ላይ ይሰራሉ። በዚህ ቀን ቴዲ አፍሮ ሲዘፍን የሰርጉ ታዳሚ በቴዲ የአዘፋፈን ብቃት ከመጠን በላይ ተደስቶ ነበርና ከሰርገኞቹ መሀል አንዱ ለቴዲ ሶስት መቶ ብር ይሸልመዋል። በወቅቱ ገንዘቡ ዳጎስ ያለ በመሆኑ ሁሉም የባንዱ አባላት ሽልማቱ ደስታን ፈጥሮላቸዋል። ያንኑ ዕለት ማታ ደግሞ ሰርግ ውለው ደከመን ሳይሉ ሂልተን ሆቴል ውስጥ ሙዚቃቸውን በማቅረብ ህዝቡን እያስደሰቱት ነበር። እናም





ቴዲ የሚዘፍንበት ተራ ደረሰና የክቡር ዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ገሰሰን "የህይወቴ ህይወት" የተሰኘውን ዜማ ሲጫወት በአዘፋፈን ስልቱ፣ በእንቅስቃሴውና በጣዕሙ-ቅላፄው በመማረክ አንድ የውጭ ዜጋ ወደ መድረኩ ሲንደረደር መጥቶ መቶ የአሜሪካን ዶላር ይሸልመዋል። ቴዲ አፍሮም በሚገባ ዘፈኑን ተጫውቶ ከመድረክ ሲወርድ የሚዝናናው ታዳሚ በደማቅ ጭብጨባ ሸኘው። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ነገሮች ለቴዲ እየቀለሉ እንጂ እየከበዱ አልመጡም።

በዚህም ቴዲ ገና አንድ የሙዚቃ አልበም ሳያሳትም የተሳካለት ዘፋኝ ሲሆን እንደሚችል አስመሰከረ።

ቴዲ በዚሁ አፍሮ ሳውንድ ባንድ ውስጥ ሳለ ለቀጣዩ አልበሙ የሚሆኑ ጣፋጭና ማራኪ ዜማዎችን ራሱ በኪቦርድ እያጀበ ይጫወት ነበር። በየትኛውም የሥራ መስክ ላይ እንደሚስተዋለው በባንዶች ውስጥም እርስ በርስ አለመግባባትና መቃቃር ሲፈጠር ይችላል። ይህም ችግር በአፍሮ ሳውንድ ባንድ ውስጥ ተከስቶ ነበር።

ታዲያ የሚፈጠሩትን አለመግባባቶች ሁሉ ቴዲ በብልሃትና በትዕግስት ያረግባቸው ነበር። "ቴዲ ቂም መያዝ ብሎ ነገር የማያውቅ ችጅግ ቀና ሰው ነው" ይላሉ አንዳንድ ባንዱ ውስጥ አብረዉት የነበሩ የሥራ ባልደረቦቹ። "እንደውም አስታራቂ ሀሳብን በማምጣት ፀብና ጥላቻን ከመሀከላችን ለማስወገድ ይጥር ነበር። ዘወትር ‹ቅን ነገር እናስብ፣ መልካም ነገር ብቻ እንስራ። ከፀብ ምን ይገኛል? ከመዋደድና ከፍቅር ግን አንድነት ይኖረናል› በማለት ይመክረንም ነበር።

የኋላ ኋላ ሁሉም በየፊናው የየግል ሀሳብን ማውጠንጠን ሲጀምሩ ከድራመሩ ሁንአንተ ሙሉ ጋር በሀሳብ አለመግባባት ተፈጠረና ሁንአንተ ባንዱን ሲሰናበት ሌሎቹም የሙዚቃ መሳሪያ ባለሙያዎች እንደሱ የመነጣጠል አቅጣጫ ውስጥ ገቡ።

ቴዲም ትኩረቱን ሙሉ ለሙሉ በካሴት ሥራው ላይ አሳረፈ። እናም ከብርቱ ጥረትና ትግል በኋላ በ1993ዓ.ም መጨረሻ

አካባቢ ደረጃውን የጠበቀና የማንንም ጆሮ የሚማርክ ዜማና ግጥም በጥንቃቄ በመቀመር "አቡጊዳ" የተሰኘውን አልበሙን ለህዝብ ጆሮ አደረሰ። ቴዲ አቡጊዳን እየሰራ ባለበት ወቅት ለተወሰኑ ሰዎችና ዘፋኞች አስገምግሟቸው ነበር። እነሱ ሆዬ "ከተለመደው ቅኝት ወጣ ያለ በመሆኑ ማን ይሰማሃል?" በማለት ከንፈር በመምጠጥ ተሳልቀውበት ነበር። ሆኖም ቴዲ አንድ ነገር በልቡ ውስጥ ስለበራለትና ግልጥ ብሎ ስለታየው ጉዞውን መንፈሱ በመራው መንገድ ቀጠለ።

አልቀየም - ትንቢቱም ተገለጠ። ያቺ ተናፋቂዋ ክብርት ቀን ደርሳ "አቡጊዳ" የተሰኘውን አልበሙ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ደረሰች። በትላልቅ ናይት ክለቦች ውስጥ እጅግ ተወዳጅና ተፈላጊ የነበረው ቴዲ አፍሮ በዚህ አንድ ካሴት ብቻ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚሊዮኖችን ቀልብ ሳበ። "አንድ ቀን ምርጥ ድምጻዊ እሆናለሁ" ብሎ እንደተነበየው ሁሉ እውነትም ማንነቱን አስመስክሮ ታላቅ ድልና ስኬት ተቀዳጀ። "አቡጊዳ" በህዝብ ዘንድ ከዳር እስከ ዳር ወደር የለሽ ተቀባይነትን ተጐናጸፈ። በየቦታው የቴዲ ዘፈን መደመጥ የተለመደ ክስተት ሆነ። ብዙ ሰዎች ቴዲ አፍሮ ስለተባለው አስደናቂ ወጣት መነጋገር ጀመሩ። ሥራውን በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ አሜን ብሎ ወደደለት።

ካሴቱ ለህዝብ ተሸጦ ድንበርና ኬላ ጥሶ ለማለፍ የሳምንት ጊዜ አልፈጀበትም ነበር። በዚህም የተነሳ የቴዲ የታዋቂነትና የተፈላጊነት መጠን በአንድ የዘፈን ካሴቱ ገነነ። ጥበብን ምርኩዝ አድርጎ በፈጠረው እግዚአብሔር ተመክቶ በተስፋ የተነሳው ይሄ ብላቴና ታሪክ ሰርቶ ተገኘ።

አቡጊዳን ካሴቱ ለራሱ ለቴዲም ሆነ "ይሄ ስራ ወጣ ያለ ዘመናዊ በመሆኑ ማን ይሰማሃል?" ብለው የንቀት ቃል ለወረወሩለት ሰዎች ሳይቀር ትዝታው የማይፋቅ ደማቅ ታሪክ ጥሎ አለፈ።





የቴዲ ዘፈኖች የወንጌል ስብከት ያህል በየቤቱ እያንኳኩ ዘልቀው የመግባት እድላቸው ሰፊና የትየለሌ ሆነ። ካሴቱንም ያዳመጡ ሁሉ "ቴዲ በኢትዮጵያ ምድር ላይ አዲስ የዘፈን ታሪክ የሰራ ጊዜ የፈጠረው የምርጦች ምርጥ" ሲሉ አወደሱት። "የዘፈን ጥማታችንን በቴዲ ዘፈን ቆረጥን" በማለት በርካቶች ስለብቃቱ መስክሩለት። በአንድ ጊዜም ሚሊዮኖች አድናቂዎች ለማትረፍ በቃ።

ከአድናቂዎቹ በቀረበለት ጥያቄም መሰረት በምሽት ክበብ ውስጥ የሙዚቃ ስራውን ማቅረብ የጀመረ ጊዜ አስገራሚ የህዝብ ጐርፍ በመታየቱ ጉድ ተባለ። መዝናኛው አልበቃ ብሏቸው ከቤት ውጪ ሆነው የሚያምር ድምጹን በደስታ የሚኮመኩሙ ብዙዎች ነበሩ። በሌሎች ቀደምት ዘፋኞች ተይዞ የነበረው የዘፈን መሪነት በአንድ የዘፈን ካሴት ለመረከብና ታላቅ የጥበብ ቀማሪነቱን ለማስመስከር የቻለ ድንቅ አርቲስት ነው እያለ ህዝቡ ለቴዲ እውነተኛ ፍቅርና አድናቆቱን ቸረው። በተለይ ቴዲ በተፈጥሮ የተሰገለውን በወላጅ አባቱ ምክር የዳበረውን መልካም ባህሪው የበለጠ እንዲወደድ ታላቅ አስተዋጽኦ አደረገለት።

ይህ "አቡጊዳ" የተሰኘ አልበም በሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ታሪክን የሰራ ቁጥር አንድ አልበም ለመሰኘት ሲበቃ፣ ድምጻዊው ቴዲ አፍሮም ለሙዚቃ ዕድገት የተፈጠረ ምርጥ ከያኔ የሚል ማዕረግ አላበሰው።

አንዳንድ የሙዚቃ ባለሙያዎች የግጥሙን መልዕክትና ብስለት፣ የዜማውን ጥንካሬና መስህብነት፣ እንዲሁም የሚጠቀምባቸው ግብአተ ድምጾች አጣጥመው ቴዲን እንደማንም ተራ ድምጻዊ "ድምጻዊ" ብቻ ብለው ለማለፍ አልፈቀዱም። ምክንያቱም ባካሄዱት ጥናት መሠረት ከሌሎች ዘፋኞች የሚለይበትን ዓብይት ነገሮችን ነቅሰው አውጥተዋል። በዚህም በግጥሞቹ ጥልቅነትና ፍልስፍናዊ ይዘት፣ በሚቀምራቸው እጹብ ድንቅ ጣዕመ ዜማዎች በአንድ ድምጽ አጀብ ጉድ ብለዉለታል።

ቴዲ አፍሮ አቡጊዳ የተሰኘ የሙዚቃ ሥራው ጊዜ ሰጥቶ፣ እጅግ ደክሞበት በጥንቃቄ ለአድማጭ ጆሮ ያቀረበው በመሆኑ በህዝብ ዘንድ ያገኘው ተቀባይነት ለቴዲ እስካሁኗ ሰዓት ታላቅ ትዝታ ጥሎበት አልፏል። እናም ቴዲ አፍሮ በልጅነት ዕድሜው ሙዚቃን ሀ ብሎ ሲጀምር በልቡ ያለውን፣ በአዕምሮው የሳለውን የጠበብተኝነት ክብርን በፅናት፣ በከፍተኛ ሞራልና በታላቅ ወኔ በመታገዝ ትንቢቱን በተግባር ገልጦ አሳየ።

ቴዲ መቼም ቢሆን ሊነጥፍ የማይችል የትዕግስት ባለቤትና ገና አንድ ፍሬ ልጅ እያለ የት እንደሚደርስ ፍንትው ብሎ የታየው ሰው በመሆኑ የሁልጊዜ ምኞቱ ትልቅ ትልቁን ነበር - "ትልቅ ተመኝ፣ ትልቅ ነገር ታገኝ ዘንድ" እንዲሉ።

## "ተማፀንኪት"
## የበኹር ልጅነቱን የተነጠቀ አልበም

አሁን ቴዲ አፍሮ ዝነኛ ሰው ሆኗል። ዘፈኑን ሰምቶ የአድናቆት እጁን በአፉ ያልጫነ ከቶ ማን ሊገኝ?

በ1968ዓ.ም በአዲስ አበባ ልዩ ስሙ ኳስ ሜዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ከሁለት የጥበብ ሰዎች፣ ማለትም ከጋዜጠኛ ካሳሁን ግርማሞና ከአርቲስት ጥላዬ አራጌ የተወለደው የዛሬው ዝነኛ ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን አሁን የሁሉም ሰው መነጋገሪያ፣ የሁሉም ሰው የዓይን ማረፊያ ሆኗል። በምኞት ብቻ ያልቀረው ቴዲ በከፍተኛ ጥረት ምኞቱን ዕውን ከማድረጉም አልፎ ለሚሰራው ሥራ ክብርና ኃላፊነት የሚሰማው ታላቅ አርቲስት ነው። ሙያውን የሚያከብር ጠንቃቃ አርቲስት መሆኑንም አስመስክሯል። በዚህም ትክክለኛ እሉነቱን አሳውቋል።

እናም ሁለተኛ አልበሙ "አቡጊዳ" በህዝብ ዘንድ የተቀባይነቱ መጠን ሰማይ ጠቀስ መሆኑ የገባው፣ ያ የቴዲን "ተማፀንኪት"





የተሰኘ የበኩር የሙዚቃ ሥራ ገዝቶ ለወራቶች አፍኖ ለህዝብ ሳያቀርብ ያዘገየው አከፋፋይ ሙዚቃ ቤት "ተማፀንኪት" እንደ ሁለተኛ አልበም በሚመስል አኳኋን ገበያ ላይ ለቀቀው።

በወቅቱ በተፈፀመው ድርጊት ቴዲ ክፉኛ አዝኗል። ስለሁኔታው በዝርዝር በጋዜጣ፣ በመፅሄትና በሬድዮ እውነታውንም ተናግሯል። አንድ ሙዚቃ ቤት አንድን የሙዚቃ አልበም ተዋውሎ ክገዛ በኋላ ከስድስት ወር በላይ ማዘግየት የለበትም።

"ተማፀንኪት" የተሰኘው የቴዲ አልበም እጅግ በጣም የተዋጣ ምርጥ የሙዚቃ ሥራ ሆኖ ሳለ ሙዚቃ ቤቱ ለምን ሊያፍነው ቻለ? በርግጥ ቴዲ ይዞ የቀረበው የሙዚቃ ሥራ በወቅቱ ከነበረው የሀገራችን የሙዚቃ ቅንብር እስታይል ወጣ ያለ በመሆኑ ሙዚቃ ቤቱ ገበያውን ፈርቶት ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል። እንደዚያም ሆኖ በወቅቱ ስንት ለጆሮ የሚሰቀጥጡ የዘፈን ካሴቶች ተባዝተው ለገበያ ይቀርቡ ስለነበረ ያንን የመሰለ ማራኪ አልበም አፍኖ ለረዥም ጊዜ ማቆየቱ ለምን ይሆን የሚለው እንቆቅልሽ ገና በቂ መልስ የተገኘለት አይመስልም።

ለማንኛውም ይህ "ተማፀንኪት" የተባለ አልበም ከብዙ ጊዜያቶች በኋላ ለህዝብ ቢደርስም ህዝቡ ሥራዎቹን ወዷቸዋል። ምክንያቱም ቴዲ በዚያን ወቅት የተጠቀመባቸው ምጡቅ የዜማ ቅንብሮች እጅግ የተዋጣላቸው ከመሆናቸውም በላይ በእያንዳንዱ ዜማ ውስጥ ያሉ ግጥሞች በሳልና በርካታ አይረሴ ቁም ነገሮችን ለማስተላለፍ የቻሉ ሆነው በመገኘታቸው ነው። ቴዲ ይህን ሥራ ሲሰራ "በዚያ በጨቅላነት ዕድሜው ያንን የመሰለ ዜማና ግጥም እንዴት ሊሰራ ቻለ?" በማለት የብዙዎቹን አፍ በአድናቆት አስከፍቷል። እውነትም ቴዲ ለዜማ፣ ለግጥምና ለውብ የሙዚቃ አሬንጅመንት..... በአጠቃላይ ለኪነ-ጥበብ ዕድገት የተፈጠረ ጥበበኛ ነው!

## የናቁት አንጋጠው አዩት

ጎልያድ ቢዝትም
ደርሶ ቢታበይም
አልቀረም መውደቁ
ደርሳ ሰዓቱ
        ቴዲም ወደ ሙዚቃ ዓለም ሲንደረደር ያዩት
        እንደ ዳዊት ትንሽዬ ጠጠር መያዙን ያስተዋሉት
        እነዚያ እንደ ተራ ሰው የገመቱት
        "ዞር በል!" ብለው ያከላበቱት
        "አንተን ብሎ ዘፋኝ!" በማለት ከመድረክ የገፈተሩት
        በሽሙጥ፣ በፌዝ የተሳለቁት
        አፍታም ሳይቆይ ሲያመልጣቸው አዩት፡፡
"ሄደ! ሄደ! ተመነጠቀ" አሉ እጅግ ተገርመው
እሱ ከላይ እነሱ ከታች አንጋጠው
        አዎን፣ ሄደ ገሰገሰ
        ከፍልሚያው ደረሰ
        ወጣም በነፃነት
        ከማማው ለገነት
እነዚያ የናቁት
አንጋጠው እያዩት
        ሞገስ አሸክሞት ታድሎት ከሰማይ
        ከፍ ከፍ ሲል ተመለከቱት በጥበብ ማማ ላይ፡፡





2

# ለቴዲ አፍሮ ስኬት ከፍተኛውን ሚና የተጫወተው የአባቱ የሥነ-ልቡና ጨዋታ

***‹‹ልባም ያደረገኝ አባቴ ነው››***

ቴዲ አፍሮ

በዚህ ዓለም ማንኛውም ህፃን የቤተሰቡን ወይም የወላጆቹን እንክብካቤና ፍቅር ይሻል፡፡ አንድ ሕፃን አድጎ ጥሩ ደረጃ እንዲደርስ የቤተሰቡ ጥብቅ ክትትል፣ ምክርና ተግሳፅ ወሳኝ ሚና አለው፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ከኤክስፕረስ ባንድ ጋር በመሆን ማይክ ጨብጦ የዘፈን ጥማቱን መወጣት የጀመረው፣ በአጭር ዓመታት ውስጥም የራሱን የሙዚቃ ባንድ ለማቋቋምና ዛሬ ደግሞ ለታላቅ ዕውቅና የበቃው ስኬታማው አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን፣ ከወላጅ አባቱ ከጋዜጠኛው ካሳሁን ግርማሞ ጋር የነበረው የልጅነት ህይወት ምን ይመስላል? በዚህ ምዕራፍ በመጠኑ ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡

ካሳሁን ግርማሞ ለልጁ ቴዲ አፍሮ ጥልቅ የሆነ እውነተኛ ፍቅር እንደነበረው በቅርበት የሚያውቋቸው ሰዎች ይመሰክራሉ፡፡ ቴዲ አፍሮም ቢሆን አባቱን የሚወድበት የፍቅር መስፈርት ሚዛን የደፋ፣ ቀልብን የሚገዛ፣ ለሰሚም ሆነ ለተመልካች የሚገርም ለዘላለም ሊጠፋ የማይችል ሐይልና ብርቱ ነው፡፡

ቴዲ አፍሮ ለአባቱ ስላለው ፍቅር ቢፅፍና ቢተርክ አልፎም ተርፎ ቢዘፍን በልቡ ውስጥ ያለውን የአባቱን ፍቅር የሚገልጽለት አይመስለውም፡፡ ጋዜጠኛ ካሳሁን ግርማሞ በህይወት እያለ በጣም ለሚወደው ልጁ ለቴዲ አፍሮ ከአፉ ነጥሎ ያጎርሰው እንደነበር አንዳንድ ለዎች ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ፡፡ በሄደበት ሁሉ የልጁን ስም በማንሳት ስለ ልጁ ቀጣይ ህይወት የሚጨነቅለት እውነተኛ አባትም ነበር፡፡

የካሳሁን ምኞት ቴዲ ዘፋኝ እንዲሆን አልነበረም፡፡ አንቱ የተባለ ዶክተር እንዲሆንለት ይመኝ ነበር፡፡ በምኞት ብቻ ሳይሆን በተግባርም በተለያዩ ጉዳዮች ይረዳው ነበር፡፡ ነገር ግን የቴዲ የነፍስ ጥሪና የልብ ትርታ ወደ ሙዚቃው አደላ፡፡ ይህንን ያስተዋለው ታዋቂው ጋዜጠኛ አባቱ ካሳሁን ግርማሞ ልጁ ወደ ሙዚቃ ህይወት ጠልቆ እንዳይገባ በብርቱ በተደጋጋሚ መክሮታል፤ ከልክሎታል፡፡ ነገር ግን ቴዲ ከጨቅላነቱ አንስቶ ግጥምን ፅፎ፣ ዜማ ቀምሮ፣ ከበሮ እየደለቀ ማንጎራጎር የሚወድ ዜመኛ ነበር፡፡ አባቱ ግን ወደ ጥሩ ህይወት እያቀና እንዳልሆነ በመገመቱና ቀጣይ የህይወት ጉዞውንም ስላሳሰበው ዘወትር ይገስፀውም ይጨነቅለትም ነበር፡፡ በዚያ ዘመን የዘፈን እና የዘፋኝ ህይወት እምብዛም ጥሩና አስደሳች ስላልነበር ወደ ዘፈን ህይወት እንዳይገባ እገዳ እስከ መጣል ደርሶ ነበር፡፡ የዛሬው ዝነኛ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ በሙዚቃ ፍቅር ናውዞ ሙዚቃን የሙጥኝ ብሎ በመያዙ አልተሳካለትም እንጂ፡፡ አባት ሙዚቃን ተው፣ ልጅ አልተውም በሚል የሐሳብ አለመጣጣም ለአንድ ዓመት ያክል ምንም ቃል ሳይለዋወጡ እንደተኮራረፉ በአንድ ቤት ውስጥ አብረው ኖረዋል፡፡





ካሳሁን ስለ ልጁ ቴዲ አፍሮ የወደፊት ህይወት በመጨነቅ ከቅርብ ጓደኞቹ ጋር መወያየት የጀመረው በዚያን ጊዜ ነበር፡፡

ቴዲ ደግሞ መኝታው ክፍል ውስጥ ትራሱን በመቀጣጠል አንሶላና ብርድ ልብስ አልብሶ የተኛ ያስመስልና ማንም ሰው ሳያየው በመስኮት ተንጠልጥሎ በመዝለል እየጠፋ ወደ ናይት ክለብ በመሄድ ይዘፍን ነበር፡፡ በመጨረሻም ምንም እንኳን አባቱ ባለበበትና በተመኘለት መንገድ ባይጓዝም ራሱ በቀየሰው የህይወት ጉዞ ለስኬታማነት የበቃ ጠንካራ አርቲስት ለመሆን ችሏል፡፡ በዚህም የአባቱንም ምኞት በሌላ መልኩ አሳክቷል ማለት ይቻላል፡፡

ቴዲ አፍሮ በወርሀ ሚያዝያ ከታተመው ፅጌረዳ መፅሄት ጋር ስለ አባቱ እንዲህ ሲል ቃሉን ሰጥቶ ነበር፡፡ ‹‹ህፃን ሆኜ ተደናቅፌም ሆነ በሌላ ምክንያት ሳለቅስ አያፅናናኝም ነበር፡፡ ‹ተነሳ፣ የወደከው ራስህ ነህ፤ የጣለህ ሰው ስለሌለ ማልቀስ የለብህም› ይለኛል፡፡ ‹አስራ ስምንት ዓመት ሲሞላህ ደግሞ ከቤት አባርርሃለሁ› በማለት ዝቶብኝ ነበር፡፡ ይህንን ያለኝ በጥላቻ ሳይሆን ልክ በሰለጠነ ዓለም የሚኖሩ ሰዎች እንደሚያደርጉት በራስ የመተማመን እና የስነልቦና ዝግጅት እንዲኖረኝ በማሰብ ነው፡፡ አባቴ በጣም ልዩ አባት ነው፡፡ ለእኔ ለልጁ ያለው እውነተኛ ፍቅር ሁሌም እጅግ ይገርመኛል፡፡ ምግብ እንኳን ከእኔ ተነጥሎ መብላት አይወድም፡፡ በእርግጥ ማንም አባት ለልጁ ጥሩ ነው፡፡ የእኔ አባት ግን ለእኔም ለራሴ ይገርመኛል፡፡

‹‹ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ስጨርስ ኮምፒዩተር ቤት አስገባኝ፡፡ እኔ ግን በዚያን ሰዓት ተደብቄ ሙዚቃ እሰራ ነበር፡፡ ይህንን ሲሰማ ትምህርቴን አስቆመኝ፡፡ በተጨማሪ አስራ ሁለተኛ ክፍል እንደጨረስኩ ከአሁን በኋላ የቤት ኪራይ ትከፍላለህ ብሎኝ ነበር፡፡ እርግጥ ሲቀልድ ነው፡፡ ይህንንም ያለኝ በዛን ወቅት የምኖርበት ቤት የእኔ ቤት እንዳልሆነና ሌላ የራሴን ቤት መስራት እንዳስብኝ ስላለበ ነው፡፡ ‹በዚህ ዓለም የፈለከውን መሆን ትችላለህ› እያለ ዛሬ የዚህ አይነቱ ልብ እንዲኖረኝ አድርጎኛል፡፡ በዚህም ምክንያት ምንም ነገር ስመኝ ትልቁ ትልቁን ነው፡፡ ይህንንም ማድረግ

የምችልበት ልብ እንዲኖረኝ አባቴ ልባም አድርጎኛል›› ሲል ዝነኛው ቴዲ አፍሮ ተናግሯል፡፡

ቴዲ አፍሮ ዛሬ በጥንካሬ ተሞልቶ አሁን ካለበት የገዘፈ ስም እና የናረ ዝና ለመድረስ የበቃው የአባቱ የስነልቦና ጨዋታ ከፍተኛውን ሚና በመጫወቱ ነው፡፡ በእርግጥ ማንም አባት የልጁን ትልቅ ደረጃ መድረስ ይመኛል፡፡ ስኬታማነቱንም ማየት ይናፍቃል፡፡ የጋዜጠኛ ካሳሁን ግርማሞ ግን የተለየ ነው፡፡ ካሳሁን ጠንካራ ሰው ምርጥ አባትም ነበር፡፡ የሚፈራውና የሚያከብረው እግዚአብሔሩ ነፍሱን የቅዱሳን ቦታ በሆነችው መንግስተ ሰማያት ያኑርልን፡፡ መንግስተ ሰማያት የመልካም ሰዎች ናትና፡፡

ጋዜጠኛ ካሳሁን አባትነቱ ለቴዲ አፍሮ ብቻ አልነበረም፡፡ በሚኖርበት አካባቢ የሚኖሩ ህፃናትና ወጣቶችንም ልክ እንደ ልጁ አድርጎ የሚመክር የሁሉም አባትም ጭምር ነበር፡፡ አብረውት ስራ ገበታ ላይ ለተሰማሩት የሞያ አጋሮቹ ዕውቀቱን ሳይሰስት ያካፍላቸውና በሥራ-ነክ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ቀና ሃሳብና ምክርን ይለግሳቸው እንደነበር የስራ ባልደረቦቹ በፍቅር ያወሳሉ፡፡ በተሰማራበት የስራ ዘርፍ የተጣለበትን ሃላፊነት ከበቂ በላይ የሚወጣ፣ ደከመኝ ሰለቸኝ የማይል፣ ብርቱና ጠንካራ ሰው እንደነበረም ይመሰክራሉ፡፡

ሰዎች ጥሩ ደረጃ ደርሰው ማየት የሚናፍቅ፣ ልበ-ቅን ጭምር ነበር፡፡ ካሳሁን በስራ ሰዓት ስራ ነው፡፡ የእረፍት ሰዓቱን ሳይቀር በስራ ነበር የሚያሳልፈው፡፡ ሙያውን ይወደዋል፡፡ ስራውንም ያከብራል፡፡ በወቅቱ በሚሰራበት መስሪያ ቤት ውስጥ ካሉ ሰራተኞች በመልካም ምግባሩ በቁጥር አንድ የሚጠቀስ የሰራተኛ አንቀሳቃሽ ሞተር ነበር፡፡ ስራ ለመስራት ህሞቱን ያፈሰሰ ሰው የጋዜጠኛ ካሳሁንን የስራ ፍቅር ካየ የኋላ ኋላ ከስንፍናው ተላቆ ስራ ወዳድመሆኑ አይቀርም፡፡ አንድ የስራ ባልደረባው የሆነ ግለሰብ "በህይወቴ" ይላል፤ "በብዙ የስራ መስኮች ላይ ተሰማርቻለሁ፤ ከሚገባው በላይ የተደሰትኩት ግን ከካሳሁን ጋር በአንድ መስሪያ ቤት እሰራ በነበረ ወቅት ነው፡፡"





ጋዜጠኛ ካሳሁን በአንድ ወቅት ለስራ ጉዳይ ወደ ክፍለሃገር ለመሄድ ይነሳል፡፡ በጣም ከሚወደው ልጁ ከቴዲ አፍሮ ጋር በቀጣይ ህይወቱ እንደሚነጋገሩ አስቦ ሻንጣውን አዘጋጅቶ የልጁን ጉንጭ አገላብጦ ከሳመው በኋላ የፍቅር እንባ እየተናነቀው ወደ ጉዞው ያቀናል፡፡ ነገር ግን ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ካሳሁን ከሄደበት ክፍለ ሃገር ወደ መኖሪያ ቤቱ የተመለሰው ታሞ ነበር፡፡ የበሽታው አይነት ማጅራት ገትር እንደሆነ የህክምና ባለሞያዎች ነግረውታል፡፡ እናም በፖሊስ ሆስፒታል ውስጥ ህክምናውን እንዲከታተል ከተደረገ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ከሆስፒታሉ ወጣ፡፡ ካሳሁን በወቅቱ በሽታው ባይጸናበትም ከመስሪያ ቤቱ የዓመት እረፍት ወስዶ ነበርና ከህክምናው መልስ ቀጥታ ያመራው ወደ ቤቱ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበሽታው ስሜት እየፀናበት መጥቶ በህክምና እየተረዳ ሳለ በድንገት ህይወቱ አለፈች፡፡ ይሄኔ ለቴዲ አፍሮ ከሀዘንም የላቀ ሀዘን ከመከራም የበረታ መሪር መከራ ወደቀበት፡፡ ሳይታሰብ በድንገት ከዚህ ዓለም በሞት ያሸለበው አባቱ፣ ይመክረው የነበረው ምክር፣ አብሮ መብላት መጠጣቱ፣ ሽርሽርና አብሮ መጨዋወቱ፣ አዕምሮው ላይ እየተደቀነ በጥልቅ ሀዘን መታው፡፡ የአባቱን ሞት ለማመን ቢያስቸግረውም መፅናናትን መረጠ፡፡ ግን አልቻለም፡፡ አይኖቹ እንባ ከማፍሰስ፣ ልቡም በክፉ ሀዘን ከመኮማተር አላመለጡም፡፡ በዚህ መሃል አንድ ነገር ትዝ አለው፡፡ "ባለው መጽናናት ነው፡፡" ይህ አባባል የአባቱ ነበር፡፡

"በትንሽ ነገር ካልተደሰትክ በብዙ ነገር አትረካም" በማለት ደጋግሞ ይመክረው የነበረው ውድ አባቱ ጋዜጠኛ ካሳሁን ግርማሞ በሞት ስለተለየው በሃዘን የተዋጠው ልጁ ቴዲ አፍሮ ብቻ ሳይሆን ጓደኞቹና የሚያውቁት ሁሉ ነበሩ፡፡ እንባውን ያላፈሰሰ እህ ብሎ ከአንጀቱ ያላለቀሰ አንድም አልነበረም፡፡

በእርግጥ ካሳሁን ግርማሞ የሞተው በስጋ ነው፡፡ በነፍሱማ ህያው ነው፡፡ ልጁ ቴዲ አፍሮ በተገኘበትና ባለፈበት መንገድ ሁሉ አባቱ ካሳሁን አለ፡፡ ስማቸው አብሮ ይነሳል፡፡ ካሳሁን በአካል ሞቶ

የሚወደውን ልጁን አሁን ከደረሰበት የገነነ ቦታ ደርሶ ለማየት ባይታደልም ጅማሬውን ሰምቷል። በምስሉ የተቀነባበረውን የክሲፕ ዘፈኑንም ለማየት ችሏል። "እንኳን ደስ አለህ" የሚል የምስራች መልዕክቶችንም ከወዳጅ ዘመዶቹ ደርሰውታል።

ጋዜጠኛ ካሳሁን በህይወት ዘመኑ ስራውን አክብሮ በሰዓቱ እስራው ገበታ ላይ የሚገኝ፣ ለስራው ልዩ ፍቅር የነበረው፣ ለብዙዎች የስራ ክቡርነትን ምሳሌ ሆኖ ያስተማረ ልዩ ሞዴል ነበር። ልጁም አደራውን አክብሮ የአባቱን በትር ተቀብሏል።

ለቴዲ አፍሮ አባቱ ከምንም በላይ ባለውለታው ነው። በመልካም ምክር ገንብቶታል። በማይደለዝና ከልብ በማይጠፋ እውነተኛ ፍቅር አሳድጎታል።

ቴዲም በአባቱ ሞት የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን እስከአሁኗ ሰዓት ከህሊናው አልተሻረም። ለዚህም ነው «ሙዚቃ ህይወቴ» በተሰኘው ዜማው አባቱን እንዲህ ሲል የዘከረው

*በሟች ማዘን የለም*

*ባለው መፅናናት ነው*

*ብለህ እንዳስተማርከኝ*

*በአንተው ምክር ሄጄ*

*በአንተው አስጨከንከኝ*





# ጀግና ተወለደ!

በዚያ አንድ ፍሬ ልጅ - በዚያ ብላቴና

በአቡጊዳ ሀሌታ - ሲሰማ የምሥራች ዜና

እልል አለች ኢትዮጵያ እጆቿን ዘርግታ

የትንቢት ቃሉን ሲፈፀም አይታ ተደስታ።

በዚያ በጥበብ መጀመሪያ በአቡጊዳ ቀዳማይ ፊደል

የጥበብ ትንሳኤ የምስራች አዋጅ ሲነገር

ፌሽታ ሆነ በተስፋይቱ ምድር በዚች ውዷ አገር።

በሙያው ሀገሩን ያገለገለ

ህያው ሥራ ሰርቶ በክብር ያለፈ

ያ ደጉ ጥበበኛው አባት

አሁን ደግሞ ለቅድስቷ ሀገር ለዚች ለሚወዳት

ልጁን ምትኩን ሰጥቶ እንደ ስሙ ዳግም ካሳ ሆናት።

ያቺ ዕድለኛ ወላጅ እናቱማ

የትንቢት ቃሉን ሲፈፀም ያየች ቁማ

ትጠራዋለች አሉ "ቴዲዬ ማዕረጌ" ብላ

የሁላችን ማዕረግ ለማለት ፈልጋ።

# 3

# ቴዲና የትምህርት ቤት ቆይታው

## *"ትልቅ ነገር እንድታገኝ ትልቅ ነገር ተመኝ"*

ለአንድ ሀገር እድገት የተማረ ህይል ወሣኝ ሚና አለው። የለው ልጅ በርትቶ ከተማረ የብዙ ነገሮች ተጠቃሚ የመሆን እድሉ የሰፋ ነው። ዝነኛው ድምፃዊ ወጣቱ የዘፈን ብላቴና ቴዲ አፍሮ እንደ ማንም ኢትዮጵያዊ ህፃን ፊደል ለመቁጠር መጀመሪያ ያመራው ወደ መዋዕለ ህፃናት ነው። ቴዲ ከዚያች ዕድሜው አንስቶ አዕምሮውን በትምህርት ለማበልጸግ የነበረው ፍላጎት ቀላል ግምት የሚሰጠው አልነበረም።

ወላጅ አባቱ ጋዜጠኛ ካሳሁን ግርማሞ ከስራ መልስ በተደጋጋሚ ፊደልን ያስቆጥረው እንደነበርና የአባቱም ጥረትና ክትትል በርትቶ እንዲማር ትልቅ ሚና እንደተጫወተለት ቴዲ ይናገራል።

ቴዲ ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት አምርቶ 12ኛ ክፍልን እስካጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አንድም ጊዜ ወድቆ አያውቅም። ነፍስ





እያወቀ እና ክፉና ደጉን እየለየ ሲሄድ ለትምህርት ያለው ፍላጎትና ጉጉትም ከእድሜው ጋር አብሮ እያደገ መጥቶ ሁሌ በትምህርት ገበታው የሚገኝ ብርቱ ተማሪ ለመሆን በቃ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በቤተልሄም የተከታተለ ሲሆን ከመምህራኖቹ ጋር መልካምና ጤነኛ ግንኙነት ያለው፣ ያልገባውን በመጠየቅ የሚረዳ፣ በትምህርት የሚፈለግበትን ሃላፊነት የተወጣ ጎበዝ ተማሪ ነበር።

ቴዲ በጣም የሚወደው የትምህርት ዓይነት ሳይንስ እና እንግሊዘኛ እንደነበር አብረውት ከተማሩ ጓደኞቹ ማወቅ ይቻላል። በሚማርበት ክፍል ውስጥ ረብሻን የማይወድ፤ ከጓደኞቹም ጋር ፍቅር የነበረው ተወዳጅ ሰው ነው። በእረፍት ጊዜው ለእግር ኳስ ጨዋታ ልዩ ፍቅር ነበረው። የተሰጠውን የቤት ስራ አጠናቆ የሚመጣ ለተማሪዎች ጠመኔን ይዞ ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ የሚያስረዳ እንደነበረ የሳይንስ መምህሩ ዛሬ ድረስ ይመሰክሩለታል። ቴዲ በተለይ ትምህርቱን የሚከታተለው በተመስጦ እንደነበረ አክለው ይገልፃሉ።

ከሌሎች ተማሪዎች የሚለይበት ብዙ ነገሮችን መጥቀስ ቢቻልም አንዱና ዋነኛው ግን ስርአቱና የትምህርት ፍላጎቱ ነው ይላሉ። ቴዲ እድሜው እየጨመረና የትምህርት ደረጃውም ከፍ እያለ በሄደ ቁጥር የአስተሳሰብ እድማሱና አስተዋይነቱም አብሮ ያድግ ነበር የሚለው የትምህርት ቤት ጓደኛው የቴዲ ሁኔታ ገና ልጅ ሳለ ነበር የሚገርመኝ ይላል። ዛሬ ካለበት ቦታ መድረሱ አይገርመኝም። ምክንያቱም ቀድሜ የነበረውን ብቃቱን፣ አስተዋይነቱንና ልበ ሙሉነቱን አስተውዬ ስለነበረ ነው። ስምንተኛ ክፍልን ጥሩ ውጤት አምጥቶ ማለፉንም አውቃለሁ። ዝቅተኛ ውጤት አምጥተው ወደ ቀጣይ ክፍል መዘዋወር ባልቻሉ ተማሪዎች ሲያዝን አይቼው ገርሞኝም ነበር። ለካስ ፍቅር የገባው ሩህሩህ ልጅ ነበር" ይላል።

ቴዲ በተፈጥሮ የተሰገሰው እምቅ የጥበብ ሀብት ያን ጊዜ ነው መጠቀምና ከትምህርቱ ጎን ለጎን ማስኬድ የጀመረው። ይሄኔ ነበር የበለጠ የፈጠራው ውጤቱን በየጊዜው ግጥም እየፃፈ ለማሳደግ የበቃው። ትምህርቱ ላይ ያሳይ የነበረው ታታሪነትና ጉብዝና እንዳለ

ሆኖ አንዳንድ ቀን ማርፈድ እና መቅረት የጀመረው በዚህን ጊዜ ነው። የዚህ ዋነኛ ምስጢር ደግሞ ከተለያዩ የሙዚቃ ባንዶች ጋር ማዘውተር ስለጀመረ ነበር። ትምህርቱን በማይጋፋ መልኩ ሙዚቃን የበለጠ አጎልብቶ ከት/ቤት መልስ የረፈደበት እስኪመስለው ወደ ሙዚቃ ጓደኞቹ ይኮበልላል።

ምክንያቱም ሙዚቃ ለቴዲ እውነት ነች። መናገር መተንፈስ ማስረዳት የሚፈልገውን ሁሉ በሙዚቃ ውስጥ ማስተላለፍ እንደሚቻል ስለገባው ነው። ጊዜ አለፈና ቴዲ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ማገባደጃ ላይ የመጀመሪያ አልበሙን መስራት ጀመረ።

ቴዲ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በሚከታተልበት ጊዜ እንደ በፊቱ ከጎበዝና ከጠንካራ ተማሪዎች ጋር የሚወዳደር ነበር። ቴዲ ግን የሁልጊዜው ሀሳቡ ሙዚቃ ሆነ። የወደፊት ህልሙን በልጅ አድሜው አልሞ መልካሟን ህይወቱን ተያያዘ። ቴዲ በትምህርት ብዙም እንክን አልገጠመውም። ምክንያቱም የሚጠበቅበት ሀላፊነት የገባው ስለሆነ። ሙዚቃ ግን የሰዎችን ፊት አሳይቶታል።





# ክፍል ሁለት

# ቴዲ አፍሮን ለታላቅነት ያበቁት ዓበይት ምክንያቶች

4

## ቴዲ፣ ሥር ነቀል ለውጥ ያመጣ አብዮተኛ

የብዙዎቹን የሙዚቃ አፍቃሪያን ልብ ያማለለና በሙዚቃ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አይነተኛ ለውጥ ያመጣ እንደ ቴዲ አፍሮ ከቶ ማንም የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። በመላው ኢትዮጵያውያን ዘንድ መልካም ስሙና ዝናው የናኘ፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ፣ ከዳር እስከ ዳር የሰው ልጅ ፍቅር የተላበሰ፤ በሙዚቃው ህይወት ውስጥ የማይሞትን ነብስ የዘራ፤ የለውጥ ሀዋርያ ነው ቴዲ አፍሮ!!

አቡጊዳ የተሰኘው አልበም እንደወጣ አብዛኛው ድምፃዊ ቆም

ብሎ ራሱን እንዲመረምርና ስራውን እንዲፈትሽ አድርጎታል። ስለሆነም በሚገመት እድሜው የማይገመት ህያው ስራን የሰራ ጠንካራ አርቲስት ነው። በቀደሙት ዘመናት የነበሩት የህገራችን ዘፋኞች ያልደፈሩትንና ያልዳሰሱትን የአዘፋፈን ስልት ይዞ በመቅረብ ለመጀመርያ ጊዜ በሙዚቃ ህይወት ውስጥ የዘፈንን አብዮት ያፈነዳ አብዮተኛ ነው።

የቴዲ አፍሮ ዘፈኖች ሁሉን አቀፍ እንጂ በአንድ ህሳብ ዙርያ ብቻ የሚሽከረከሩ አይደሉም። ስለ ትላልቅ አንጋፋ ሰዎች አውስቷል፣ ስለ ህገር ፍቅርና ስለባንዲራ ክብር አዚሟል፣ ስለ ሃይማኖትና ፖለቲካ መቻቻል ሰብኳል፣ የአፍሪካውያን ቀንደኛ ችግር ስለሆነው ስደት አቀንቅኗል፣ ስለፍቅርም ሃያልነት ጥልቀትና ብስለት ባለው መልኩ ዘምሯል. . . በአጠቃላይ ሁሉንም የህይወት ዘርፍ የሚዳስስ ብልህና ጥበበኛ አርቲስት መሆኑን አስመስክሯል።

በዚህም የተነሳ የቴዲ ዘፈኖች ከአፍሪካም አልፈው በተለያዩ የአውሮፓ ህገሮች በከፍተኛ ደረጃ ተደማጭነትንና ተቀባይነትን አግኝተዋል። የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝብ ይቅርና ለቋንቋው ባዕድ የሆኑ የውጭ ዜጎች እንኳን በቴዲ የአዘፋፈን ስልትና የድምጽ ቅላፄ እጅግ ከመማረካቸው የተነሳ ተዘውታሪ በሆነ መልኩ በዘፈኖቹ ሲዝናኑ ማየት የተለመደ ሆኗል።

ቀናት ያልፋሉ፣ ዓመታት ያረጃሉ፣ አዲስ ነገር የነበረው በሌላ አዲስ ነገር ይተካል። ጨረቃ በፀሀይ፣ ክረምትም በበጋ፣ ጨለማም በብርሃን፣ ሞትም በህይወት፣ እየተፈራረቁ ለዘመናት ይኖራሉ። የቴዲ አፍሮ ሥራዎች ግን ምንም ሁኔታ ሳይገድባቸው ድንበርና ኬላ ሳይወስናቸው ጥልቁን ባህርና ሰፊውን የሰማይ አድማስ አቋርጠው ለዝንተ-ዓለም ይጓዛሉ። ነብስ ባለው ፍጡር ዘንድ እንደተወደዱ ሁሌም ህያው ሆነው ለዘላለም ይኖራሉ።

ቴዲ አፍሮ በሚያቀነቅነው በእያንዳንዱ ዘፈኑ ውስጥ በአንድ ስንኝ ብዙ መልዕክትን ማስተላለፍ የቻለ ድንቅ አርቲስት ነው። ከዚህ





ቀደምም ሆነ በዚህ ዘመን የሚቀመሩ ዜማዎችና የሚደረሱ የዘፈን ግጥሞች ከቴዲ አፍሮ የአዘፋፈን ስልት ጋር አንዳች የሚያመሳስል ነገር የላቸውም ማለት ይቻላል። የልዩነታቸውም መጠን የሰማይና የምድር ያክል ነው ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል። ቴዲ አፍሮ ሁል ጊዜ አዲስ ነገርን በመፍጠር ድንቅ ችሎታው የሚታወቅ እፁብ ድንቅ አርቲስት ነው። በማንኛውም ጊዜና ቦታ ስለ ዘፈን ከተወሳ፤ በየአንዳንዱ ሰው ህሊና ውስጥ የቴዲ አፍሮ የገዘፈ ስም በግንባር ቀደምነት መነሳቱ አይቀሬ ነው። አርቲስቱ ለየት ባሉ ስራዎቹ የብቃቱን ምጥቀት ያሳየ ጠንካራና አስተዋይ አርቲስት ነው።

ተወዳጅና ዝነኛው ድምፃዊ ደረጃውን የጠበቀና የማንንም ጆሮ የሚማርክ ዜማና ግጥም በቀን ተቀን በተከታታይ የመስራት ችሎታ እንዳለው የብዙኀኑ ኢትዮጵያዊ ልብ ያውቃል። በተለይ ዜማን ለመቀመርና ግጥምን ለመፃፍ ቦታና ጊዜ አይመርጥም። መኪና እያሽከረከረ መፃፍ ከፈለገ መኪናውን ተገቢ ቦታ አቁሞ ይፅፋል። በጨዋታ መሀል ሳይቀር ይፅፋል። በፈለገው ጊዜ የመፃፍ ችሎታ ያለው ታላቅ ሰው ነው።

ቴዲ አፍሮ ግጥምን ከሽኖ ፅፎ ዜማን ቀምሮ የሚያገኘው እርካታ ወደር የለውም። በሚፈጥራቸው ምርጥ ስራዎቹ የሚያገኘው ደስታ ‹‹ሀሴቱ ይገለኛል ብል ይሻለኛል›› በማለት እሱ ራሱ ይገልፃል። በወርቃማ ስራዎቹ እንባውን ያፈሳል። ወይም ሌሊቱን በሙሉ በደስታ ፈጣሪውን ሲያመሰግን ያድራል። በተለይ ‹‹አሳምን አለና›› ‹‹ሼህ ማንደፈር›› በአንድ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ዜማን ሰርቶ ግጥሙን ፅፎ ባገኘው ወደር የለሽ ደስታ የቀመረውን ዜማ እየሰማ እስከማንባት ደርሷል።

ቴዲ አፍሮ ዜማም ሆነ ግጥም ሲቀምር ነፍሱን ከልቡ ጋር አስማምቶ ነው። በዚህም በተቸረው ጥበባዊ ክህሎቱ የህገራችን እንቁ ነው። ከፈጣሪው የተለገሰው የጥበብ ችሎታ ብቸኛ የህገራችን ምትክ የለሽ አቀንቃኝ በመሆን የአንደኝነትን አክሲል ደፍቷል።

"ልባችንን ካዳመጥነው የራሱ የሆነ ቋንቋ አለው። ስለሆነም አንድን ነገር ሰርተን ለህዝብ ከማቅረባችን በፊት መጀመሪያ ከልባችንና ከነፍሳችን ጋር እንስማማ" ሲል ይህ ብርቅዬ አርቲስት ብዙዎችን ይመክራል። ቴዲ አፍሮ ተሰምተው የማይሰለቹ ዜማዎችና ተደጋግመው በተደመጡ ቁጥር ሁሌ አዲስ ቁም ነገር የማይታጣባቸው በሳል ግጥሞቹ ተፈጥሮ ካደለችው ውብ ድምፅ ጋር አቀናጅቶ በግጥሙና አምላክ በቸረው ድምፁ ከግምት ባለፈ መልኩ ለሀገሩ ኢትዮጵያ ትልቅ ገፀ በረከትን አበርክቷል። በሁሉም ዘፈኖቹ ብዙ ነገርን አስተምሮናል። አንድነትን፣ መቻቻልን፣ ፍቅርን፣ .... ወዘተ ነግሮናል። በስሜትና በማስተዋል ስለሚዘፍን በየአንዳንዱ የዘፈን እንቅስቃሴው የለውን ልጅ የልብ ትርታ ያዳምጣል። "ፈጣሪ በሰገለኝ የጥበብ ችሎታ ወገኔን ማገልገል እፈልጋለሁ!!" ብሎ የሚያምን ታላቅና ልበ ብሩህ አርቲስት ነው። ታይተው ለሚጠፉ ቅፅበታዊ ነገሮች ሳይሆን፣ ለጥልቅ ጉዳዮች ትኩረትን የሚሰጥ፣ ቀና ሀሳብ ያለው፣ የፈጠራ ችሎታውን ለማዳበር አዘውትሮ ማንበብ የሚወድ፣ በተለይም የአምላክ ቃል ለሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ትልቅ ትኩረት ያለው፣ ለገንዘብ ሲል ሙዚቃን የማይሰራ፣ የጥበብን እድገት የሚመኝ፣ የሀገራችን ብርቅዬ አርቲስት ቢኖር በቁጥር አንድ ተጠቃሹ ቴዲ አፍሮ ነው።

ከዚህም አልፎ ቴዲ አፍሮ ወደ ሙዚቃ አለም ከተቀላቀለበት ጊዜ አንስቶ ብዙ የሀገራችን ወጣቶች እሱን እንደ ሞዴል በመከተል የጥበብ ህይወትን እየተቋደሱ ይገኛሉ። ተወዳጁ ድምጻዊ ቴዲ አፍሮ ዛሬ ካለበት ከፍታ የመድረሉ ዋነኛው መሰረት ለሙያው ለፊ ሰዓት በመስጠቱና ልቆ ለመውጣት ካደረገው እልህ አስጨራሽ ከፍተኛ ጥረት የተነሳ ነው። በሚሰራው ስራ ላይ ሁሉ ከትንሽ እስከ ትልቅ፣ ዘር ፆታና ሃይማኖት ሳይለይ ማንም ሰው የሚሰጠውን አስተያየት በቅንነትና በአክብሮት በመቀበሉ ለስራው ማደግ ከፍተኛ እገዛ አድርጎለታል። የጊዜን ክቡርነት ጠንቅቆ የተረዳ አንድም ሴኮንድ ቢሆን ያለ አግባብ የማይባክንበት፣ የስራን ክቡርነት ያወቀ፣ ታላቅ አርቲስት ነው።





ኢትዮጵያዊ ስብዕና ያለው፣ የሀገሩን ወግና ባህል ለማንጸባረቅ የሚተጋ፣ ለበጎ ነገር የተፈጠረ፣ በሙያውና በስራው ሁሉ የራሱንና የሀገሩን ማንነት ቅልብጭ አድርጎ የሚያሳይ፣ ለወገኑና ለሶስቱ ቀለማት ልዩ ልባዊ ፍቅር ያለው፣ የአንደበቱ የፍሬ ቃል የሚጣፍጠው፣ የሀገራችን ሙዚቃ ለዘመናት ካንቀላፋበት የቀሰቀሰ፣ የሙዚቃ መሲህ፣ የኪነ ጥበብ አርበኛ፣ የሀገራችን የሙዚቃ ባለቅኔ የቅዱስ ያሬድን የዜማ ቅኝት ያልረሳ፣ ሕይወቱን ሁሌም ለጥሩ ነገር የሚሰዋ፣ የሙዚቃን ክቡርነት በሚያከብረው ሙያው ያስመሰከረ፣ በሚደረድረው የግጥም ስንኝ፣ በሚቀምረው ረቂቅ ዜማ፣ በሚያቀናብረው አሬንጅመንት ለጥበብ ሥራ የተፈጠረ የዘመናችን ብቸኛ ታላቅ ሰው ነው - ቴዲ አፍሮ።

*አይንሽ ጎላ ጎላ የትንባሆ ፍሬ*

*አንቺን የወሰዱ መልካም ሸማግሌ*

በሚሉና በመሳሰሉ ሀራምባና ቆቦ የግጥም ስንኞች ዘፈን ይዘፈን የነበረበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። የሚገርመው ደግሞ አሁንም ቢሆን ከዚህ ያልተሻሉ ጆሮ ጠላዥ ዜማና ግጥሞችን እየሰማን መሆናችን ነው። ልብ በሉ በዚህ ውልክፍክፍና ያልበሰሉ ሥራዎች ተጥለቅልቀን የዘፈን ጥማት በናፈቀን ወቅት ነው ይህ ብርቅዬ ጀግናችን ቴዲ አፍሮ ምትሀታዊ በሆነው የግጥም አፃፃፍ ስልቱና በማይጠገቡ ዜማዎቹ አድማጮችን ለማስደሰትና የጋዜጠኞችን ብዕር ለማማዘዝ የበቃው።

በዚህ መሰል ድንቅ ሥራው የአርቲስቶች ንጉስ ለመሰኘት በቅቷል። ዘመን አይሽሬ ግጥሞቹ በዜማ ጣፍጠው ለአድማጭ ጆሮ ሲደርሱ ቀልብ የሚስብና ልዩ ማራኪነት አላቸው። ቴዲ አፍሮ በፈጠራ ስራዎቹ የልጅ አዋቂ፣ የትልቅም ትልቅ የሚሰኝ ነው!! አብዛኛዎቹ ስራዎቹ ፍልስፍናዊ ይዘት ያላቸው ናቸው። ከግጥሞቹ መሃል ለአብነት አንድ ሁለቱን ብንጠቅስ

*ተማፀንኪት ፀናሁ ደጅ*
*ባስለምናት ባማላጅ*
*ይቅር በቃ እያለችኝ*
*አለሁ ብላ ተለየችኝ*

(ተማፀንኪት)

................

*አያጣውምና ፍቅርን እንቅፋት*
*ከፍቶኝ ብቀየምሽ ባንድ ቀን ጥፋት*
*መልሼ ልፀፀት እራሴን ልውቀሰው*
*እንዴት አሳልፌ አንቺን ልማሽ ለሰው*

(ለማን ልማሽ)

................

*ዘጽአት ለኢትዮጵያ ወደተስፋ ጉዞ*
*ባህሩን የሚያሻግር አንድ ሙሴን ይዞ*
*ቅርብ ነው አይርቅም የኢትዮጵያ ትንሳኤ*
*በአንድነት ከገባን የፍቅር ሱባኤ*

(ያስተሰርያል)

................

በሙዚቃ ህይወታቸውና በሙያቸው የዜግነት ሀላፊነታቸውን ከተወጡና እየተወጡ ካሉ ኢትዮጵያውያን መሀል በቁጥር አንድ ጀግና ማን እንደሆነ ቢጠየቅ ሁሉም ከሊቅ እስከ ደቂቅ በአንድ ድምፅ





‹‹ቴዲ አፍሮ ነዋ!›› ብለው ምስክርነታቸውን እንደሚሰጡ ቅንጣት ታክል ጥርጥር የለውም። ቴዲ አፍሮ ቀምሮ ለአድማጭ ካበረከታቸው የሙዚቃ ታምራት ውስጥ መቼም ቢሆን ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሀሊና ሊጠፋ የማይችለው ያ በሃያ አራት ሰዓት አጭር ጊዜ ውስጥ ግጥምን ደርድሮ፣ ዜማን ቀምሮ፣ ለአንድ ሙዚቃ የሚያስፈልጉትን ግብአቶች አሟልቶ፣ አሳምሮና ከሽኖ ያቀረበውና ህዝብን በደስታ እንባ ያራጨውን ‹‹ቀነኒ ኬኛ›› የተሰኘ ምርጥ ሥራው በቁጥር አንድ የህዝብ ጀግንነቱ የሚጠቀስ ነው። ይህ ዜማ ለህዝብ በተለቀቀበት ወቅት አትሌቶቻችን ለሀገራቸው ካስገኙት ሜዳልያ ጋር ተደምሮ ለህዝብ እጥፍ ድርብ ሀሴት ፈጥሮለት ነበር።

ለጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ክብር ሲባል የተዜመው ይህ የቴዲ አፍሮ ምርጥ የፈጠራ ስራ፣ ለማንም ቢሆን በአንድ ሌሊት የተጠናቀቀ ሥራ ነው ብሎ ለማመን እጅግ ይከብዳል። ግን ቴዲ አደረገው!

የቴዲ አፍሮ የፈጠራ ብቃት ጎልቶ የታየው በዚህች ነጠላ ዜማ ብቻ አይደለም። ሌሎች ያበረከታቸውን ገድለኛ ስራዎቹ ያዳመጡ ብዙዎቹ "ስለአርቲስቱ የምንናገርበት ቃል አጥሮናል" ሲሉ ተደምጠዋል።

በሚሰራቸው ስራዎቹ ሁሉ እምነት ያለው፣ ለሀገሩና ለወገኑ ካለው ጥልቅ ፍቅር፣ ለሶስቱ ቀለማት ባንዲራው የሚሞት፣ መቼም ከህዝቡ አዕምሮ ሊፋቅ የማይችል የብዙዎቹ ምርጫና ብልጫ ያለው አርቲስት ነው የሚሉ ብዙዎች ናቸው።

ሌላው ቀርቶ በሥራው የተቀዳጀው የዝና ከፍታ ገና የሚያንሰው፣ ከተባለው በላይ ብዙ ሊባልለት የሚገባ፣ የምርጦች ምርጥ ነው በማለት አድናቂዎቹ ይመሰክሩለታል። ለመኖርያነት የውጭ ሀገራትን ምቹ ሕይወት ያልመረጠ፣ በሀገሩና በአበሻነቱ የሚኮራ፣ በጥቁር አፈሩ የሚደሰት እንደ ቴዲ አፍሮ ያለ ከቶም የለም በማለት ‹‹ቴዲ አፍሮ የማይጠገብ የነሀሴ ጸሀይና የበረሃ ጥላ ነው›› ሲሉ ለእሱ ያላቸው ልዩ ፍቅር በአጭሩ ይገልጻሉ።

ቴዲ ለህዝብ ባበረከታቸው የሙዚቃ ስራዎቹ እሱነቱን ከማስመስከሩ በላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አድናቂዎቹ ሙዚቃን በሚገባ ያወቅናት በቴዲ አፍሮ ነው በማለት የቴዲንና የሙዚቃን ስር የሰደደ ጥምረት ይገልፃሉ፡፡

ተወዳጁ ድምጻዊ ቴዲ አፍሮ ዛሬ ካለበት ከፍታ የመድረሱ ዋነኛው መሰረት ለሙያው ሰፊ ሰዓት በመስጠቱና ልቆ ለመውጣት ካደረገው እልህ አስጨራሽ ከፍተኛ ጥረት የተነሳ ነው፡፡ በሚሰራው ስራ ላይ ሁሉ ከትንሽ እስከ ትልቅ፣ ዘር ፆታና ሃይማኖት ሳይለይ ማንም ሰው የሚሰጠውን አስተያየት በቅንነትና በአክብሮት በመቀበሉ ለስራው ማደግ ከፍተኛ እገዛ አድርጎለታል፡፡





## ማን እንደ ቴዲ አፍሮ !!!

ጥበብ በጥበብ ላይ በቅኔ አሸብርቆ
ያዜመዋል ቴዲ እውነትን ሰንቆ
አይበግረው የምቀኛ ወሬ
ሙያውን ወዶ ብሎ ክብሬ
ጊዜን ይሰጣል ለሙዚቃ
አሉባልታን ነብሱ ንቃ
ሙዚቃን የተጠበበላት እንዲህ አሳምሮ
አይተንም አናውቅ ማን እንደ ቴዲ አፍሮ
በሙዚቃ ህይወት ማነው የለውጥ ሀዋርያ?
ቴዲ አይደለም ወይ ትናገር ኢትዮጵያ
ቢነገር ቢወራ ቢጻፍ ቢተረክ
ክቶም አላየንም በቴዲ አፍሮ ልክ
በተሰጠው ፀጋ ዜማውን ቀምሮ
እውነቱ ከወጣ ማን እንደ ቴዲ አፍሮ
ዛሬም ሁሌም ለዝንተ ዓለም ትነግሳለህ
አይነካህም ክፉ የአምላክ ፍቅር አለህ
ግና ስም አነሰው ለመጠሪያ
ለይሚለት ኢትዮጵያ
አዋቂ ነው ብልህ ሰው
ለክብሩ መጠሪያ አነሰው!

**5**

# ቴዲ ለሀገሩ ያለው ስሜት

***"ሀገር በምንም ነገር የማትለወጥና የማትሸጥ***

***ውድ የፈጣሪ ስጦታ ናት።"***

**ቴዲ አፍሮ**

ሀገር ማለት ወንዙ፣ ተራራው፣ አራዊቱና የቆመው ድንጋይ ሳይሆን ህዝቡ ነው። ‹‹ሀገርን መውደድ በአፍ ሳይሆን በተግባር ነው›› የሚለው ቴዲ አፍሮ ስለ ሀገሩ ሲናገር እውስጡ ባለ እውነተኛ ፍቅር ነው። ቴዲ ሀገሩን የሚወዳት ከልቡ ጠብ ባለ ጥልቅ ፍቅር እንጂ የይምሰል አፋዊ አይደለም። ለዚህም አንዱና ዋንኛው ምስክር የሚሆነን ለማይ ጠቀስ የሆነ የተከበረ ስምና ዝና እያለው ያለምንም ማካበድ በሀገሩ ለመኖር መምረጡ እንደማንም ሰው የውጭውን አለም ለመኖሪያነት አለመመኘቱ ነው። ለሀገሩ ያለውን ሥር የሰደደ ፍቅር ከመናገር አልፎ ኑሮውን በሀገሩ መስርቶ በተግባር ለማሳየት የበቃ ሀገር ወዳድ ጀግና ነው። ቴዲ የሙዚቃ ስራውን በባዕድ ሀገር





ለሚገኙ ወገኖቹ በሚያቀርብበት ጊዜ የሀገሩን ባንዲራ ከፍ አድርጎ ያላውለበለበበት፣ ሀገሬ ብሎ ያላቀነቀነበት መድረክ ከቶ የለም።

አበባ ጊዜውን ጠብቆ ጠውልጎ ይረግፋል፣ ባለስልጣናትም ከስልጣናቸው ይሻራሉ። ሰውም ያረጃል። ብርሃንና ሌሊትም ሰዓታቸውን ጠብቀው ይፈራረቃሉ። ኢትዮጵያ ግን ዛሬም ነገም ለዘላለም ኢትዮጵያ ነች።

ዝነኛውና ተወዳጁ ቴዲ አፍሮ ለሀገሩ ያለው ፍቅር ምን ጊዜም የሚነጥፍ አይደለም። ስለ ሀገሩ ኢትዮጵያ ሀላፊነት ከተጣለባቸው ባልተናነሰ መልኩ ይጨነቃል። ነጋ ጠባ የሀገሩን ሰላም ውሎ ማደር ይመኛል።

ቴዲ አፍሮ በችካጎ ከተማ በስደት ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ በአይነቱ ለየት ያለ የሙዚቃ ኮንሰርት ባዘጋጀበት ወቅት ስለሀገሩ እንዲህ ሲል አዚሞ ነበር።

*ሁሌ አጎንብሼ ለነጭ አለቃ*
*ነገ ዛሬ ስል ስንቄ ሳይበቃ*
*ምን ይገዤ ልግባ ስል ወደሃገሬ*
*አልመልስ አለኝ ያወጣን እግሬ*

በታላቋ ችካጎ ከተማ እልህና ቁጭት በተሞላበት የአዘፋፈን ስልቱ ሲያዜመው ከኮንሰርቱ ታዳሚዎች እንባውን ያላፈሰሰ፣ አፉን ከፍቶ በናፍቆት ያልጮኸ አንድም እንኳን አልነበረም። ይህ ሁሉ ለሀገር ካለው ጥልቅ ፍቅር የመነጨ ነበር። ቴዲ አፍሮ በማንኛውም ሰዓትና ጊዜ ስለሀገሩ ሁሌም ሲናገር ይሰማል። ስለሀገሩ አውርቶ አይጠግብም።

በሀገሩ ላይ ቁርጠኛ አቋም ያለው፣ የሀገሩን መልካም ትንሳኤ ለዘላለም የሚናፍቅ፣ አስደናቂ አርቲስት ነው። ቴዲ ስለ ሃገሩ የወደፊት ትንሳኤ በራሱ አንደበት እንዲህ ብሏል፡- "ስለ ሃገሬ መልካም ትንሳኤ ይታየኛል። ቀኑ ቢረዝምም አይዘገይም። ሁሉም ነገር ቀኑ ሲደርስ ተፈጽሞ እናየዋለን።"

የቴዲ አፍሮ ምኞት በሙዚቃ ህይወት ዝናና ክብሩ አሁን ከደረሰበት ጣራ በላይ ከፍ ብሎ እንዲጠራ ማስቻል ብቻ ሳይሆን በሀገሩ ያለውን ሁለንተናዊ ችግር በአስተማማኝ ሁኔታ ተቀርፎ የሚወዳትን ሀገሩንና ወገኑን ከመከራ ችግር ተላቀው ህዝቦቿም እጃቸውን ወደ ፈጣሪያቸው አንስተው ሲያመሰግኑ ማየት ጭምር ነው።

"ሀገር በምንም ነገር የማትለወጥና የማትሸጥ ውድ የፈጣሪ ስጦታ ናት። በተለይ ኢትዮጵያውያን በሰላም ወጥተን በሰላም የመግባታችን ዋነኛ ምስጢር ሀገራችን ሰላም ስትሆን ብቻ ነው" የሚለው ቴዲ አፍሮ በስራ ምክንያት ከሀገሩ በወጣ ቁጥር ጥልቅ ሀዘን እንደሚሰማው የቅርብ ወዳጆቹ ይመሰክራሉ።

አብዛኛው ሰው በስራ ምክንያት የተሻለ ኑሮ ፍለጋ እና በተለያዩ ጉዳዮች ከሀገሩ ወጥቶ በዛው ለመቅረት ስለቱን ያበዛል። ይህ ሁሉ ደግሞ የሚመኘውን ነገርና የሚያልመውን ስኬት ካለማግኘቱ የተነሳ ነው። ለቴዲ ግን ይህ ሁሉ ከንቱ ነው። "ከአውሮፓ ምርጥ ጣፋጭ ምግብ ይልቅ የሀገሬን ሽሮ እመርጣለሁ" ባይ ነው።

በምንወዳት ሀገራችን ተንሰራፍቶ ያለው ችግር ሁሉ ተቀርፎ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ከያሉበት ተሰብስበው የደስታን ችቦ የምንለኩስበት ጊዜ ሩቅ አይደለምና ላንድነትና ለለውጥ እንትጋ" ይላል። የቴዲ አፍሮን ሀገር ወዳድነት ከእውነተኛ ልብ የመነጨ፣ በጥቁርነቱ የሚኮራ፣ የማንነት ጥያቄ የሌለበት፣ ከኢትዮጵያ ምድር በመፈጠሩ የሚደሰት፣ በተግባራዊ ስራው ለብዙሀኑ ልዩ ሞዴል





መሆን የቻለ ነው።

"ኢትዮጵያን የሚወድ እግዚአብሔር ይወደዋል" የሚለው ቴዲ አፍሮ ለሀገሩና ለወገኑ ያለው እውነተኛ ፍቅር ወደር የማይገኝለትና ትልቅ ሀይል ያለው ነው።

## የኢትዮጵያን ጓዳ ቴዲ አፍሮ ሲሞላው

ሀገራችን ኢትዮጵያ በሌላው የዓለም ክፍል መልካም ገፅታ ባይኖራትም ለመላው ልጆቿ ተስማሚ የአየር ንብረት ያላት ውድ ሀገር ናት። ህዝቦቿም ቢሆኑ በእንግዳ ተቀባይነታቸው በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ መልካም ምግባር ያላቸው ናቸው።

ምንም እንኳን ይህ እውነተኛ ገፅታዋ ቢሆንም ሀገራችን በድህነት ስሟ መጠራቱ አልቀረም። ይህንን ስም ይዛ ግን ዘለዓለም አትኖርም። ደሃ የሚለውም መጠሪያዋ ተረት ሆኖ ይቀራል። ህዝቦቿም ቀንና ሌሊት ወገባቸውን አስረው ለመልካም ራዕይ ይሮጣሉ።

የታላቁ የሬጌው አቀንቃኝ ቦብ ማርሊይ 60ኛ የልደት በአል በሀገራችን መዲና አዲስ አበባ በየካቲት ወር 1997 ዓ.ም ይከበር ነበር። እንኳን የዚህን ታላቅ አርቲስት የልደት በአል ማክበር ቀርቶ ትንሽም ድግስ መደገስ ወገብ ይሰብራል። በዚህ የልደት በአል ላይ ከአርቲስቱ ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ውጪ ከተለያዩ የአፍሪካ አገራትና አውሮፓ የመጡ የውጭ ዜጎች በልደት በአሉ ላይ ታዳሚ ነበሩ።

ልብ በሉ! የቦብ ማርሊይን የልደት በአል ለማክበርና የበአሉን የክንውን ስርአት ለመከታተል ሲመጡ እነዚህ አንቱ የተሰኙ አርቲስቶችና ሌሎችም እንግዶች ለአገሩ ባዳ ለሰዉ እንግዳ ናቸው። እነዚህን በእንግድነት የመጡትን ህዝቦች ማን ያስተናግዳቸው?

እንኳንስ ብዙ አድናቂ ያለውን ቦብን የሚያክል አርቲስት ቀርቶ የአንድን ሰው ልደት ለማዘጋጀት ያለው ውጣ ውረድ በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

እንግዶችን ጋባዥ ኢትዮጵያ ነች። ጓዳዋ ግን ባዶ ነው። ነገር ግን ሀገራችን ኢትዮጵያ የፀሎተኞች አገር እንደ መሆኗ በልጆቿ አታፍርም። በዚህ ጊዜ ዝነኛው ወጣቱ የሙዚቃ አውራ ቴዲ አፍሮ የኢትዮጵያን ጓዳ ሞላው። ይህ አርቲስት ከፍተኛ የሆነ የሀገርና የወገን ፍቅር አለው። በዚህ ታላቅ የልደት በአል ላይ ቴዲ ባይኖር ኖሮ ማን ነበር የጎደለውን የሚሞላው? የበአሉ አዘጋጆች እኛው ሆነን ሳለ እንግዶቻችን ጥሪውን አክብረው ሲመጡ ተገቢውን መልስ ሳይገኙ ሲቀር ምን ያህል ያሳፍር ነበር? እግዚአብሔር ለዚህች ምድር በሰጣት ቴዲ አፍሮ ካለው የተቃጠለ የአገር ፍቅር በመነሳት አገሩንና ወገኑን አኮራ። ባቀነቀነው ቦብ ማርሊይ የተሰኘው ነጠላ ዜማ ለእንግድነት የመጣው ህዝብ ሁሉ እሰየው እንኳን መጣን በማለት ፈነደቀ። ያለአግባብ ያባከኑት ጊዜ፣ ያባከኑት ገንዘብ እንደሌለ መስክረውና የአርቲስቱን ታላቅነት አድንቀውም ወደ መጡበት ተመልሰዋል። ‹‹ቦብ ማርሌይ›› የተሰኘው የቴዲ አፍሮ ነጠላ ዜማ ለህዝብ ጆሮ ሲደርስ የሙዚቃው ኖታና የድምፅ ቅላፄው አጀብ ጉድ ተብሎ ተመስክሮለታል። ቴዲ አፍሮ ለቦብ ማርሌይ የፀና ፍቅር እና ልዩ አክብሮት አለው። ቦብ ማርሌይን በህይወት ዘመኑ ፀበኛ ፓርቲዎችን ያስታረቀ፣ አፍሪካን አንድ ለማድረግ የታገለ፣ በጥቁሮች ላይ የሚደረገውን የነጮች አድሎአዊ ጫና አጥብቆ የተቃወመ፣ በተለይ ሀገራችንን ኢትዮጵያን እጅግ የሚወድ፣ ህዝቦቿንም የሚያፈቅር ነው።





# ትንሳኤዋን ዘምርላት!

አንተ የሀገር ጀግና - አንተ ስመ-ጥሩ

ቅን ነህና - የህዝብ መከታ ክብሩ

ዛሬም በዚያ በተለመደው የእውነት ቃልህ

በገባኸው ቃልኪዳን በፅኑ ማዕተብህ

አለሁልሽ በላት ለእምዬ ኢትዮጵያ ለዚች ውድ ሀገርህ።

አዎን፣ ለዚች ውድ ሀገርህ

ለዚች የፈጠረችህ ልጄ ብላ በዕልልታ

በክብር የተቀበለችህ እጆቿን ዘርግታ

ለገነት ላይ ያኖረችህ ና ብላ በደስታ

ዛሬም ሁናት ኩራት መከታ አለኝታ።

አሁንም

ባንዲራዋን ከፍ አድርገህ አውለብልብላት

ፍቅር አንድነቷን ስበክላት

ሰላምዋን ተመኝላት

ትንሳኤዋን ዘምርላት

ብልጽግናዋን አብስራት

በዚያ በኃያሉ በረቂቁ ጥበብህ

በዚያ ተስረቅራቂ ውብ አማላይ ድምጽህ

በላት እንደገና እምዬ ሀገሬ ኢትዮጵያ

አንቺ የተባረክሽ ምድር የእግዚአብሔር ቃል ማሰሪያ

ኑሪ ለዘላለም የዓለም ኩራት ሆነሽ መክበሪያ።

# 6

# ቴዲና ነፃነት

***"እግዚአብሔር የሰው ፍጥረትን ሲፈጥር በነፃነት ስለሆነ በነፃነት መኖርን እጅግ በጣም እመርጣለሁኝ"***

ቴዲ አፍሮ

ለወጣቱ የሙዚቃ ንጉስ ዘፈን ማለት፡- ሐሳቡን ያለምንም ገደብ በነጻነት መግለጽ ነው። በመሆኑም የቴዲ አፍሮ ዘፈኖች የነፃነት ብርሃንን የተላበሱ መሳጭ ናቸው። ይሄንን ልጫወት ያኛውን ልተወው ወይም ይቅርብኝ የሚል የፍርሃት ስሜት በፍጹም የማይነበብበት የዘመኑ የኩራት መገለጫ እና እውነተኛ ሠላማዊ ፍጡር መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም።

ለመሆኑ ስንቶቹ የሃገራችን ዘፋኞች ይሆኑ እንደ ቴዲ አፍሮ ዘፈን የነፃነት ጉዞ የመሆኑ ምስጢር የበራላቸው? አንድ አቀንቃኝ በሚያዜመው ርዕሰ ጉዳይ ላይ እውነትን በዜማ ለመግለጽ የሚፈራ ከሆነ ዘፋኝ ሳይሆን በአጋጣሚዎች ብር ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ጥቅመኛ ያስብለዋል። እናም ዘፈን የነፃነት ዋነኛው መንገድ ከሆነ እያንዳንዱ የሃገራችን ዘፋኝ ሃሳቡን ያለ ገደብ በነፃ ማለማት





ይጠበቅበታል። የነፃነት ሰው ለመሆን ደግሞ የነፃነት መንገድ ሊከተል ግድ ይላል። የቴዲ አፍሮ የነፃነት ጉዞ ግን በያዘው የዘፈን ሙያ ላይ በስፋት ጎልቶ የሚታይ ነገር ነው። በመሆኑም የፈጠራ ስራዎቹ ከሃገር ቤት አልፈው አፍሪካንና አውሮፓን በማካለል የተቀባይነት መጠን ወሰን የለሽ ሆኖአል።

ቴዲ አፍሮ የልዩ ልዩ ነገሮች ባለፀጋ ውድ ፍጡር ነው። "እግዚአብሔር የሰው ፍጥረትን ሲፈጥር በነፃነት ስለሆነ በነፃነት መኖርን እጅግ በጣም እመርጣለሁኝ" ሲል እራሱ ቴዲ አፍሮ በግልጽ ይናገራል። እውነት ምን ጊዜ እውነት ነች። የቴዲ አፍሮን ምትሃታዊ ሐይልና ጉልበት ያላቸው ዘፈኖቹ ቴዲ የነፃነት ሰው ስለመሆኑ ምስክሮቹ ናቸው። ብዙዎች በፍርሃት፣ በመሸማቀቅ ብሎም በቸልተኝነት የሚዘሉትን የነፃነት ጉዳይ በቴዲ ህሊና ግን ልዩ ቦታ አለው። ቴዲ መናገር ካለበት ይናገራል። ካላመነበትና ካልመሰለው ደግሞ ሃሳቡን ያለ አንዳች ስሜት በነፃነት ያራምዳል። ስለሆነም ዛሬ ያለው ቴዲ አፍሮ ነገም ይኖራል። ራስን የመሆንና የማወቅ ታላቅ ምስጢር ያለው እዚህ ጋ ነውና።

በገንዘብ የማይለውጥ ለእውነት ሲል ወደፊት የሚራመድ ስለ መሆኑ በርካቶች ይመሰክሩለታል። ምክንያቱም የማንንም ክብር በማይነካና በማያጎድፍ አካሄድ ሃሳቡን በነፃነት ስሜት በእውነት አደባባይ ላይ የሚናገር ታላቅ አርቲስት ነውና። አርቲስት (ዘፋኝ) የህዝብ አንደበት እስከሆነ ድረስ የህብረተሰቡን የልብ ትርታ አድምጦ በአደባባይ ችግሩን የመናገር ነፃነት ሊኖረው ይገባል።

ሙዚቃ እጅግ በጣም ሐይልና ጉልበት ያላት ሞገደኛ ነች። የሰዎችንም ልብ ዘልቃ የመግባት እድልዋ የሰፋ ነው። በመሆኑም የሙዚቃን ጠንካራ ጉልበት አርቲስቶቻችን (ዘፋኞች) እንደ ቴዲ አፍሮ መረዳት ያለባቸው ይመስለኛል። አንድ ሰው ራሱን ማወቅ ሲጀምር ወይም ማንነቱን ሲረዳ በነፃነት ጎዳና ላይ ይንሰራፋል። ዘፈን ያለ ነፃነት ነፃነት ያለ ዘፈን ከቶ ሊሆን አይችልምና ሁላችን የጥበበ ሰዎች በመሆኑም በፈጣሪ የተሰጠንን የነፃነት መብት ልንጠቀምበት ይገባል።

## ሙዚቃ ለቴዲ

የነፃነት ምስጢር

የውስጥ ስሜቱ ምስክር

እስትንፋስ ጉልበቱ

ሃይልና ብርታቱ

እርካታ የጥማቱ

ነች ሙዚቃ ለቴዲ የነፃነት መገለጫ

የደስታው ምንጭ የነፍሱ ምርጫ

የውስጡን የተነፈሰባት

ምኞቱን የገለጸባት

ቅኔን የተቀኘባት

ህልሙን የፈታባት

ነች ሙዚቃ ለቴዲ ሁሉ ነገሩ

ከሥጋ ከደሙ የተዋሃደች እስትንፋስ ክብሩ!





# 7

# የሰላም እርግብ

***‹‹ብፁህ ሰው ከምሁር ይማራል››***

እየሱስ ክርስቶስ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ ‹‹መንፈስ ከሰማይ እንደ እርግብ ሲወርድ አየሁ›› ማለቱን ቅዱስ በሆነው የአምላክ ቃል መፅሀፍ .ቅዱስ ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ እርግብ የሰላም ምልክት ከመሆኗም ባሻገር ፍቅር አብሳሪና መልዕክተኛ ነች፡፡ እርግብ የዋህ ነች፡፡

የሀገራችን ሙዚቃ ብላቴና የሆነው ወጣቱ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ስራና ምግባር፣ ልፋቱና ውጤቱ፣ ድርጊቱና ክንውኑ፣ ኑሮና ህይወቱ፣ የሰላም እርግብ አስብሎታል፡፡ ይህ ድምፃዊ በተፈጥሮው የብዙ አስገራሚ ነገሮች ባለቤት ነው፡፡ የማንንም ሰው ክፉ መስማት አይፈልግም፡፡ ሁለት የተጣሉ ወገኖች ከገጠሙትም ሳያወቃቅስ ‹‹አንተም ተው፤ አንተም ተው፤ ይቅርታን አውርዱ፤›› በማለት በመሀከላቸው የሰፈነውን ፀብ አስወግዶ የሰላም ዘር ይዘራል፡፡ ቴዲ አፍሮ ፍቅርን ሰጥቶ ፍቅርን መቀበል ይችላል፡፡ በተፈጥሮ የታደለውና ያካበተው ሰላም ለሚወደው ሁሉ እንዲሆንለት አጥብቆ ይመኛል፡፡ ቴዲ ሰላምን ይወዳል፡፡ የሁለት ወገኖችን የእርስ በርስ ፀብ

አጥብቆ ይቃወማል።

በ1997 ዓ.ም በግንቦት ወር ለህዝብ ጆሮ የደረሰው ‹‹ጃ ያስተሰርያል›› የተሰኘው አልበም ሰላምን ከመናፈቅ፣ መቻቻልን ከማስተማር፣ ፍቅርን ከመሰበክ፣ ወደ ኋላ አላሰም። ማይኩን ጨብጦ መድረኩን ሲረግጥ የመጀመሪያው መልዕክቱ ‹‹ሰላም ነው›› የሚል ነው። በተሰያየ አጋጣሚ የሚገጥመውን ሰውና ጓደኞቹን ‹‹ሰላም ናችሁ›› በማለት የሰላምን አስፈላጊነት የሚገልጽ የሰላም እርግብ ነው።

ቴዲን ከሰላም አብሳሪዋ እርግብ ለይቶ ማየት አይቻልም። ልቡ የዋህ፣ ለፍጡር አዛኝ፣ ሰላም ናፋቂ ብሎም ዘማሪ ነው። የዚህ ሙዚቃኛ ሃሳብ በእርሱ ዘንድ ያለው ሰላም በሚወደው ወገኑ ላይ ተንሰራፍቶ ማየትን ይመኛል። ቴዲ ገራገር ልጅ ነው። ያለውን ነገር በማበርከት ወገናዊ ፍቅሩን በተለያዩ ጊዜ የሚገልጽ ነው። ለማንም ሰው ከገንዘብ ይልቅ ሰላም ወሳኝነት አለው የሚለው ቴዲ ስለ ሰላም ተናግሮና ዘክሮ አይጨርስም። የማንም ሰው ሰላም ሲደፈርስ ማየት አይፈልግም። ሰላምን ፈላጊ ሰላምን አያጣምና በሰላም ተከቦ በእውነት ታጅቦ ለዘመናት ይኖራል። የቴዲ አፍሮ ትልቁ ሀብት የብር ክምችት ሳይሆን የሚወደውን ህዝቡን በሰላም ታጅቦ ማየት ነው። እየሱስ ክርስቶስ ከሃዋርያት ጋር በተገናኘ ጊዜ ‹‹ሰላም ለእናንተ ይሁን›› በማለት አይደል የሰላምን መሰረታዊ አስፈላጊነት የነገራቸው? ቴዲም ከፈጣሪው በተሰገሰው ፀጋ ሁልጊዜ የሰላምና የፍቅር ሰው ነው። ብልህ ሰው ከምሁር ይማራልና ልብ እንበል። ሰንቱ ፍጡር በሰላም ከቤቱ ወጥቶ በሰላም መመለስ እንዳቃተው ቤት ይቁጠረው።

ቴዲ ግን በሚያሳየው እርጋታ፣ በሚዘምረው ሰላም፣ በሚያደርገው ቸርነትና በወገኑ ላይ ላለው ርህሩህ ልብ ሳቢያ የሰላም እርግብ ነህ ሊባል ችሏል። የሰው ልጅ ያለ ሰላም ሲኖር እንዴት ይችላል? ቴዲ አፍሮ ከሀገሩ አልፎ ለሰዓሰም ሰላም መሆን አብዝቶ የሚመኝ የሰላም ሰው ነው። በእስራኤልና በፍልስጤም መካከል አሳባራ ያለውና ለረጅም አመታት የዘለቀውን ጦርነት ከልቡ ያሳዘነው





ቴዲ ‹‹እየሩሳሌም›› ሲል አዚሟል። በዚህ ዘፈኑ ውስጥ የሰው ልጆችን ያለ አግባብ መሞትና የሰላምን መሰረታዊ አስፈላጊነት ጠቅሷል።

ቴዲ አፍሮ ለሰላም ትልቅ ቦታ አለው። የሰው ልጆች ሁሉን ነገር ለማከናወን የሚችሉት በሰላም ነው ብሎም ያምናል።

## *የሰላም እርግብ*

ያች መልዕክተኛ - ሰላም አብሳሪ እርግብ
ኖረች ከቴዲ ጋር - ከዚያ ንፁሁ ልብ
ሰላም ከማይሰለቸው - ሁሌ አውርቶ ከማይጠግብ
    በሄደበት ቦታ - በቆመበት ምድር
    ሰላምን ወዶ - ሰላምን ሊዘምር
    ተፈጠረ ቴዲ - የሰላም አምባሳደር
ጥላቻን አውግዞ
የሰይጣንን ክፋት ገልጦ
ሰላም ሊያሰፍን በምድሩ
ተፈጠረ ቴዲ - ልበ-ቀና ገራገሩ
    ሁሌ ሰላም ብሎ
    ሰሰሰላም ዘምሮ
    ሰላምን ሰብኮ - ሰላምን ሊዘራ
    እንካችሁ ይላል - የፍቅር አዝመራ
ልዩነታችንን አጥብቦ
አንድ አድርጎ ሰብስቦ
ዕርቅ ያወርዳል - ፀበኛውን አስማምቶ
    ይሄ የቅንነት መንገድ - የታደሰው ቀና ልብ
    ምሳሌ የሆነ - የዚያች የዋህዋ እርግብ
        ብልፅግናችንን ተመኝቶ - ከፍ ሊያደርገን በዓለም
        እንደ እሱ ሰላም ሰላም ያለ - ከቶ አንድም የለም!





8

# ቴዲ አፍሮ ከባህሪይ አንፃር ሲታይ

### *‹‹ፍቅር ያሸንፋል››*

**ቴዲ አፍሮ**

መልካም ባህርይ የማንነት መገለጫ ነው፡፡ ማንም ጥሩ ሊሆን ቢፈልግ ቀድመው የተገኙትን ጥሩዎች አክብሮ ይገኝ፡፡ ማንም ደግሞ ስራው ጉብዝናው ይመስክርለት እንጂ ጎበዝ ነኝ ብሎ በማውራት በየአደባባዩ የምላስ ምስክርነት አያስተጋባ፡፡ መልካምነት ለራስ ነው፡፡ ትዕቢትና ኩራት ደግሞ የውርደት መሰላሎች ናቸው፡፡ ማንም ሰው የራሱ የሆነ የተፈጥሮ ባህሪ አለው፡፡ መልካም ባህሪ ፍቅርን ይሸልማል፡፡

እያንዳንዱ ሰው እንደመልኩ ብቻ ሳይሆን እንደ ውስጡ የቅንነትና የክፋት ባህሪ ባለቤት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ጥሩ ባህሪ ያላቸው ሰዎች በጥሩነታቸው ሊወደዱ፣ ሊከበሩና እንደ ምሳሌነት ሊጠቀሱ እንደሚችሉ አሻሚ አይደለም፡፡ በተቃራኒው መጥፎ ባህሪያቸውን

ደብቀው ተሰሳልሰው ጎንበስ ቀና በማለት ያልሆኑትን ለመሆን የሚያስመስሉ በርካቶች ይኖራሉ፡፡ በጥበብ ህይወት ውስጥ ላሉ የጥበብ ባለሞያዎች ለህዝብ ምሳሌ ናቸውና በሚሰሩት የጥበብ ስራ ብቻ ሳይሆን በግል ህይወታቸውም የጥሩ ባህሪ ባለቤት ሆነው መኖርና መታየት አለባቸው፡፡

ለምሳሌ አንድ ፊልም ሰሪ /ተዋናይ/ ብዙ ጊዜ በሚሰራው የትወና ሂደት ውስጥ መልካም ሆኖ ይሆናል፡፡ የግል ህይወቱ ግን ከዚህ በተቃራኒው መንገድ ከሆነ ያ ባለሞያ ትክክል አልነበረም፡፡ ምክንያቱም እውስጡ የሌለን ነገር በሀሰት ማስመሰል ይሆናልና፡፡ ማንም ሰው መሆን ያለበት እራሱን እንጂ ሌላውን መስሎ መገኘት የለበትም፡፡ ሰዎች አንድን ሰው በሰራው ስራ ውጤታማነት ብቻ ሳይሆን በግል ባህሪውም ጭምር ነው ማድነቅና ማወደስ አለባቸው፡፡ እንጂ አረማመዱ ማራኪ የአፉ ፍሬ ትቢያ መሆን የለበትም፡፡ ስንቶችንስ አይተናል በሌላቸው ነገር ሲኮፈሱ አርቴፊሻናዊ ባህሪን እያንፀባረቁ መልካምና ጥሩ ለመምሰል ሲዳክሩ፡፡

ሙዚቃ ትልቅ መልእክት የሚተላለፍበት ጥበብ ነው፡፡ ዘፋኝን ማድነቅና ማወደስ ዛሬ ሳይሆን የከረመ ባህላችን ነው፡፡ ትውልድ እየተቀየረ አዲስ ትውልድ እየተተካ በሔደ ቁጥር የኢኮኖሚ እድገት ብቻ ሳይሆን የሰዎችም ንቃተ ህሊና እየተሻሻለና እየጎለበተ የሚሔድበት ሁኔታ በግልፅ ይታያል፡፡

በዚህ ዘመን በዘፈን ስራው በሚሊዮኖች የሚወደድና በብዙ ሚሊዮኖች የሚደነቅ የክፍለ የዘመኑ ብርቅዬ የዘፈን አብዮተኛ ቴዎድሮስ ካሳሁን ጊዜና ወቅት ጠብቀው ለህዝብ ካበረከታቸው ማራኪና ጣፋጭ የዜማ ስራዎቹ በተጨማሪ ለአድናቂዎቹ በተፈጥሮ ባህሪው የሚመች እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

‹‹ፍቅር ያሸንፋል›› የሚለው ቴዲ እሱ የፍቅርና የሰላም ፍጡር በመሆኑ ብዙዎቹን በፍቅር ለማሸነፍ ችሏል፡፡ ሠዎችን የመውደድና በፍቅር የመማረክ መግነጢሳዊ ሀይል አለው፡፡ ቴዲ ብዙ





ጊዜ በሚያቀርባቸው የሙዚቃ ኮንሰራቶች ላይ በመልካም ባህሪው የብዙ ሰዎችን ቀልብ ለመግዛት በቅቷል፡፡ ቅንነት ያበዛል፤ መልካም ነገርን አብዝቶ ያስባል፤ ያለውን ነገር ያካፍላል፤ አድናቂዎቹን ከአብራኩ እንደተፈጠሩ ልጆቹ አድርጎ ይወዳል፤ ህይለኛም የሰው መውደድ ልቡ ላይ ነግሶበታል፡፡ በየትኛውም ቦታና ስፍራ አድናቂዎቹ ሲያገኙት ያሉትን ለማድረግ የተቻለውን ይጥራል፡፡ ፈርምልን ካሉት የአድናቆት ፊርማውን ይፈርማል፡፡ የሚጠይቁትን ጥያቄ ሳይደምር ሳይቀንስ በሚገባ ይመልሳል፡፡ ከእርሱ ጋር መቆየትም ከፈለጉ ካለው ሰዐት ላይ አሸጋሽጎ አብሯቸው በቁም ነገር ያሳልፋል፡፡

ጣራ የነካ ዝና ስላለኝ የኩራት ስሜትን ላንፀባርቅ የማይል ማንነቱን አብጠርጥሮ የሚረዳ ጥንቁቅ አርቲስት ነው፡፡ ከሰዎች ጋር ያለው ማህበራዊ ግንኙነት መልካም ከማድረጉም በላይ በእያንዳንዷ ነገር ጥልቅ ቅንነት የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

ነገር ግን አንዳንዶች እፍ ቢሉት እንደ ሻማ በማይክሮ ሰከንድ የምትጠፋ ጭላንጭል ታዋቂነትን ይዘው ታዋቂነት በሰጣቸው ህዝብ ላይ ሲንጠባረሩ፤ ትክሻቸውን ሲነቀንቁ፤ በሙሉ አይናቸው ለማየት ሲጠየፉ ስንቱ ታዝቦ በትዕዝብት አልፏቸዋል፡፡ አንድ ዘፋኝ ካሴት የሚሰራው ለህዝብ ነው፡፡ ህዝብ ደግሞ ገዝቶ ይሰማል፡፡ ይህ ደግሞ የእርስ በእርስ ጥቅም ሳይሆን የህይወት ጉዞ ነው፡፡

ነገር ግን ህዝብ በገዛው ካሴት ዘፋኙም ሸጦ ባገኘው ብር ህዝብ ላይ የትዕቢት መጋረጃን ከመዘርጋትና ራስን እንደ አዋቂና እንደ ትልቅ ከመቁጠር ይልቅ የቴዲ አፍሮን ባህሪና ያለውን ትልቅ የህዝብ ፍቅርና አክብሮት በማሰብ እኔ ማን ነኝ? ምንስ እየሰራሁ ነው? አካሔዴ ወዴት ነው? በማለት ማሰብ ይገባቸዋል፡፡ ክቡር ዶ/ር ጥላሁን ገሰሰ በአንድ ወቅት እንዲህ ሲል ተናግሯል፡- ‹‹ልኮራ እፈልግና እማን ላይ ነው የምኮራው እላለሁ፡፡ አንተ የተባልከውን ሰው አንቱ ባስባለህ ህዝብ ላይ አትንጠራራበት›› ብሎ ነበር፡፡ ስለዚህ በትንሽ ታዋቂነት ሰክረው ባስከበራቸው ህዝብ ላይ ለሚመፃደቁ

አንዳንድ አርቲስቶች እንደማንም ሰው መሆናቸውን ለዘነጉትም ማንነታቸውን አበጥረው ማወቅ ይገባቸዋል። ቴዲ አፍሮ ግን ከሚሰራው የዘፈን ተአምር በተጨማሪ ከሌሎች ልቆ እንዲወደድ ያደረገው ይህ መልካም ባህሪውና እውነተኛነቱ ነው።

ሌላው ቀርቶ በተሰጠው ተፈጥሯዊ ችሎታ ሳይኩራና ሳይመፃደቅ ለብዙ የስራ ባልደረቦቹ ጥሩ የሆኑ ስራዎችን አበርክቷል። ለሙያ አጋሮቹ ዜማም ይሁን ግጥም ሲሰጥ ከራሱ ባልተናነሰ አጣፍጦና ከሽኖ ነው። እኔ እበልጣለሁ የሚል ግትር አቋም የለውም። ሊሰራ ያሰበውን ሰው ያበረታታል።

ተስፋ የቆረጠውን በሀሳብ በስነልቦና ብሎም በገንዘብ ደጉሞ ተስፋው እንዲለመልም ያደርግለታል። ስለሆነም ይህ ወጣት ድምፃዊ በገንዘብ መጠን ቢጎለብት፣ የህዝብን ፍቅር ከሌሎቹ አብልጦ ቢላበስ ያንሰዋል እንጂ አይበዛበትም፣ ሁሉን ነገር የሚሰጥ እግዚአብሔር ነውና። ‹‹በላብህ ጥረህ ግረህ ብላ›› እስከተባለ ድረስ፣ ቴዲ እግዚአብሔር ሊረዳውና የስራውን ፍሬ ሊባርክለት የቻለው የልፋቱንና የድካሙን ውጤት አይቶ ነው። በተለይ ደግሞ ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር አምላክ የልቡን ንጹህነት ስላየለት ነው። ቴዲ በማንም አይቀናም፣ የማንንም ውድቀትም አይፈልግም። ንፁህ ልብ ያለው የኢትዮጵያ ልጅ ነው።

የጊዜን ክቡርነት ጠንቅቆ የተረዳ አንድም ሴኮንድ ቢሆን ያለ አግባብ የማይባክንበት፣ የስራን ክቡርነት ያወቀ፣ ታላቅ አርቲስት ነው።

በባህሪውም ቢሆን ሰውን አክባሪ፣ የተቸገረን ሰው አይቶ ማለፍ የማይሻ በማንም ሰው ላይ ችግር ሲደርስ ማየት የማይመኝ፣ ያለውን ለሌላው የሚያካፍል ሩህሩህ በመቻቻልና በፍቅር መኖር የሚመርጥ፣ ከምንም በላይ ሀገሩንና ወገኑን የሚወድ፣ የሀገሩን ትንሳኤ አብዝቶ የሚመኝ፣ እውነተኛ የህዝብ ልጅ ነው።





## *የምታበራ የእውነት ፀሐይ*

እውነትን የሚሰብክ በተሰጠው ሙያ

አንድ አለ ታላቅ ሰው ቴዲ ለኢትዮጵያ

ታሪክን ይናገራል እውነትን አስደግፎ

የነፍሱ ታቦት በጥበብ ታጥሮ

ለጥቅም የማያድር

በእምነቱ የማይደራደር

የሐቅ አባት እውነተኛ

ላመነበት የማይተኛ

ለፍትሕ ተሟጋች

ለሀገር ህዝብ ሟች

አንድ አለ ቴዲ እውነትን የሚናገር አትልቶ

የእውነትን ፍሬ አጣጥሞ በልቶ

የማትሞት እውነት አለች በቴዲ ላይ

ቀንና ሌሊቱን የምታበራ ፀሐይ

አሁንም ቦግ ትበል ትፍለቅለቅ እንደ ምንጭ

በእውነት ማዕበል አሉባልተኞችን ታስምጥ

፫

9

# ቴዲ አፍሮ ማንን ይፈራል?

***‹‹የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው››***

የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ብዙ ውጣ ውረድ በበዛበት የዓለም መድረክ ላይ የሚተውን ፍጡር ነው፡፡ በመኖርና በመሞት መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ በፍርሃትና በድፍረት ያለው ልዩነት ግን ጥቂት ብቻ ነው፡፡

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ፈሪ ነው፡፡ ፍርሐት ከውስጡ ጨርሶ የወጣለት ሰው ደግሞ ደፋር ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ቢባልም የፍርሃት ስሜቱ ፈፅሞ ተወግዶ ይጠፋል ማለት አይደለም፡፡ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ብዙ አስፈሪ ነገሮች አሉ፡፡

የመኖር ዋስትና ማጣት፣ በሞት መወሰድ፣ በጨለማ ውስጥ መኖር፣ ያልታሰበ ድንገተኛ ክስተት፣ ጩኸት፣ ኮሽታና ... ወዘተ ያስደነግጡታል፡፡ ብሎም ያስፈሩታል፡፡ ፍርሃት ከራስ አዕምሮ





የሚመነጭ ድንገታዊ የነርቭ መልዕክት ነው፡፡ የውስጣችን የነርቭ ክፍል አስቀድመን ስለፍርሃት ሰውስጥ ስሜታችን ከነገርነው መላ ሰውነታችን በፍርሃት ስሜት ሳናስበው ሊንቀጠቀጥ ይችላል፡፡

በርካታ የአለማችን ሰዎች በሞት መወሰድን አብዝተው ይፈራሉ፡፡ ሞትን ግን ለምን እንደሚፈሩት ጠንቅቀው ምን ያህል እንደሚያውቁ ግራ ያጋባል፡፡ ስላላየነው ነገር እንዴት ልንፈራ እንችላለን?

ለመሆኑ የምንፈራቸው ነገሮች በእውነት አስፈሪዎች ናቸውን? በዚህች ዓለም ማንም ፈሪ ወይም ደፋር ሆኖ የተፈጠረ የለም፡፡ የምንፈራውም እንዲሁ በራሳችን ምክንያት ነው፡፡ ደፋር ወይም ፈሪ የምንሆነውም ውስጣችን በተፈጠረው ድምር ውጤት መነሾ ነው፡፡

የህገራችን የሙዚቃ አባት የሆነው ድምፃዊው ቴዲ አፍሮ ኀ ፍርሃት አስቦ አያውቅም፡፡ በህይወት ዘመኑ አንድም ቀን ፈርቶ ያውቅም፡፡ ይህ ድምፃዊ በአንድ ወቅት በአንድ ጋዜጠኛ እንዲህ ተብሎ ተጠይቆ ነበር፡፡ ‹‹በአሁን ሰዓት በአገር ውስጥና ከሀገር ውጪ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ አድናቂዎች አሉህ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ያንተን መውደቅ የሚመኙ እንደሚኖሩ እገምታለሁ፡፡ ለመሆኑ በዚህች ምድር ላይ ምን ያስፈራሃል?›› ሲል ጠይቆት ነበር፡፡ ቴዲ አፍሮም ‹‹እግዚአብሔርን እፈራለሁ፡፡ ከዚህ ሌላ ግን ማንንም አልፈራም፡፡ ምክንያቱም የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው" አለ፡፡

በወቅቱ ጋዜጠኛው ለጠየቀው ጥያቄ ያገኘው መልስ እጅግ አስገርሞት ስለነበር ‹‹የዓለማችን ልበ ሙሉ ሰው፣ ጊዜን በስራ የመነዘረ፣ ለዚህች ምድር ለበጎ ተግባር የተፈጠረ፣ መልካም ሰው" ሲል አሞካሽቶታል፡፡ የቴዲ አፍሮ አፈጣጠር ለብዙዎች የሚገርም ክስተት ነው፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚናገረው አስደናቂ ቃል የብዙዎችን አግራሞት ያጭራል፡፡

አም እግዚአብሔር ለፈራው አክባሪ፣ ለጠራውም ፈጥኖ ደራሽ፣ ለራቀው እሩቅ ነው፡፡ ቴዲ አፍሮ አንድም ጊዜ የፈጣሪውን ስም ከአንደበቱ ሲለየው ታይቶ አይታወቅም፡፡ በደስታ፣ በሐዘኑ፣ በችግሩ፣ በህይወት ውጣ ውረድ የአምላኩን ስም ከእውነተኛ ልቡ ሲጠራ ተሰምቷል፡፡

በተደጋጋሚ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር አለ ብሎ የሚያምን ጠንካራ ሰው ነው፡፡ ‹‹ስራዬን እንደማንኛውም ሰው ነው የምሰራው፡፡ በምሰራበት ጊዜ ግን የሰራሁት ስራ ወይም ዘፈን ለአድማጭ ጆሮ ከመድረሱ በፊት እኔን ሊያስደስተኝና ሊማርከኝ ይገባል›› ይላል፡፡ ‹‹በዚህ ላይ ደግሞ የእኔን የስራ ውጤት እግዚአብሔር ስለሚባርክልኝ ሁሉ ነገር የተቃና ይሆናል›› የሚለው የሁልጊዜ ቃሉ ነው፡፡

በአሁኑ ሰዓት ከአገሩ ኢትዮጵያ ጀምሮ በአፍሪካና በአውሮፓ አገራት ጭምር ከፍተኛ እውቅና ያገኘ ይህ አርቲስት ‹‹ሁሉ የሆነው ከእግዚአብሔር ነው›› ይላል፡፡ ‹‹መውደዱንም ሆነ የሰውን ፍቅር የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው›› ካለ በኋላ፤ ‹‹እኔም መላው የኢትዮጵያ ህዝብንና አገሬን እንዲሁም በውጪ ያሉትን አድናቂዎቼን እወዳቸዋለሁ፤ ሀሳባቸውንም እረዳለሁ፡፡ እኔም ዛሬ ካለሁበት ቦታ እንድደርስ የረዱኝ እነርሱ ናቸው›› ሲልም ይደመጣል፡፡ ቴዲ አፍሮ በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ህዝብ ልብ ትርታ ውስጥ ህያው ነው፡፡ መወደድን የሚሰጥ እግዚአብሄር ነው፡፡

በአንድ ወቅት ‹‹ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዓለምን የማዳን ፀጋ አለው›› ብሎ ሲናገር ለታሪክ የሚቀመጥ ምርጥ ቃል አስብሎለታል፡፡ ቴዲ ይህንን ከባድ ቃል የተናገረው ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር ቅርብ ነች፤ ህዝቦቿም በፀሎት የበለፀጉ ፈጣሪያቸውን የሚፈሩና የሚያከብሩ ናቸው፤ ከሚለው ሀሳብ በመነጨ ታሳቢነት ነው፡፡ ዓለም ካለችበት የረሃብ፤ የጦርነትና የእልቂት ጣጣ በኢትዮጵያኖች ፀሎት ሁሉ ነገር ይረግባል እንደማለት ነው፡፡





# ቴዲና ፍርሃት

ቴዲና ፍርሃት መቼ ይዋደዳሉ

ጎዛቸውን ይዘው በሩቅ ይሸሻሻሉ

ቴዲ ፍርሃት አያውቅም ከእግዜር ሌላ

ላመነበት ነገር ሳያፈገፍግ ወደኋላ

እውነትን እንግቦ ይጓዛል በመላ

ፈጣሪ አምላኩን አድርጐ ከለላ

እሱ አይፈራም ለእውነት መለዋት

ሐቀኛ ነው አይጠጋውም ፍርሃት

ታድሎታል ጀግንነት

ከአባቱ የወረሰው ወንድነት

እውነት ነው ስንቁ

ይሄ መልካም ሰው ብርቁ

እናም

በዚህ ዓለም እሱ ምን ሊፈራ

ወንድነት ነውና የእሱ ሥራ

የእውነትን ምስጢር አያውቅም ተርቦ

ይኖራል ለዘላለም እውነትን እንግቦ

10

# ታላቅ ሰው ታላላቅ ተግባር የሰሩትን ያከብራል

በዚች ምድር ላይ የማያልፍን ስራ ሰርተው ላለፉ ስኬታማ ሰዎችን ማክበር የታላቅነት ሚስጢር ነው። ማንም ሰው ራስን የመሆን ሰዋዊ ጥበብ ሲኖረውና ለሚሰራው የፈጠራ ስራ መልካም ግምት ሲሰጥ ታላላቅ ክንውኖችን ሰርቶ ለመገኘት አስቸጋሪ ነገሮች አያዳግቱትም። በዓለማችን ላይ በርካታ የዚህ ዓይነት ስኬታማ ሰዎች አሉ።

አንድ ሰው በሕይወት ዘመኑ የሰራው ታሪካዊ ስራ ከአፈር በታች በዋለበት ጊዜ እንኳን ሰርቶ ያሰፈው ታላቅ ተግባር ስሙን ዘወትር ያነሳሰታል።

ስለ ሙዚቃም ሲነሳ አሁን ባለንበት ትውልድ ውስጥ የመድረኩ ፈርጥ፣ እንደ ባህር ዓሣ የሚወረወረውና በሙዚቃ ስራ ውስጥ እየቀዘፈ የሚዋኘው፣ ብዙዎችን በሚሰራው ማራኪ የሙዚቃ ስልት የሚያስደምመው፣ ትልቅ ሰውጥ የፈጠረውና የጥበብን





ሕይወት በብዙኃኑ ህዝብ ዘንድ እንዲወደድ ያደረገው ወጣቱ ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል። ይህ ወጣት ድምጻዊ ብዙዎች የሚዘነጉትን ወይም በቸልተኝነት የሚዘሉትን የታላላቅ ሰዎችን ተግባር ፈጣሪው በተፈጥሮ በቸረው እምቅ የጥበብ ችሎታ በመጠቀም በማራኪ ድምጹ አቀንቅኖላቸዋል። ወደ ኋላ መለስ ብለን ቴዲ ለህዝብ ካበረከታቸው የሙዚቃ አልበሞች አቡጊዳን ብቻ ብንመለከት እንኳን ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ እና ለጀግናዊ አትሌት ሺህ አለቃ ሐይሌ ገ/ሥላሴ ዘፍኖላቸዋል።

ልብ በሉ! ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ የኢትዮጵያ ንጉስ ነበሩ። በነገሱባቸውም ዓመታት ታላላቅ ተግባሮችን አከናውነዋል። በተለይ በአፍሪካ ህዝቦች ዘወትር የሚነገርላቸው የጥቁሮች አፍሪካውያን በነጮች ተረግጦ መኖርና የአፍሪካ አገሮችን መከፋፈል በመቃወም አፍሪካ አንድ ነች በማለት ወገባቸውን ታጥቀው የተከራከሩ በመሆናቸው የአፍሪካ አባት የሚል ቅጽል ስም አለጥቶአቸዋል። ከዚህም በላይ በርካታ ተግባሮችን ለሃገራችን ኢትዮጵያ ያበረከቱ ታሪካዊ ታላቅ ንጉሥ ናቸው።

ሌላው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ ነው። ጀግናው አትሌት ሐይሌ በተሰማራበት ሩጫ ላይ በተለያዩ የዓለም ሃገሮች በመዘዋወር በተወዳደረባቸው ስፍራዎች በሙሉ የአንደኝነትን ደረጃ በተቀናጀባቸው በርካታ ውድድሮች ላይ ለዓለም ሃገራት የሃገሩን ባንዲራ ከፍ አድርጎ ያውለበለበ ከመሆኑም በላይ ለሃገሩ ያለው ፍቅር አስገድዶት ተረከዙን ታሞ ኦፕራሲዮን ሆኖ እንኳን የሩጫ ውድድሩን በድል በማሸነፍ ለባንዲራው ያለውን ስር የሰደደ ፍቅር በተደጋጋሚ ያሳየ ታሪካዊ አትሌት ነው። ቴዲ አፍሮ እነኚህን ሁለት ኢትዮጵያዊያን ታላላቅ ሰዎች ስማቸውን እያነሳ ማንም ሰው ባልሞከረው መንገድ ዘፈነላቸው።

በእነኚህ ታሪካዊ ሰዎች ብቻ ሳያበቃም ጃማይካዊው የሬጌ ንጉስ ቦብ ማርሊይንም አወድሶታል። ቦም ማርሊይ ኢትዮጵያን የሚወድ አረንጓዴ ቢጫና ቀዩን ሰንደቅ አላማ የሚያከበር ከዚያም

በላይ በርካታ ተግባሮችን ያከናወነ ትልቅ ሰው ነው። በተለይ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴን አፍሪካ አንድ ነች የሚለውን ሐሳብ በመደገፍና ከኢትዮጵያኖች ጋር አብሮ በመስለፍ የሚጠበቅበትን ሐላፊነት የተወጣ ታሪካዊ አርቲስት ነው።

ቴዲ አፍሮ ታላላቅ ሰዎችን በማወደስ ታላቅነቱን አስመስክሯል። ቴዲ አፍሮ ወደ ሙዚቃ ዓለም ገና ዘልቆ ሳይገባ ጀምሮ ለክቡር አርቲስት ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ እንዲሁም ባለፉት ዘመናት ለነበሩና ለዘፈን እድገት ትልቅ አስተዋፆ ላበረከቱ የዘፈን ጀግኖች አድናቆቱን ተናግሯል። አንድ ሰው ሌላው የሰራውን መልካም ስራ ማድነቅ ሲጀምር የእሱን ታላቅነት በተዘዋዋሪ መንገድ ይገልጻል። ቴዲ እጅግ በጣም ከፍተኛ የዝና ባለጸጋና በብዙ ሚሊዮን ህዝብ ዘንድ እንደ ተምሳሌትነት የሚገለጽ ኢትዮጵያዊ ታላቅ ድምጻዊ ነው።

ታላቅ ሰው ታላላቅ ተግባር የሰሩትን ታሪካዊ ጀግኖች ያከብራል። ምክንያቱም በልቡ ውስጥ የምትኖር የታላቅነት የእውነት ምስጢር አለችና። በመሆኑም የበረቱ ሰዎችን ታሪክ መዘከርና ማወደስ ታላቅ ለሆነ ሰው ለነፍሱ ደስታን ይቸራታል።





# ከሆኑ አይቀር ...

መሆን ነው እንጂ ከሆኑ አይቀር

እንደ ቴዲ ልበ - ሙሉ በምንም የማይበገር

* * *

ከሰሩ አይቀር - እንደ ቴዲ ታሪክ መስራት

ከራስም አልፎ ለህዝብ ልጅነት መብቃት

* * *

ከተወደዱ አይቀር - እንደ ቴዲ መወደድ

በህዝብ ፍቅር ተከቦ በሞገስ መራመድ

* * *

ከታደሉ አይቀር - እንደ ቴዲ መታደል

ፍቅር ሰጥቶ የህዝብን ፍቅር መቀበል።

# 11

# የቴዲ አፍሮ የደግነት መለኪያዎች

ጥሩ ሰው መሆን ውጤቱና እርካታው ለባለቤቱ ነው። ደስታውም ቢሆን መልካምነትን ያዘለ የህይወት ጉዞ ነው። ደግ ሰው እድሜው ረጅም ወዳጆቹ ብዙ ናቸው። ደግነት ከውስጥ የሚመነጭ የቅንነት ውጤት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ አብዛኛው በየዋህነቱ ለተቸገረ በመርዳቱና በአክብሮቱ የሚታወቅ ህዝብ ነው። ብዙ የሀገራችን ባለሀብቶች በሀገራቸው በተለያዩ ችግሮች ላይ ፈጥኖ በመድረስ ሀገራዊ ወገናዊ ፍቅራቸውን ከገንዘብ እስከ ጉልበታቸው ሲያበረክቱ ይታያሉ። ይህ ሁሉ የደግነት መገለጫ ሊሆን ይችላል።

ዝነኛው ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን በብዙሀኑ ወይም በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ በደግነቱና በጠንካራ የስራ ውጤታማነቱ ዘወትር የሚወደስ፣ በየትኛውም ቦታና ስፍራ በአብነት የሚጠቀስ፣ ታላቅ ተምሳሌት የሆነበት ምክንያት ምን ይሆን? ቴዲ አፍሮ ዘፋኝ ብቻ ነው ለማለት ይከብዳል። ምክንያቱም ከሚሰራው ሙያ በተጨማሪ ለሀገሩ ብዙ ነገሮችን አበርክቷል። ወገኑ በተቸገረ ጊዜ ፈጥሮ ደራሽነቱን አስመስክሯል።





ለምሳሌ፡-

1 ወደፊት ሰንዳፋ ላይ ይሰራል ተብሎ እቅድ ለተያዘው ዘመናዊ ስታዲየም የአቅሙን ገንዘብ በማበርከት ከማንም በፊት ሀገራዊ ፍቅሩንና ወገናዊ አክብሮቱን ገልጿል፣ ህላፊነቱን ተወጥቷል።

2 ሌላው በደግነት የሚታወቅበት ክፋት የሌለባቸው የድሬዳዋ ህዝብ ባልታሰበ ስአትና ጊዜ በወርሀ ክረምት 1998 ዓ.ም በደረሰባቸው የጎርፍ አደጋ ለሚደረግላቸው የመልሶ ማቋቋም ቴሌቶን ላይ እንደ ሁሌው ከማንም በፊት የተሰማውን ከባድ ሀዘን በመግለፅ ያለውን ገንዘብ ሳይሰስት አበርክቷል። በወቅቱም ድሬዳዋ ድረስ በመጓዝ በችግር ላይ የነበረውን ህዝብ አጽናንቷል።

3 በሚኖርባት ርዕሰ መዲናችን አዲስ አበባ ውስጥ የሚኖሩ የጎዳና ልጆችን በገንዘብ በመርዳት አይዞአችሁ ከጎናችሁ ነኝ የሚል ስር የሰደደ ወገናዊ ፍቅሩን አሳይቷል።

4 ክብርት ዶ/ር ወ/ሮ አበበች ጎበና ለሚያደርጉ በጎ አድራጎት ትልቅ ወገናዊ ፍቅር አለኝ የሚለው ቴዲ ቸርና ወገናዊ እጁን በመዘርጋትና በተደጋጋሚ ድርጅታቸውን በመጎብኘት በርካታ ብሮችን ለግሷቸዋል። ክብርት ዶ/ር ወ/ሮ አበበች ጎበናም ለዚሁ ታላቅ ገራገር አርቲስት ያላቸውን ክብር ከገለጹለት በኋላ እያረጀሁና አቅሜ እየደከመ ስለሆነ ድርጅቱን ተረከበኝ ሲሉ የክብር ደብዳቤ ፅፈውለታል።

5 በፈጣሪ የተሰጠውን ጥበብ በመጠቀም ዜማና ግጥም ለብዙ ጀማሪና ታዋቂ ዘፋኞች አበርክቶላቸዋል። ዜማና ግጥምን ከመስጠቱ ባሻገር ገንዘብን በመደጎም ብሎም ዜማን በማስጠናት የብዙዎቹ ባለውለተኛ ነው።

በአጠቃላይ የቴዲ አፍሮ እጅግ በርካታ የደግነት መለኪያዎች በዝርዝር መጥቀስ እጅግ ይከብዳል።

## ቴዲ አፍሮ ሲነበብ

- ሳቂታና ጨዋታን አዋቂ
- ትሁትና ሰውን አክባሪ
- ጨዋና ዝምተኛ
- የዋህና አዛኝ
- ለፍቅር ተሸናፊ
- ሐሜትን የማይወድ
- ቅንነትን አብዝቶ የሚሻ
- ትዕቢትና ኩራት የሌለበት
- ላመነበት መስዋት የሚሆን
- ሰዎችን በእኩል ዓይን የሚመለከት
- መሆን ያሰበትን የሚሆን
- ሰፊ የትዕግስት ባለቤት የሆነ
- ከመናገር መስማትን የሚመርጥ . . .





# 12

# ቴዲና ኮንሰርቶቹ

‹‹ከድርን አትርሱ››

ቴዲ አፍሮ

## ጅማ 2000

የሚሊኒየም ዋዜማ ቀን በአዲስ አበባ ስቴዲየም በአሉን ምክንያት በማድረግ የሙዚቃ ኮንሰርት ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ በዚያ ኮንሰርት ላይ በርካታ ህዝብ ታድመዋል፡፡ ቴዲ ወደ ጅማ ከማምራቱ በፊት በስቴዲየም የተሰበሰበውን ህዝብ ለማዝናናት ወደ አበበ ቢቂላ ስቴዲየም አምርቶ ነበር፡፡ በወቅቱ ቦታ ቦታውን ይዞ ተቀምጦ የነበረው ህዝብ ከተቀመጠበት በመነሳት ከሌሎች ዘፋኞች በተለየና በሚገርም ሁኔታ ለቴዲ ታላቅ አቀባበል አደረገለት፡፡ ቴዲም ህዝቡ ከሆነለትና ከማንም በላይ የላቀ ፍቅር ሲያሳየው ይህ የዝናዬ መጠን ነው ብሎ ሳይኮራና ሳይመጻደቅ ልቤ ሆይ!! ትዕቢትና ኩራት እንዳይሰማሽ ይህ ሁሉ የሆነልሽ በእግዚአብሔር ነው!! ብሎ ነበር

ለልቡ ያሳለባት፡፡ በሀገራችን የተከበረው ሚሊኒየም ቀን፣ ለጅማ ህዝብ ልዩ ፌሽታ ነበረች፡፡

የምንወደውና የምናከብረው ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ሲያዝናናቸው ነበር በአሉን ያሳለፈው፡፡ በሙዚቃው ኮንሰርት ላይ ከዛሬ ሃያ አመት በፊት ስለሞተው በጅማ ህዝብ ዘንድ ስለተረሳው ‹‹አብዱል ከድር›› አርቲስቱ ‹‹ከድርን አትርሱ›› ሲል ተማፅኗል፡፡ የጅማ ህዝብ የረሳው አንድ ግለሰብ በዚህ ብላቴና እንደምን ሊታወስ ቻለ?

ቴዲ አፍሮ ለጅማ ሀገር እንግዳ ነበር፡፡ ይህንን ታሪክ በማንሳቱ አርቲስቱ ከጥበቡ ስራው በተጨማሪ ታሪክ አዋቂ እንደሆነ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ባቀረበው የሙዚቃ ኮንሰርት ላይ፣ ለሙዚቃው ታዳሚ ቀለል ያሉ የማነቃቂያ ቃላትና መልዕክቶች ያስተላልፍ ነበር ‹‹….ጅማ›› ‹‹አጋሮ›› እያለ ህዝቡን ያነቃቃ ነበር፡፡ ታዳሚው አፀፋውን በጩኸትና በፉጨት ይመልስ ነበር፡፡ የጅማ ህዝብ ለቴዲ አፍሮ መቼም ቢሆን ከልቡ ሊጠፋ የማይችል ጽኑ ፍቅር እንዳለው በዚያ ኮንሰርት ላይ አሳይተውታል፡፡

*በሰባ ሰባት*

*አንድ እንጀራ ለሰባት*

*እሱንም ምንአልባት*

ብሎ ቴዲ ታዳሚውን ሲመለከት በህዝቡ ላይ የመደንገጥ ባህርይ ይታይ ጀመር፡፡ የዚህ ግጥም ባለቤት ማን እንደሆነ ማሰብ የጀመሩ ይመስላሉ፡፡ ወጣቱ የሙዚቃ አርበኛ ከመዝፈን ባሻገር በህብረተሰቡ ዘንድ የተረሱ ታሪካዊ ነገሮች በማውሳት ታሪክን የሚዘክር የታሪክ አዋቂ ነው፡፡

ለመሆኑ ቴዲን በሚያክል አርቲስት ስሙ የተነሳው ይህ ሰው ማን ይሆን? ከድር ይባላል፡፡ ከድር ከሃብታም ቤተሰብ የተወለደና





በህብረተሰቡ ዘንድ የሚከበርና የሚወደድ ሰው እንደነበረ በወቅቱ የነበሩ የአይን እማኞች ይመሰክራሉ፡፡ እሱና ቤተሰቦቹ የእስልምና ሀይማኖት እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡

ከድርም የቁራን ትምህርትን ልቅም አድርጎ ተምሯል፡፡ ከድር በምቾት ያደገ ነው፡፡ አለባበሱም ጨዋ የሚሰኝ ነበር፡፡ ታይቶ በማይታወቅ ድል ባለ ሰርግ ቆንጂዬ ልጅ አግብቶ ይኖር ነበር፡፡ በስራ ህይወቱ የተዋጣለት ነጋዴ ነበር፡፡ ከድር እድሜውን በሙሉ ያሳለፈው ከዝቅተኛ የገቢ ምንጭ ካለው የህብረተሰብ ክፍል ጋር ነው፡፡ ደሃን ይወዳል፡፡ የተቸገረን አይቶ ማለፍ አይሻም፡፡ ያለውን በማካፈል የሚያምን ገራገር ሰው ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከድር በጅማ ህዝብ ዘንድ የሚታወቀው በፈጣን ግጥም ገጣሚነቱ ነው፡፡ ወጣቱ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ከድርን አስታውሱት ያለው፣ ከድር ወረቀትና ብዕር ሳይፈልግ ስለሰማውና ስለተነገረው ብሎም ስላየው ነገር ሁልጊዜ በግጥም የመናገር ችሎታ ስለነበረው ነው፡፡ ጠንካራ መልክት ያላቸውን ግጥሞች የሚፅፈው ዝቅተኛውን ማህበረሰብ ስለሚወድ ነበር፡፡ ‹‹የግጥም ተሰጦ አለን የምንል የግጥም ፀሀፊዎች እንኳን አንድ ግጥም ፅፎ ለመጨረስ አእምሮአችንን አጨናንቀን፣ የብዕራችንን ቀለም አሟጠንና ብዛት ያላቸው ወረቀቶቻችንን አባክነን ነው›› ይላሉ፡፡ ለዚያውም ላያምርና ላይስብ ይችላል፡፡

ከድር ግን ከዚህ ይለያል፡፡ ስለ ሀገር፣ ስለ ፍቅር፣ ስለ ፖለቲካ ስለ መቻቻል … ወዘተ ስለፈለገው ነገር በተፈጥሮ በተሰጠው ችሎታ በቃሉ የመግጠም ችሎታ ነበረው፡፡

በሚሊኒየም የመጀመሪያ ቀን በጅማ ከተማ በተዘጋጀው ኮንሰርት ላይ ከከተማዋ ነዋሪ በተጨማሪ በአሉን ለማሳለፍ ወደ አገር ቤት የመጡና ከተለያዩ አገራት ወደ ወርቃማዋ ምድር የሔዱ ነበሩ፡፡

እናም በጥበብ ስራዎቹ የብዙዎቹን ቀልብ የመግዛት ኃይል ላለው ለቴዲ የጅማ ህዝብ ለየት ባለ መልኩ ነበር አቀባበል ያደረገለት፡፡ የሙዚቃ ኮንሰርቱ የተካሄደው በስቴዲየም ውስጥ ነበር፡፡

በወቅቱ ጭቃ ቢኖርም ህዝቡ ግን ግልብጥ ብሎ ነበር የወጣው። ቴዲ ህዝቡን ለማዝናናት ወደ መድረክ ሲወጣ የሀገሩን ባንዲራ ተጎናጽፎ ፍቅር ያሸንፋል!! እንዋደድ እያለ በጉልበቱ ተንበርክኮ ወደ ሰማይ አንጋጦ ሲጸልይ ታይቷል። በሺህ አመት አንዴ የሚመጣውን የሚሊኒየም በአል አስመልክቶ በጅማ ህዝብ በተደረገለት ጥሪ መሰረት በአሉን አብሮ በማሳለፉ በጣም ደስተኛ እንደሆነ ቴዲ ተናግሯል። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ የበአል ዝግጅት ላይ የተጣሉትን አስታርቆ ይቅር ለእግዚአብሔር አባብሏቸው ነበር የተመለሰው። ቴዲ በሄደበት ቦታ ሁሉ ሰላምን ለማውረድ ይጥራል። ፀበኞችን ያስታርቃል። አርቲስቱ ዘፋኝ ብቻ ሳይሆን የሰላምንም አስፈላጊነት አበክሮ የሚሰብክ ታላቅ ሰው ነው።

*ቴዲ ሄደለት ለጅማ*

*የተጣላውን ሊያስማማ*

*እርቅ አወረደ በምድሩ*

*እንዲሰመነን እግዜሩ*

*መከራረፍ እንዳላይ*

*ብሎአል እግዜር የበላይ*

*የሰላም ሰው በሄደበት*

*የሰይጣን ስራ ከሸፈበት*

*እንኳንስ ሰው ምድሩም አይረሳው*

*የቴዲማ ስራ ሁሌም ፍቅር ነው*





# የግዮን ሆቴል ኮንሰርት

ህዳር 7 ቀን 2000 ዓ.ም ልዩ ቀን ነበር። ዝነኛው ወጣት የሙዚቃ ፈርጥ ቴዎድሮስ ካሳሁን ከሁለት ዓመት ቆይታ በኋላ ያዘጋጀው የሙዚቃ ኮንሰርት ለአፍቃሪዎቹ የሚያቀርብበት ውድ ዕለት። ቴዲ አፍሮ በስራ ጫና ምክንያት ለሀገሩ ህዝብ በተለይ ደግሞ ለመዲናችን አዲስ አበባ ነዋሪ በግንባር ቀርቦ በቀጥታ ሲዘፍን ከታየ ሰንበትበት ብሎ ነበር።

ቢሆንም ግን ህዳር ወር ላይ በግዮን ባዘጋጀው የሙዚቃ ኮንሰርት ብዙዎቹን አስደስቶ አልፏል። ትኬቱ አራት መቶ ብር ቢሸጥም ተወደደ ብሎ ሲያማርር የተሰማ አንድም ታዳሚ አልነበረም። ኮንሰርቱ በግምት ከአስራ አምስት ቀን በፊት በሬዲዮ ሲተዋወቅ፣ የቴዲን ምስል የያዙ ፖስተሮች በከተማው በተለያዩ ቦታዎች ሲለጠፉ፣ እሰይ ያላለና ያልተደሰተ ማንም አልነበረም።

ምክንያቱም አርቲስቱ ባለበት የጊዜ እጥረት ሳቢያ ከሚወደው ህዝብ በቅርበት በመገናኘት ሊያዝናናቸው አልቻለም። ስለሆነም በዚህ አጋጣሚ ያልተደሰተ የለም። በሙዚቃ ኮንሰርቱ ላይ ለመታደም ከመዲናችን አዲስ አበባ በተጨማሪ ከተለያዩ የሀገራችን ክልሎች በርካታ ሰዎች መጥተው ነበር።

በዚህ የሙዚቃ ኮንሰርት ላይ የቴዲ የልፋት ውጤት ታይቶበታል። ዝግጅቱ ሊጀመር ገና ብዙ ሰዓታት ሲቀረው ነበር ታዳሚው ካለው ከፍተኛ ጉጉት የተነሳ ወደ ግዮን ሆቴል ያመራው።

እኔን ጨምሮ ብዙ ሰዎች ባዳራሹ ተቀምጠን ሳለ ወጣቱ የሙዚቃ አርበኛ መድረኩን የሚረግጥበትን ሰዓት በጉጉት እንጠብቅ ጀመር። ከምሽቱ 1፡15 ገደማ የምንወደውና የምናከብረው ምትክ የለሽ ቴዲ አፍሮ ብርድን የሚከላከል ባለ ኮፊያ ልብሱን ለብሶ መድረክ ላይ ብቅ አለ። ቴዲ በእለቱ ዘፋኝ ብቻ አልነበረም። የራሱ ባንድ ከሆኑት የሙዚቃ ባለሙያዎች ጋር የድምፅ ችግር

በማስተካከልና የመድረክ መብራቱን ቼክ በማድረግ ሲያረጋግጥ ተስተውሏል፡፡ ስመድረክ ዝግጅቶቹ የሚገባውን ሁሉ አድርገው ከጨረሱ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ የቴዲ ባንዶች የቅኝት ፍተሻ አደረጉ፡፡ ታዳሚው በአፀፋው በፉጨትና በጭብጨባ ገለፀ፡፡

በዚህ መሃል ቴዲ አፍሮ ለተወሰኑ ለዓታት ከመድረክ ጠፋ፡፡ ምንም እንኳን ቴዲ ከመድረክ ቢሰይም ወላጅ እናቱ አርቲስት ጥላዬ አራጌ ባዘጋጀችው የፋሽን ትርኢት ስንዝናና ቆየን፡፡ በየመሃሉ ለመንፈስ ምግብ የሚሆኑ ምርጥ ዘፈኖች በዲጄዎች አማካኝነት እየሰማን ነበር፡፡ ለኮንሰርቱ የተዘጋጀው ስፍራ ለህዝብ ስለጠበበ እጅግ በርካታ ሰው የዝግጅቱ ታዳሚ ለመሆን ሳይታደል ወደ ቤቱ ተመልሷል፡፡ በሙዚቃው አዳራሽ የነበርን እንኳን ተጠጋግተን ተፋፍገን ነበር የተቀመጥነው፡፡

ሰዓቱ ገሰገሰ፡፡ 3:20 ሲሆን አቡጊዳ የሙዚቃ ባንዱ አባላት ሙሉ ጥቁር ሱፍ ለብሰው ቦታ ቦታቸውን ያዙ፡፡ ህዝቡም ‹‹ቴዲ›› እያለ ጩኸቱን ማሰማት ቀጠለ፡፡ ቴዲም ቢሆን ጥሪውን አክብሮ ብቅ አለ፡፡ ‹‹ሰላም ነው›› ብሎ ለህዝቡ ሲጠይቅ ህዝቡም ከተቀመጠበት ተነስቶ በማጨብጨብ ‹‹አዎ ሰላም ነው›› እያለ መልሱን ሰጠ፡፡ ቴዲም በቀጥታ ሙዚቃ መጫወቱን ቀጠለ፡፡ በየመሀከሉ ምክር አዘል መልዕክት ያስተላልፍ ነበር፡፡

## የመድረክ ሁኔታ

መድረኩ ለተመልካች የሚማርክ ከመሆኑም በላይ ለድምፃዊያኑ እንቅስቃሴ የሚመች ሰፊ ነበር፡፡ የመድረኩ ከፍታ ከፍ ያለ በመሆኑ ተመልካቹ እንደልቡ እንዲያይ አስችሎታል፡፡ የመድረኩ ስፋት በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የታየ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ይህም በመሆኑ ስድስቱን የሙዚቃ ተጫዋቾች፣ ሁለት ተወዛዋዦችና ድምፃዊው እንደልባቸው እንዲንቀሳቀሱ ረድቷቸዋል፡፡





በመድረክም ላይ የሚበራው የብርሃን መጠን ለአይን የሚስማማና ቀለማቱም የሚማርክ ነበር፡፡

## ድምፅ

ብዙ ጊዜ በሀገራችን በሚዘጋጁ ኮንሰርቶች ላይ እንደዋና ችግር የሚነሳው የድምፅ ችግር ነው፡፡ ምክንያቱም የድምፅ ችግር እውቀት ያላቸው ጥቂቶች ስለሆኑ ነው፡፡ በቴዲ አፍሮ የሙዚቃ ዝግጅት ላይ ግን ምንም አይነት የድምፅ ችግር አልታየም፡፡ ለመሳሪያውም ሆነ ለማይኩ በትክክል የድምፅ ክፍፍል ተደርጎላቸዋል፡፡ በዚህ ኮንሰርት ላይ የታየው የመድረክ ድምፅ ከቫይረስ ነፃ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ኮንሰርት ሲዘጋጅ በድምፅ ችግር ሙዚቃው ተቋርጦ ባንዱ ስራውን አቁሞ ገመድ ሲቀጣጥሉ ይታዩ ነበር፡፡ በቴዲ ኮንሰርት ላይ ግን ይህ እንከን አልታየም፡፡ የድምፅን አጠቃላይ ክፍፍል ሁኔታ በዚህ ሙያ የሰለጠኑ ባለሙያዎች በሚገባ የስራ ድርሻቸውን ተወጥተዋል፡፡

## ቴዲና ያቺ ቀን

ቴዲ በሀገሩ ላይ ከሁለት ዓመት ቆይታ በኋላ ያዘጋጀው የሙዚቃ ኮንሰርት እንደመሆኑ መጠን ዳግም የተወለደ ያህል ነበር የቆጠረው፡፡ ‹‹ከወገኔ ጋር በፍቅር ያሳለፍኩት ልዩ ቀን›› ሲል ገልፆታል፡፡ ስለሆነም ህዳር 7 ቀን 2000ዓ.ም ቴዲ አፍሮ በአዲስ አበባ ታሪክ የሰራበት ቀን ነበረች፡፡ በዚህ ዝግጅት ላይ የድምፃዊው ከፍተኛ የሆነ የጥረት ውጤት ታይቶበታል፡፡ የላቀ የጥበብ ስራ ያቀረበ ታላቅ አርቲስት ነው፡፡

በእለቱ በርካታ ዘፈኖችን ዘፍኗል፡፡ የአዘፋፈኑም ስልት ታዳሚውን በደስታ አስፈንድቆታል፡፡ የሚጠበቅበትንም ከበቂ በላይ

አሟልቶ ተገኝቷል። በሙዚቃውም መሀል የሙዚቃ ተጫዋቾቹን ስም በመጥራትና በማነቃቃት ከህዝብ ጋር ያስተዋውቃቸው ነበር። ቴዲ እኔ ብቻ ልታወቅ የሚል የራስ ወዳድነት ስሜት የሌለው እና የሌላውን ሰው እድገት የሚመኝ ቅን አርቲስት ነው።

## የኮንሰርቱ ልዩ ዓላማ

‹‹ገንዘብ የሰው ልጆች ባሪያ ነው›› የሚለው ወጣቱ ድምፃዊ ለገንዘብ ሲል ስራን አይሰራም። ስለገንዘብ ብዙም አይጨነቅም። ቴዲ ገንዘብ ፈልጎ ሳይሆን ገንዘብ እራሱ ቴዲን ፈልጎት ነው የሚመጣው። ‹‹ብር ተራ ወረቀት ነው። የሰው ልጅ ግን ክብር ፍጡር ነው›› የሚለው ቴዲ በግዮን ሆቴል ኮንሰርቱን ያዘጋጀው በሁለት መሰረታዊ ነጥቦች ነው።

የመጀመሪያው ለብዙ ጊዜ ግንባር ለግንባር እየተያየ ከወገኑ ጋር የሙዚቃ ዝግጅት ከሰራ ሁለት ዓመታትን ስላስቆጠረ አድናቂዎቹን በቅርበት አግኝቶ እነሱን ለማስደሰት ሲል ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በዚህ የሙዚቃ ኮንሰርት የሚገኘው ገንዘብ ለክብርት ዶክተር ለወ/ሮ አበበች ጎበና ህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ለማበርከት ነው። ቴዲ አፍሮ ክብርት ዶክተር ወ/ሮ አበበች ጎበና ለሚያሳዩት ወገናዊ ፍቅር ‹‹ኪዳናዊ እናት›› የሚል ፅሁፍና ፊርማው የሰፈረበት የወርቅ ሜዳሊያ አበርክቶላቸዋል። ቴዲ አፍሮ ከዚያ በፊትም ለድርጅቱ በርካታ የገንዘብ ድጎማ ችሮአል።

ከዚህ አንጻር አንቱ የተባሉ የሀገራችን ባለ ሀብቶች የዜግነት ግዴታቸውን ሙሉ በሙሉ ገና አልተወጡም ማለት ይቻላል። ይህ ወጣት ድምፃዊ ግን የሚያከለውና የሚወዳደረው የጠፋ ታላቅ የወገን ፍቅር ያደረበት ብቸኛ አርቲስት ነው። ወ/ሮ አበበች ጎበና ስለአርቲስቱ ብስለትና ለወገኑ ካለው ወሰን የለሽ የጋለ ፍቅር የተነሳ ‹‹እኔ አቅሜ እየደከመ ስለሆነ ልጆቼን ተረከበኝ›› ሲሉ ደብዳቤ ፅፈውለታል። ቴዲ ኪሴን ሳዳብር፣ ልብሳበት፣ ልጠጣበት ብሎ





ሳያስብ ላቡን ጠብ አድርጎ ያገኘውን ሃብት ለወገኖቹ መልሶ ያበረክታል። የዚህ አርቲስት መፈጠር ከጥበብ ስራ ውጪ የሚያደርጋቸው በጎ ተግባራት ለበጎ ነው ያስብላሉ። ይህ ገራገርና የዘመኑ ምርጥ አርቲስት በሚያደርገውና በሚተገብራቸው መልካም ስራዎቹ ህፃን፣ አዋቂ፣ ዘርና ጾታ ሳይለይ በሁሉም ኢትዮጵያዊ አድናቂዎቹ የብሔራዊ መዝሙር ያክል ስሙን ዘወትር ሲያወድሱት ይሰማል።

## *ሙዚቃን በቴዲ*

መድረኩን ሲረግጥ ማይኩን ጨብጦ
ቀና ብሎ ያየዋል እልፍ ሰው አንጋጦ
በተሰጠው ግርማ ሞገስ ፍጥረታቱ ተገርሞ
መዝፈንማ ሲጀምር በመረዋ ድምጹ ዜማን ሲቀኝው
"የሱስ ልዩ ነው" ይላል ህዝበ-አዳም እየገረመው
በዚህ ብላቴና በዚህ ጀግና አንድ ለናቱ
ቀን ከሌሊት ሙዚቃን አለመ ምድር ፍጥረታቱ
አዎን፣
በመረዋ ድምጹ ቅኔን ሲቀኝ ሰምተን ተደንቀናል
ማመን እስኪያቅተን ሳንተኛ ቃዥተናል
በፍጹም ደስታ በታላቅ እርካታ ሀሴት አድርገናል
ብለንም መስክረናል
"እየናት ቀመስናት ወደን አጣጣምናት
ሙዚቃን በቴዲ ከልብ አፈቀርናት!"

*ቴዲ አፍሮ ጎልቶ የሚታወቅባቸው ጥቂት ነጥቦች፡-*

1. አንደበተ ርቱዕ፣ ንግግሮቹ አስገራሚና መሳጭ
2. ለሃገሩና ለወገኑ ፅኑ ፍቅር ያለው
3. የዕውቀት አድማሱ የሰፋ
4. በአልባሌ ቦታ የማይገኝ
5. ላመነበት ነገር መስዋእትነትን የሚከፍል
6. የህግን የበላይነት የሚያከብር
7. ያለውን በማካፈልና የተቸገረን በመርዳት የሚያምን
8. ለጎዳና ልጆች ፅኑ ፍቅር ያለውና ለችግራቸውየሚደርስ
9. የሀገሩን የሙዚቃ እድገት በላቀ ደረጃ የሰወጠ. . .





# ክፍል ሦስት

## ቴዲ ከማንም አርቲስት ልቆ የከበረ አክሊል እንዲደፋ ያደረጉ ታላላቅ እውነታዎች

13

### ሙዚቃ ያኔና ዘንድሮ

ማንም ሰው ከተወለደበት ጊዜ እንስቶ አንድ አይነት ሙዚቃ መስማቱ አይቀርም። ምናልባትም ወላጅ እናታችን እንቅልፍ እንዲወስደን እሹሩሩ እያለች አዚማልን ይሆናል። እድሜያችን እየገፋ ሲሄድ ግን ለመንፈሳችን የሚስማማ ለነፍሳችን የሚሆን ሙዚቃ መምረጣችን አይቀርም። ሙሉ ጊዜያችንን በስራ ተጠምደን ውለን ወደ ቤታችን ስንመለስ ወይም መኪና ስናሽከረክር በመረጥነው ሙዚቃ ዘና ማለታችን አይቀርም።

የዘፈን ግጥም ብዙ ነገርን የያዘ ነው፡፡ ሙዚቃ በሁሉም ህብረተሰብ ውስጥ እንዲናኝ ካደረጉት ዋና ምክንያቶች መካከል አንዱ በሰዎች ጤንነትና ደህንነት ላይ በጎ ተፅዕኖ በማሳደሩ ነው፡፡ ሙዚቃ ለህመም ማስታገሻ ዋና መፍትሄ ነው፡፡ ሐኪሞች በጭንቀት ለሚሰቃዩ ህመምተኞች ለስለስ ያለ ሙዚቃዎችን እንዲሰሙ ይመክራሉ፡፡ እነኚህ ሙዚቃዎች ደግሞ ለህመምተኛው እንደ መነቃቂያ ሆነው ሊረዱ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ሆስፒታሎች ውስጥ ልዩ ህክምናና ክትትል በሚሰጥበት ክፍል ውስጥ ሳይቀር ሙዚቃ እንዲከፈት ይደረጋል፡፡ ሙዚቃ ለውነትን ዘና በማድረግ በምጥና በወሊድ ጊዜ የሚፈጠረውን ውጥረት ለመቀነስ ያግዛል፡፡

አዎ፣ ሙዚቃ ልዩ፣ ረቂቅና ሀይለኛ ነው፡፡ ያረጋጋል፡፡ ያዝናናል፡፡ ሊያስተምረንና መንፈሳችንን ሊያድሰን የሚችል ሞገደኛ ነው፡፡ ደስታችንንም ሆነ ሀዘናችንን ለመግለፅ ያስችለናል፡፡ ጥንትም ሆነ በአሁኗ ሰዓት የምንሰማቸው ሙዚቃዎች በሰው ልጅ ልብ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡

ሙዚቃ የሠው ልጆች የደስታ ምንጭ ናት፡፡ ስንከፋ የምንፅናናባት፣ ስንደሰት የምንረካባት፣ የውስጥ ስሜታችንን የምንገልፅባት .እንደሙዚቃ ያለ ምንም ነገር የለም፡፡ ሰዎች ፍቅራቸውን ለመግለፅ፣ የውስጣቸውን ሀሳብ ለመተንፈስ በግንባር ቀደምትነት ሙዚቃን ይመርጡዋታል፡፡ የሰው ልጆች ለሙዚቃ ያላቸው ፍቅር እንዲህ በቀላሉ የሚገመት ሳይሆን ስር የሰደደ ጥምረት ነው፡፡

በእርግጥም ጥበብ የፈጣሪ ስጦታ ነች፡፡ ስለጥበብ ስናነሳ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ ጥበበኛ ሆኖ የምናገኘው ጠቢቡ ሰለሞን ነው፡፡

ሰለሞን በህይወት ዘመኑ ከፈጣሪው በተሰጠው የጥበብ ችሎታ ስራውና እንቅስቃሴው ሁሉ በጥበብ ነበር፡፡ የአገራችን የዜማ ደራሲ ቅዱስ ያሬድ ከዘላለም አባቱ በተሰጠው የጥበብ ችሎታ ግዕዝ





እዝልና አራራይ የሚሉትን የዜማ ክፍሎች ቀምሯል፡፡ ‹‹ጥበብ ከእግዚአብሔር ነች፡፡ የጥበብ ባለቤት እርሱ ብቻ ነው፡፡ ጥበብን ፈልጓት ታገኟታላችሁማል›› ይላል፡፡ በቅዱስ ያሬድ የተቀመረው የዜማ በር በአገራችን ላለው ለማንኛውም ዘፈንም ሆነ ዝማሬ ዋነኛ ምንጭ እንደሆነ ይነገራል፡፡

የሀገራችን ኢትዮጲያ የሙዚቃ እድገት ስንመለከት በርካታ ጥበብ ያፈራቻቸው ጥበበኞች ለሙዚቃው እድገት ታላቅ ዋጋ እንደከፈሉ እንረዳለን፡፡ ምንም እንኳን የሠው ልጅ ህልውና ግዴታ ሆኖ ይህችን አለም ለአንዴና ለመጨረሻ በሞት ቢለዩዋትም በህይወት ዘመናቸው የሰሩት የጥበብ ውጤት አሻራው ለዘላለም ላይጠፋ ክትውልድ እስክ ትውልድ እየተወራረሰ ሲተላለፍ መዘከሩ አይቀሬ ነው፡፡

“ማንኛውም ሰው ሲፈጠር ለአንድ አላማ ተፈጠረ እንጂ ለከንቱ ወደዚች አለም አልመጣም፡፡” እያንዳንዱ የሠው ልጅ በፈጣሪው የተሠጠው የራሱ የሆነ የመክሊት ባለቤት ነው፡፡ በመሆኑም ያለምንም ክፍያ በነፃ የተሠጠውን ፀጋ መጠቀምና ታሪክ ሰርቶ መገኘት የሰውየው ወይም የግለሰቡ ወሳኝ ድርሻ ይሆናል፡፡

እድሜና ጤና ተችረው ለምስክርነት የበቁ ብዙ አንጋፋ የሙዚቃ ሰዎች ስለሀገራችን የሙዚቃ ያለፈ ታሪክና ስላሳለፉት አንገፍጋፊ የፈተና መንገድ በእልህ፣ በቁጭትና በምሬት ሲናገሩ ይሰማል፡፡ እርግጥ ነው ተደባብቆም ሆነ ተለባብሶ ሊታለፍ የሚችል አይደለም፡፡ በቀደሙት ዘመናት የነበረው የሙዚቀኞች ህይወት እንደምንሰማው ታሪክም እንደሚያስረዳን ክሆነ እምብዛም ደስታና ምቾች የሌለበት ከመሆኑም በላይ በህዝብ የነበራቸው የተቀባይነትም መጠን አሳዛኝ ነበር፡፡

ተፈጥሮ የቸረቻቸውን ውብና ማራኪ ድምጽ ይዘው ለጥበብ እድገትና ፍቅር በሚያቀነቅኑበት ጊዜ ሞራል በሚነካና ተስፋ አስቆራጭ በሆነ አኳኋን ይዘለፉ ነበር፡፡ ለጆሮ የሚቀፍ በርካታ

የስድብና የንቀት ውርጅብኝ ይዘንብባቸው እንደነበረ የሚዘነጋ ታሪክ አይደለም፡፡ ለጋብቻም ሆነ ለፍቅር አጋርነት በሌላው ማሕበረሰብ ዘንድ ተፈላጊነታቸው እምብዛም ነበር፡፡ ይህ የሆነው በወቅቱ ለሙዚቃ ያለው ግንዛቤ አናሳ የነበረ በመሆኑ ነው፡፡

ሆኖም በውስጣቸው ላለው የጥበብ ፍቅር ሲሉ ስድብና ግልምጫ ሳይበግራቸው መገፋትና መገለል ሳያንበረክካቸው ያንን የመሰለ አስቸጋሪና አሳዛኝ የሕይወት ውጣ ውረድ አልፈው ሙዚቃን ዛሬ ላለችበት የገነነ ክብር ሊያበቋት ችለዋል፡፡ ቀደምት ኢትዮጲያዊ ዘፋኖች፣ ሙዚቃኞች፣ ደራሲና የዜማ ቀማሪዎች እንደብሄራዊ መዝሙር በየአደባባዩ ጥበብን ለዘመሩ በህይወትም ላሉት ይሁን በህይወት ለሌሉት ምስጋና ይድረሳቸው፡፡

ከ1950ዎቹ እስከ 1970ዎቹ ዓ.ም አካባቢ የሀገራችን የሙዚቃ እድገትን መለስ ብለን ስናጤን መልካም እንቅስቃሴና አበረታች ሁኔታ የሚታይበት ታላቅ የሙዚቃ ዘመን ነበር ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ ህዝቡም ቢሆን የሙዚቃን ሀያልነት ገብቶት ለዘፈንም ሆነ ለዘፋኞች ጥሩ ክብር መስጠት የጀመረበት ጊዜ ነበር፡፡

ጊዜ ጊዜን ይሽረዋል፡፡ ትውልድንም ትውልድ ይተከዋል፡፡ የሠዎችም የአስተሳሰባቸው አድማስ አይደለም በቀናት ልዩነት በሠአታት ውስጥም ደርጅቶ ታላቅ ለውጥ የሚታይበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ እናም ሙዚቃ አንሰማም ዘፋኝንም በአይናችን አያሳየን የሚሉ ወግ አጥባቂዎች ሁሉ የሙዚቃ ጥበብ በደም ስራቸው ገብታ ደንዳና ልባቸውን በማንበረከክ ሙዚቃ ራሷ ሀያልነቷን አስመስክራለች፡፡

ሙዚቃ ሀያልነቷን አስመስክራ ገንና ለመውጣትና ዛሬ ለደረሰችበት ክብር የበቃችው ስንትና ስንት መስዋዕትነት ተከፍሎባት ነው፡፡ ጊዜ ጀግና ነው፡፡ ሁሉም ነገር ለማከናወን የጊዜ ድርሻ ትልቁን ቦታ ይይዛል፡፡ ጊዜ የጣለውን ጊዜ ያነሳዋል፡፡

አሁን ሁሉ ነገር ተገለባብጦ የሰውም የአስተሳሰብ ደረጃ ከፍ





በማለቱና እያደገ በመምጣቱ የተነሳ የተናቀው ዘፈን ከቀን ወደ ቀን ከጊዜ ወደ ጊዜ ተቀባይነትን ከማግኘት አልፎ የክብር መገለጫ እስከመሆን ደርሷል፡፡ ዘፈንና ዘፋኝን የሁሉም ሰው የእለት ተእለት ፍላጎት ሆኖ መታየት ጀምሯል፡፡

ጥላሁን ገሰሰ፣ ታምራት ሞላ፣ መሀሙድ አህመድ፣ ዓለማየሁ እሸቴ፣ ነዋይ ደበበ፣ ቴዎድሮስ ታደሰና ሌሎች አንጋፋና ወጣት የሙዚቃ ባለሙያዎች ለሀገራችን ዘመናዊ የሙዚቃ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡

በእያንዳንዱ ትውልድ ውስጥ ጀግና እንደሚፈጠር ሁሉ የሙዚቃ ጀግኖችም የጥበብን እንባ አንብተው አይሆኑ ሆነው ለዚህ ለአሁኑ ታላቅ ክብር አብቅተዋታል፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ ብዙዎችም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንደሚናገሩት ከሆነ በኢትዮጲያ የሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ከቀደምት ከያንያን የጥበብን ዱላ የተረከቡት ጥቂት ድምፃዊያን ናቸው፡፡ ታላቁ የሙዚቃ ንጉስ ክቡር አርቲስት ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ በሀገራችን ኢትዮጲያ ምድር ላይ ያሳረፈውና ጥሎት ያለፈውን የሙዚቃ አሻራ ከቃል በላይ ነው፡፡

መቼም ቢሆን የማይረሳና ለአፍታ እንኳን ሊዘነጋ የማይችል ታላቅ የታሪክ ሠው ነው፡፡ ከክቡር አርቲስት ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ ቀጥሎ የተፈጠረው ድምፃዊ ሙሉቀን መለስም ለሀገሩ የሙዚቃ እድገት ቀላል የማይባል የጥበብ ስራን ሰርቷል፡፡ ሙሉቀን መለሰ በርካታ ቁም ነገር ያዘሉ የዘፈን ግጥሞችን በመጫወት ለሀገሩ ትልቅ የሙዚቃን በረከት ያበረከተ ጥበበኛ ሠው ነው፡፡ ከዘመን ወደ ዘመን ተሻጋሪ በሆኑ የማይሰለቹ ጣዕመ-ዜማዎቹ በርካታ አድናቂዎችን ለማትረፍ ከመብቃቱም በላይ ለህዝብ ካበረከታቸው የዘፈን አልበሞች አንዳቸውም ሜዳ ላይ ሳይወድቁበት ሁሌ አዲስ ሆነው እስከ አሁኗ ሠዐት እየተደመጡለት ይገኛሉ፡፡

ሌላው የዚህ ዘመን የሙዚቃ ፈርጥና አርበኛ ለሙዚቃና ለጥበብ እድገት በለጋነት እድሜው ወገቡን ታጥቆ የተነሳውን ወጣቱ

ታላቅ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮን እናገኛለን። ስለ ቴዲ በተደጋጋሚ ብዙ ነገር ሲነገር፣ ሲወራ፣ ሲፃፍና ሲተረክ ማየት መስማትና አለፎም መገረም ዘወትር አዲስ ክስተት ነው።

ቴዲ አፍሮ በ1993 ዓ.ም አቡጊዳ የተሠኘውን አልበሙ ለህዝብ ጆሮ ሲደርስ ጥበብም ታላቅ በሯን ወለል አድርጋ ከፍታለት ልጇ እንኳን ደህና መጣህ በሚል ነበር በፀጋ የተቀበለችው። በወላጅ እናትና አባቱ ወደ ሙዚቃ አለም እንዳይገባ መከልከሉ፣ ከእርሱ በፊት በነበሩ ዘፋኞች እርሱ ቴዲ ዘፈን እያቻለ አትዘፍንም መባሉ፣ በጥቂቶች ሰዎች ፊት መነሳቱ ሳይበግው፣ ፊት መነሳቱ ሳያስከፋው፣ መድረክ መነፈጉ ተስፋ ሳያስቆረጠው የልቡን ሀሳብና ረጅም ትልቅ ምኞቱን ለፈጣሪው በመንገር ህልሙን ያሳካው ቴዲ ሲወርድ ሲዋርድ የመጣውን የዘፈን ምርኩዝ ዱላ ተቀብሎ በመዳፉ ከጨበጠው ጊዜ አንስቶ በሀገራችን ምድር ላይ ታላቅ የዘፈን አብዮት ከመፈንዳቱም በተጨማሪ ሙዚቃ የሁሉም ሠው ምርጫ እስከመሆን ደርሶ ታይቷል።

ቴዲ አፍሮ ከአንጋፋዎቹ የቀድሞ ዘፋኞች በተለይም ከክቡር አርቲስት ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ የተቀበለውን የታላቅነት ዱላ በተሻለና በገዘፈ መልኩ አሻሽሎ በመስራቱ ለብዙሀኑ ህዝብ አስደናቂ ክስተት ሆኗል። የሙዚቃን እድገት በታላቅ እመርታ ያሳደገ ከመሆኑም በላይ ለብዙ ዘፋኞች ሞዴል ሆኖ የታየ አንድና ብሳኝ አርቲስት ነው።

ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ወደ ሙዚቃ ዓለም ብቅ ካለበት ጊዜ ወዲህ ሙዚቃ በልዩ ሁኔታ ላቅ ያለ ትኩረትና ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚታፈስበት ለመሆን ችሏል። የዚህ ወጣት ድምፃዊ የጥበብ ስራዎች በከፍተኛ ደረጃ የቅዱስ ያሬድን የዜማ ስልት ስለሚያስታውሱም የላቀ ክብር ለመጎናፀፍ በቅቷል። ሙዚቃ አሁን ላለችበት ከፍታ እንድትበቃ ትልቁን ሚና የተጫወተው የቴዲ ወደ ሙዚቃው ዓለም መቀላቀል ነው።

ቴዲ አፍሮ በጥበባዊ ክህሎቱ ህዝብና ወገኑን ለማገልገል





ቆርጦ የተነሳ ጥበበኛ አርቲስት በመሆኑ በህብረተሰቡ ዘንድ የሙዚቃን ታላቅነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ተመስክሯል። በቀደሙት ዘመናት አንድ ሙሉ አልበም ቢበዛ እስከ አንድ ሺህ ብር ድረስ ይሸጥ ነበር። ከዚያ ወደ መቶ ሺህ ብሮች አደገ። ዛሬ ግን ወደ ሚሊዮኖች እየገሰገሰ ነው። ይህ የሆነው ደግሞ በቴዲ የተነሳ ነው። የሀገራችን ዘፋኞች በአሁኑ ሰዓት ለየት ያለ ትኩረት ከማግኘታቸውም በላይ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚሰጣቸው ክብር ሰማይ ጠቀስ ሆኗል። ሙዚቃ በድሮና ዘንድሮ መካከል ያላት ልዩነት የሰማይና የምድር ያክል ሆሰፋ እንዲሆን ያስቻለው ደግሞ ቴዲ አፍሮ ስለመሆኑ ምንም ጥያቄ አያሻውም።

አዎን ቴዲ አፍሮ በሙዚቃ ህይወት ስር ነቀል ለውጥን ያመጣ ውድ አርቲስት ነው። በዚህም የሕዝብ ስስት እስከመሆን ደርሷል። የቴዲ አድናቂዎች በሚለብሱት ልብስ፣ በቁልፍ ማንጠልጠያቸው ላይ፣ በመኖሪያ ቤታቸው ግድግዳ ላይ፣ በታክሲ ውስጥና በቤት አውቶሞቢል ተሽከርካሪዎች ላይ፣ በየቦታው፣ በየመዝናኛውና በየትኛቸውም ስፍራዎች ተዘውታሪ በሆነ መልኩ ፎቶዎቹ በኢትዮጲያ ሰንደቅ አላማ ህብረ ቀለማት አሸብርቀው ተንጠልጥለው ወይም ተለጥፈው ማየት የተለመደ ሆኗል። በሀገራችን ኢትዮጲያ በርካታ ድንቅ ዘፋኞች ተፈጥረው ለታላቅ ዝናና ክብር በቅተዋል። ሆኖም ማንም በአጭርና በውስን አመታት ጊዜ ውስጥ እንደቴዲ አፍሮ ገኖ የወጣና በህዝብ ዘንድ የላቀ የክብር አክሲል የተቀዳጀና ፍቅር የተቸረው ዘፋኝ አለ ብሎ ማሰብ ይከብዳል። ወደፊት መፈጠሩም ያጠራጥራል።

ቴዲ አፍሮ አሁን ላለው ትውልድ በተለይም ለአድናቂዎቹ ክብርቅነት አልፎ በጥበብ ዘርፍ ውስጥ በተለይም በሙዚቃ ዓለም ላይ ለናሙና የተፈጠረ ታላቅ የጥበብ ሊቅ ነው።

ብዙዎች የሚገረሙበት፣ ሚሊዮኖች በተደጋጋሚ የሚያደንቁትና ፍቅራቸውን የሚገልፁለት፣ እልፎች በሚሰራቸው የዘፈን ስራዎቹ ከልብ የሚወዱት የስስት ሀብታቸው ነው። ቴዲ

ወደሙዚቃው አለም ከተቀላቀለበት ጊዜ ጀምሮ ለረጅም አመታት የመገናኛ ብዙሃንን ትኩረት ለመሳብ የቻለ፤ የጋዜጠኞችን ብዕር ዘወትር የሚቀሰቅስ፤ ከወገኑ ህበሻዊ ዘር አልፎ በውጪ ዜጎች ጭምር ለመወደድና ለመወደስ የበቃ በኢትዮጲያ የዘፈን ታሪክ ውስጥ ትልቅ የታሪክ ምዕራፍ የከፈተ ብርቅዬ ከያኒ ነው፡፡

አንጋፋውም ክቡር አርቲስት ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ በህይወት እያለ ለዚህ ወጣት ድምፃዊ በአንድ ወቅት እንዲህ ሲል ነበር የምስክርነት ቃሉን ይፋ ያደገረው፡፡ ‹‹በህይወት እያለሁ አይኔን በአይኔ አይቻለሁ፡፡ ቴዲ ጠንካራ ዘፋኝ ነው፡፡ የሚሰራንም ነገር ጠንቅቆ የሚያውቅ ብልህ ልጅ ነው፡፡ የማይረባና ተልካሻ ቦታ አይገኝም፡፡ ገና ወደፊትም አሁን ከሰራው ስራ በላይ እንደሚሰራ አምንበታለሁ፡፡ በሚሰራውም የሙዚቃ ስራ ኮርቼበታለሁ›› ሲል ያለውን የክብር አድናቆት ተናግሮ ነበር፡፡

ቴዲ አፍሮ ከክቡር አርቲስት ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠና ከሌሎች አንጋፋ ዘፋኞች የተረከበውን የዘፈን ዱላ በሚገባ ምርኩዝ አድርጎ እውነተኛ ዘፋኝነቱን ያስመሰከረ ብርቅና ድንቅ ኢትዮጲያዊ አርቲስት ነው፡፡





# “ቴዲ መምህሬ”

ሙዚቃን ያሳወቀኝ

ጥበብ ቅኔን ያስተማረኝ

ያለውን ያካፈለኝ

እንካ ብሎ ያለስስት የሰጠኝ

ቴዲ እኮ ነው የጥበብ መምህሬ

ለህይወቴ ፋና ለእኔ ክብሬ

ቴዲ መምህሬ የሙዚቃ አባቴ

ለነፍሴ ትሩፋት ብስራት ለህይወቴ

የክፉ ቀን ደራሽ ባለውለታዬ

አንተን ያደንቁሃል ነፍስና ስጋዬ

ቴዲ መምህሬ

ከስጋዬ ተዋድዶ

ከነፍሴ ተዋህዶ

ስርጉ በልቤ ገባ

የጥበብን አዝመራ ሊዘራ

የጥበብን ፊደል ያስቆጠርከኝ የግሌ የኔታ

በልቤ አዳራሽ ውስጥ አለህ ትልቅ ቦታ

ምስጋና ይድረስ አንተን የሀገሬ ሰው የኔ ያረገህ ጌታ!

# 14

# ከዝነኝነት ወደ ተምሳሌትነት የተመነጠቀ ኢትዮጵያዊው የሙዚቃ ንጉሥ!

በማንኛውም የሥራ ወይም የሙያ መስክ ተሰማርቶ ጠንክሮ በመስራት ታዋቂ መሆን ይቻላል፡፡ በህዝብ ዘንድ ታዋቂ ለመሆን ቀላል ባይሆንም አንድ ድንቅ ሥራን መስራት በቂ ሊሆን ይችላል፡፡ ዝናና ተወዳጅነትን ለመጐናጸፍ ግን ከዚያ የበለጠ አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ ግድ ይላል፡፡ ይህ ደግሞ በቀላሉ ሊገኝ የማይችል ከፍተኛ ጥረትን፣ መልፋትንና መድከምን የሚጠይቅ ነው፡፡ በተለይ የህዝብ ሞዴልና ተምሳሌት ሆኖ የክብር አክሊልን መድፋት የብዙ ታላላቅ ሰብዕናዎች ድምር ውጤትና ጥቂቶች ብቻ የሚታደሉት ፀጋ ነው፡፡

በሀገራችን "ዝናን ተላብሰዋል"፣ "ዕውቅናን ተቀዳጅተዋል" የምንላቸው ስመ-ጥር ሰዎች፣ ቀደምት ታሪካቸውን ወደኋላ መለስ ብለን ብናጤን በብዙ ውጣ ውረድ የተከበቡና በመሰናክል የታጠሩ እንደነበር እንረዳለን፡፡ እገሌ ዝነኛ ነው ከተባለ የዝናውን በትር ከመጨበጡ በፊት የከፈለው መስዋዕትነት እንዳለ አሻግረን መገመት





አያዳግተንም፡፡ ምክንያቱም አንድ በሥራው የላቀ ደረጃ ላይ ለመድረስና ታዋቂ ለመሆን የሚሻ ሰው በወሬና በአሉባልታ ሳይፈታ፣ ለማናቸውንም ችግሮች ሳይንበረከክ፣ ሊያሰናክሉት በሌሎች የተጠመዱ ወጥመዶች ሳይበግሩት በብልሃት ተሻግሮ ካለመበት ደረጃ መድረስ የሚችል ልበ-ሙሉና ጠንካራ መንፈስ ሊኖረው ግድ ይላል፡፡

ዝነኛ ከሆነስ በኋላ? የሚዲያ ሽፋን ያገኛል፤ ስለስራውና ስለ ህይወቱ በዝርዝር ይጻፍለታል፡፡ የዚህ ጊዜ ግለሰቡ ካልተጠነቀቀና ዝናውን በአግባቡ ካልጠበቀው በራሱ እጅ የመጥፊያው መንገድ እንደተያያዘ ይቆጠራል፡፡ ዝናውን በአግባቡ የሚጠብቅ ጠንቃቃና ብልሃተኛ ከሆነ፣ በደረሰበት የዝና እርከን ሳይኩራራ ህዝቡን አክብሮ የተሻለ ምርጥ ሥራ ይዞ ለመቅረብ ከተጋና የእግዚአብሔርን ቸርነት ከተጨመረበት ግን የመጨረሻው ጉዞ ወደ ተምሳሌትነት የክብር አክሊል መድረስ ይሆናል፡፡

ተምሳሴትነት፡-

ተምሳሌትነት የዚህ ዓለም ከባዱና ማንም ሰው ከመሬት ተነስቶ የማይደርስበት የክብር ሁሉ ታላቅ ክብር፣ የማዕረጐች ሁሉ ቁንጮ ማዕረግና የመጨረሻው ጉዞ ነው፡፡ እገሌ ተምሳሌት ሆነ ማለት ህዝቡን ወከለ፣ አርአያ ወይም ሞዴል ሆነ እንደ ማለት ነው፡፡

ለመሆኑ በሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከታዋቂነት ወደ ዝነኝነት፣ ከዝነኝነት ወደ ተምሳሌትነት የተሸጋገረ ምርጥ ሰው ማነው?

በተለያዩ የምሽት ክበቦች የቴዎድሮስ ታደሰንና የነዋይ ደበበን ሙዚቃ አስመስሎ ሲጫወት ያዩት ሰዎች "ይህ ልጅ ወደፊት ትልቅ ደረጃ ላይ ይደርሳል" ብለው የመሰከሩለት ቴዲ አፍሮ፣ በ1993 ዓ.ም መገባደጃ ላይ "አቡጊዳ" የተሰኘው የመጀመሪያ የሙዚቃ ሥራው በቮይስ ሙዚቃ ቤት አሳታሚና አከፋፋይነት ለህዝብ ጆሮ ባበቃበት ወቅት፤ የዜማውን ምጡቅ ቅመራ፣ የግጥሙን በሳል መልእክትና

የድምጹን ልዩ ቃና... በተለይ ለጀግናው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ እና ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባቀነቀናቸው ዘፈኖቹ በአንድ ጊዜ እውቅናን ጨበጠ፡፡

ቴዲ በዚያች ተአምር የተፈጠረባት ዓመት "አቡጊዳ"ን ይዞ፣ በጥበብ ደጅ ቆሞ በሚሰረቀረቅ የድምጹ ቃና

*"ገና ልጅ ነኝ ብላቴና*

*ስለፍቅር ምን አውቅና..."*

ብሎ ከህዝቡ ጋር ሲተዋወቅ እውነትም በህያዎቹ መጀመሪያ የዕድሜ ክልል የሚገኝ አካላዊ ልጅ ነበር፡፡ ነገር ግን ተፈጥሮ ባደለችው እምቅ የጥበብ ችሎታ ስለፍቅር የዘመረ፤ ለላምን፣ ፍቅርንና መቻቻልን የሰበከ፤ የልጅ አዋቂ፣ የሊቆችም ሊቅ ሆኖ ነበር ብቅ ያለው፡፡ በወቅቱ በጥበብ ችሎታው ያልተገረመ ማን ነው? በአንድ አልበም ብቻ በድፍን ሀገር የእሱን ያህል ዝናና ተወዳጅነትን የተጐናጸፈ ማን አለ?

ይህ "አቡጊዳ" የተሰኘው አልበሙ ከሀገር ውጭ በተለያዩ የአፍሪካና የአውሮፓ ታላላቅ ከተሞች ውስጥ ኮንሰርቶችን እንዲያቀርብ በር ከፍቶለታል፡፡ እናም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ‹የሀገራችን የሙዚቃ ዕድገት በአንድ ሳይሆን በአስር እርምጃ ከፍ ያደረገ ምርጥ ዘፋኝ› በማለት እየተወደሰ ጉዞውን በጥንቃቄ ቀጠለ፡፡ በተለይ ወቅት ጠብቆ በየመሃሉ የሚለቃቸው አንዳንድ ነጠላ ዜማዎች ማህበራዊ ፋይዳቸውና በሳል ይዘታቸው የህዝብን ቀልብ ቆንጥጠው መያዝ የቻሉ የምርጦች ምርጥ ስለነበሩ አርቲስቱ ከህፃን እስከ ሽማግሌ የሁሉም ሰው ምርጫ እየሆነ መጣ፡፡

ቴዲም ለሙዚቃ ዕድገት ወገቡን ታጥቆ የተነሳ እስኪመስል ድረስ በየጊዜው የተሻለ ሥራ ይዞ ለመቅረብ የሚታትር ድንቅ አርቲስት በመሆኑ፣ ታዋቂነቱም የዚያኑ ያህል ገነነ፡፡ በሬድዮ ጣቢያዎች እየተነገረለት፣ በጋዜጣዎች እየተዘገበለት፣ በቴሌቪዥን እየተተረከለት፣ የውጭ መገናኛ ብዙሃን ሳይቀሩ ሰፊ ሽፋን እየሰጡት





ሄዱ፡፡ ህዝቡም የዕለት ተዕለት መወያያ አጀንዳ አደረገው፡፡ አርቲስቱ በአንዳንድ አጋጣሚዎች የሚናገራቸው መሬት ጠብ የማይሉ አስገራሚ ንግግሮቹ የበለጠ አስወደዱት፡፡ ከእሱ በፊት ሙዚቃን የጀመሩ ዘፋኞች (አንጋፋዎቹም ሳይቀሩ) ሁለት እጆቻቸውን ከፍ አድርገው በማጨብጨብ ስለብቃቱና ጥንካሬው መሰከሩለት፡፡ ገና ወደሙዚቃ ዓለም ለመግባት የሚንደረደሩ በርካታ ወጣት ድምጻውያን ደግሞ እንደ አርአያ ይከተሉት ጀመር፡፡

ወጣቱ ድምጻዊ ቴዲ አፍሮ ከ1993 ዓ.ም እስከ 1995 ዓ.ም በታዋቂነት ዙፋን ላይ ለሶስት ዓመታት ቆይቷል፡፡ ከ1995 ዓ.ም ወዲህ ግን በቀጥታ የተሸጋገረው ወደ ተምሳሌትነት ነው፡፡ ወደዚህ የመጨረሻው የክብር እርከን (ወደ ተምሳሌትነት ወይም ወደ ልዕልና) በአንዴ ያስፈነጠረው ደግሞ ለጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ ያቀነቀነው "ቀነኒ ኬኛ" የተሰኘው ነጠላ ዜማው ነው፡፡ ይህ በወገን ፍቅር በነደደ ብርቱ ስሜት የተዜመ ዜማ በመላው ኢትዮጵያዊያን ወገኖቹ ከመወደዱም በላይ ራሱን ቴዲ አፍሮን ጨምሮ ጀግኖች አትሌቶቻችንንና የብዙሃኑን ኢትዮጵያ እንባ በደስታ ያራጨ "ድራማቲክ" የሆነ ፈጣን የሙዚቃ ሥራ ነው፡፡

ይህ የድል አብሳሪ ገድላዊ ዘፈን በሬዲዮ በተለቀቀበት ወቅት በበርካታ አድማጮች የይደገምልን ጥያቄ መሰረት በሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ከአስር ጊዜ በላይ ለአየር በቅቷል፡፡ በዚህ ምርጥ ዜማ በሀገር ፍቅር ስሜት ያልተናጠ፣ የአልሸነፍ ባይነት ወኔው ያልተቀሰቀሰ፣ ከመቼውም በላይ አንድነቱንና ዕድገቱን ያልተመኘ አንድም ሀገር ወዳድ ዜጋ አልነበረም፡፡

ቴዲ አፍሮ ከዚህ ምትሀታዊ ነጠላ ዜማው ቀጥሎ ግንቦት 1997 ዓ.ም ላይ የለቀቀው "ያስተሰርያል" የተሰኘው አልበሙ ደግሞ ዝናውና ተምሳሌነቱ እንደተተኮሰ ሮኬት ሰማይ ጠቀስ አደረገው፡፡ ለሙዚቃ የተፈጠረ ልዩ የጥበብ ሰውም አስባለው፡፡ የታደለው ፀጋና ምጡቅ ክህሎቱ እንደ ባቢሎን ግንብ በቀላሉ ሊደረመስ የማይችል መሰረተ ፅኑ ስለመሆኑ አረጋገጠለት፡፡ ይህ የብዙ ጊዜ ልፋትና

የጥረት ውጤት እንደሆነ ማንም አድማጭ የሚመሰክርለት አልበም ኤሌክትራ ሙዚቃ ቤት በ1.2 ሚሊዮን ብር ገዝቶ እንዳከፋፈለው ወሬው በመላው ዓለም የተሰማ ጊዜ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአንድ ድምፅ "ይገባዋል" ሲል በደስታ ፈነጠዘ። ሌሎች ቅን ድምጻውያንም "ፀሐይ አፈነጠቅልን!" በማለት አመሰገኑት። በአጠቃላይ በሚሰራቸው ድንቅ ጥበባዊ ስራዎቹ በሁሉም ልብ ውስጥ ነግሶ፣ በሰው ልቦች ፍቅር ተክቦ የሚወደስም የሚከበርም ታላቅና ብቸኛ የጥበብ ሰው ስለመሆኑ ገሃድ ወጣ።

በዚህም የሙዚቃን ሃያልነት በማስመስከርና በሰዎች አዕምሮና ጠሊቅ ልብ ዘንድ የጥበብን ዘር ዘርቶ ለመልካም ፍሬ በማብቃት ቴዲን የሚስተካከለው አንድም ሰው ታጣ። ከዚህ ቀደም ባራመዱት ህዝባዊ ዓለማና በሙያቸው ባበረከቱት ወደር የለሽ አስተዋጽኦ ለተምሳሌትነት የበቁ ጥቂት - እጅግ ጥቂት ኢትዮጵያዊያን ቢኖሩም፣ እንደ ቴዲ አፍሮ ድንበርና ኬላ ጥሶ በአፍሪካም ሆነ በአውሮፓ ታዋቂና ተወዳጅ ለመሆን የቻለና እንዲህ ያለ የተምሳሌትነት ካባ የተጐናፈ ነበር ማለት እጅግ ይከብዳል። ይህ ያልሆነበት ምክንያት ደግሞ ቴክኖሎጂ ባለመዳበሩ ሳይሆን ቴዲ አፍሮ ለሀገራችን የሙዚቃ ዕድገት የላቀ ክስተታዊ ፍጡር ሆኖ በመገኘቱ ነው። በዚህ ምትሀታዊ በሆነ ልዩ ችሎታው ሚሊዮኖችን ያስገረመ፣ ኪነ-ጥበብን ያስከበረ፣ የሙዚቃን ሙያ በብዙ እጥፍ እንዲወደድ ያደረገ፣ በሙያው ዓለምን እየዞረ የሀገሩን ባንዲራ ከፍ አድርጐ ያውለበለበ፣ የአርቲስቶችን ክብርና ንዋያዊ ጥቅም በሚያስገርም ሁኔታ ሽቅብ እንዲመነደግ ወሳኝ አስተዋጽኦ ያበረከተ በመሆኑ ነው ከማንም በላይ ለዚህ የክብር አክሊል የበቃው።

አዎን፣ ቴዲ በሀገራችን የሙዚቃ ህይወት ላይ ያመጣው ሁለንተናዊ ስር ነቀል ለውጥና ያሳረፈው የጥበብ አሻራ ማንም ሊክደው በማይችል ሁኔታ በደማቅ ቀለም የተመዘገበ ታሪክ ነው። ለወደፊቱም ቢሆን የእሱን ያህል ደማቅ ታሪክ የሚሰራ፣ የእሱን ያህል ኃያል ተፅዕኖ ማሳረፍ የሚችል የምርጦች ምርጥ ከያኒ ይፈጠር ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ለብዙዎቹ አጠራጣሪ ሆነዋል።





# የቴዲ አፍሮ ወርቃማ አባባሎች

- "ማንም ሰው በተለያዩ አጋጣሚ ሊያስቀይምህና ሊበድልህ ይችላል። ቢሆንም ካንተ አይጉደል"
- "የእውነት ምስጢር የገባህ እለት ሞትን አትፈራትም"
- "ክፉን በመልካም ማሸነፍ ታላቅነት ነው"
- "ስለ እውነት በኖረክ ቁጥር የሀሰት ገመድ ሊያስርህ እንደሚፈልግ ልታውቅ ይገባል።"
- "በየትኛውም ስፍራ ጥሩ ሆነህ ተገኝ። ጥሩ ነገርንም አድርግ። በህይወትህ የጎደለህን ነገር እግዚአብሔር ይሞላልሃል"
- "እግዚአብሔርን የምንፈራው በማውራት ሳይሆን ከውስጣችን ባለ ቅንነት እና የዋህነት ነው"
- "ብልህ ሰው ታናሹንም ያዳምጣል"
- "የሚወድህ ሰው ከሚጠላህ የጠላህ ሰው ቢደበድብህ ይሻላል።". . .

# ክፍል አራት

# ቴዲ አፍሮ በሌሎች ዓይን

## 15

## ቴዲ አፍሮና ሚዲያ

***የሰው ልጅ በብዛት ሲፅፍም ሆነ ሲናገር ራሱን ይመስላል***

በአገራችን ለህትመት የሚበቁ የጋዜጦችና የመፅሄቶች የኪነ-ጥበብ አምዶች ካለፉት አስርት ዓመታት ወዲህ እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ አዘጋጆቹም እርስ በእርስ በቀና መንገድ በመፎካከር ለአንባቢያን አዳዲስ ቁም ነገሮችን ለማስነበብ በየፊናቸው ሲሯሯጡ ይታያሉ፡፡ በውስጥ ገፃቸው ከአገራችን አልፎ ስለዓለም ብዙ ነገርን ያስጨብጡናል፡፡ የጋዜጣ ይሁን የመፅሔት አዘጋጆች ለአንባቢያን ትምህርትና አዝናኝ ፅሑፎችን ለማስነበብ ሲሉ ብዕራቸውን

አሚጠው፣ ወረቀታቸውን አባክነው፣ አዳዲስ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ብዙ ለፍተው፣ የኢንተርኔት መስኮታቸውን ከፍተው፣ ቀንና ሌሊት ሳይበግራቸው ያላቸውን አቅም ተጠቅመው ለህዝብ ያደርሳሉ።

በአገራችንም በከፍተኛ ሁኔታ የንባብ ልምድ እየዳበረ መምጣቱ የአንባቢውን ንቃተ ህሊና ከመጨመሩም በላይ የአስተሳሰቡና የግንዛቤ አድማሱን ያሰፋል። በቀላል የማይገመትን እውቀት እያስጨበጡን ስለሆነ ለአዘጋጆች ምስጋና ይገባቸዋል።

እኔን ያስገረመኝ ግን ይህ አይደለም። ሊያስገርመኝም አይችልም። ለመሆኑ ከ1997 ዓ.ም ወዲህ ለንባብ የበቁት የህትመት ውጤቶችን ልብ ብለው አስተውለው ከሆነ ሽፋናቸው (ልባሳቸው) ላይ የማንን ስምና ምስል ያያሉ? የዝነኛው ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን ምስል ነዋ! በምንም ሁኔታ ከጋዜጣና ከመጽሔቶች ላይ ጠፍቶ አያውቅም።

ወጣቱ ድምጻዊ ቴዲ አፍሮ በአጭር ዓመታት ውስጥ ለህዝብ ባበረከታቸው ምርጥ የፈጠራ ስራዎቹ ወደር ያልተገኘለት የዚህ ህዝብ ብርቅዬ አርቲስት ነው። የድምጻዊው አድናቂ ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ ሲያሻቅብ የሚታይበትም ሁኔታ አለ። በሚሰራቸው ጥበባዊ ፈጠራዎቹ መልካም ስምና የማይደበዝዝ ዝናን ለመላበስ የበቃ አስደናቂ ሰው ነው። አድናቂዎቹም ስለዚህ ድምጻዊ አዳዲስ መረጃ ማሰባሰብ የዘወትር ተግባራቸው ነው። የአገራችንም የንባብ አምዶች በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ነገር ሲያስነብቡን ቆይተዋል። አሁንም እያስነበቡን ነው። ወደፊትም ያስነብቡናል። ስለወጣቱ ቴዲ አፍሮ በየቀኑ ቢጻፍ፣ ቢወራና ቢተረክ ስለቸን የሚል ኢትዮጵያዊ የለም። እንኳንስ በየወሩና በየሳምንቱ ቀርቶ በደቂቃዎች ልዩነት ስለ ወጣቱ የሙዚቃ ብላቴና ቢነገረው የአድናቂው ጆሮ ዜናውን ለመስማት እንደናፈቀ ነው። የጋዜጣና የመጽሔት አዘጋጆችም ቢሆኑ በዚሁ ቀጥሉበት በርቱ ሊባሉ ይገባቸዋል። ምክንያቱም ለአድናቂዎቹ የአርቲስቱ የጤና፣ የሰላምና ያለበት የስራ ደረጃ በየጊዜው ማሳወቅ ያሳስባቸዋልና።





ቴዲ አፍሮ በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትና የህዝብ ፍቅር እንዳለው የገባቸው የፕሬስ አዘጋጆች፤ ‹‹በዚህ ምክንያት እኛ ደግሞ ሁልጊዜ በህትመቶቻችን ላይ የዚህን ድምጻዊ ስም በተለያዩ ጉዳዮች እያነሳን ለምን ፅሁፋችንን አንሸጥም፤›› ብለው ቆርጠው የተነሱ ሳይሆኑ ለህዝብ ማቅረብ የሚገባቸውን አብይ ጉዳይ የማቅረብ ሙያዊ ኃላፊነት ስላለባቸው ነው።

ምክንያቱም ሚዲያ ማለት አርቲስትን ከአድናቂዎቹና ከህዝቡ የሚገናኙበት ዋና የመገናኛ መድረክ ነው። በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ከባለቤቱ ፈቃድ ውጭ በወሬና በስማ በለው የሚሰሩ ዘገባዎች አሉ። ቢሆንም ግን ፀሀፊዎቹን ሳላደንቃቸው አላልፍም። እውነተኛ ሙያዊ ግዴታዎች በመወጣት መነገርና መጻፍ ያለበትን አብይ ጉዳይ ለህዝብ እያደረሱ ነውና።

በአንድ ወቅት አዲስ ነገር ጋዜጣ ስለ ቴዲ አፍሮ ያወጣው መረጃ እንዲህ ይል ነበር። "ስለ ቴዲ በየወሩ የሚታተሙ መጽሔቶች በጥቂት ገጾቻቸው ላይ ስለ ቴዲ በመጻፋቸው ምክንያት ብቻ የቅጂዎቻቸው ብዛት ከ33 ሺህ ወደ 55 ሺህ ለማሳደግ ችለዋል። የአንባቢውን ብዛት ከ495 ሺ.ህ ወደ 775 ሺ.ህ ከፍ ማለቱን" ጋዜጣው በቁጥር 24 ቀን 2000 ዓ.ም እትሙ አሳውቋል።

ወጣት፣ አዛውንት፣ መምህርና ሹፌሩ የሚነበብ ጋዜጣ ወይም መጽሔት ሲገዙ ጋዜጣ አዟሪውን በቅድሚያ የሚጠይቁት ስለ ቴዲ አፍሮ ምን ተባለ? ነው። የዚህን አርቲስትም ስም በየጊዜው በማብጠልጠል የግል ኪሳቸውን ሲያደልቡና የንባብ አምዳቸውን ለህዝብ ሲቸበችቡ የቆዩ አንዳንድ ፀሀፊዎችና አሳታሚዎችም አልጠፉም። እነዚህ ጥቂት ሰዎች ‹‹ላም ባልዋለበት......›› የተባለውን የሀገሬን ተረት በአርቲስቱ ላይ ሲገለገሉበት ታይቷል።

በዚያ ላይ የመፅሔት እና የጋዜጣ ዋና አዘጋጆች የቅርብ ጓደኞቹ ናቸው። እናም አንድ ቀን ሻይ እየጠጣን ለፅሁፌ ማጠናከሪያ እንዲሆነኝ ስለቴዲ አፍሮ የአንድ ታዋቂ መፅሄት አዘጋጅ የሆነውን

ግለሰብ ጠየኩት፡፡ ለመጠጣት ያነሳውን ማኪያቶ መልሶ አስቀምጦ እንዲህ አለኝ፡፡

‹‹ስለ ወጣቱ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ያገኘሁትን መረጃ እፅፋለሁ፡፡ ምክንያቱም የማሳትመው ለህዝብ ነው፡፡ ቴዲ ደግሞ የዚህ ህዝብ የቅርብ ዘመድ ሆኗል፡፡ በብዙ ህዝብ ዘንድ የሚወደድና የሚከበር ነው፡፡ ሁል ጊዜ ስለቴዲ ብታስነብበው፣ ብታወራለት፣ ብትተርክለት የሚፈልግ ነው፡፡ ስለዚህ በማንኛውም እትሜ ላይ በተለይም ከአምስት ዓመታት ወዲህ በየወሩ ስለ ቴዲ አፍሮ እፅፋለሁ፡፡ ስለ ቴዲ አፍሮ ለመፃፍ ግድ ይልሃል፣ በውስጥህ የሆነ ነገር እንድትፅፍ ያስገድድሃል፡፡ ቴዲ እኮ ዘፋኝ ብቻ ሳይሆን የብዙ ነገሮች ተሰጥዖ ያለው ብርቅዬ ልጅ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ በመፅሔቴ ላይ ስለ ቴዲ የምፅፈው ለእሱ ካለኝ እውነተኛ ፍቅር የተነሳ ነው›› ብሎ በእልህና በቁጭት አጫወተኝ፡፡

ሌላው ወዳጄ የአንድ ታዋቂ ጋዜጣ አዘጋጅ ነው፡፡ በስራ ምክንያት ቁጭ ብለን ስንነጋገር ሰላምታዬን አስቀድሜ ወደ ጥያቄዬ አመራሁ፡፡ እየሳቀ ‹‹ምን ነካህ? የኔ ጋዜጣ በየሳምንቱ ለህዝብ በምትቀርብበት ጊዜ ሁሌ ስለ ቴዲ አዳዲስና የተለያዩ ዘገባዎች ቢኖራት ደስ ይለኛል፡፡ ስለሆነም እፅፋለሁ፡፡ በየሳምንቱ ቀርቶ በየቀኑ ሊፃፍለት የሚገባ ጠንካራ አርቲስት ነው፡፡

‹‹እንደውም›› አለ ‹‹አብዛኛው አንባቢ ስለቴዲ አፍሮ በአንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ ተንተርሰህ ጥሩ ነገር ብታስነብበው ደስ የሚለው ነው፡፡ ቴዲን ማንም ሰው ይወደዋል፡፡ በሚሰራውም የሙዚቃ ስራ ጠንካራ፣ እንከን የማይገኝለት ጠንቃቃ አርቲስት ነው›› ብሎኝ ቆይታችን አበቃ፡፡ በርካታ የጋዜጣና የመፅሔት አዘጋጆች ለህዝብ በሚያቀርባቸው ወርቃማ ስራዎቹ አመት አልፎ አዲስ አመት በመጣ ጊዜም ‹‹የአመቱ ምርጥ ሰው›› በማለት ያሞካሹታል፡፡





## ከቴዲ አፍሮ አድናቂዎች የተሰጠ የምስክርነት ቃል

‹‹ስሜ ትንቢት ግርማ ይባላል፡፡ የቴዲን የፈጠራ ስራዎቹን ስሰማ የዜማና የግጥሞቹ መልእክት ይመስጡኛል፡፡ በተለይ የሚያምረው ድምፁ ልቤን በሀሴት ይንጣታል፡፡ ዘፈኖቹ ለታሪክ ሊቀመጡ የሚገባቸው የኢትዮጵያ ልዩ ቅርስ ናቸው፡፡ ከዘፋኝነት ባሻገር ለወገኖቹ የሚለግሳቸው የገንዘብ፣ የሃሳብና የሞራል በጎ አድራጎቶች ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም፡፡ ስለ ቴዲ አፍሮ የፈለገው የሙገሳ ቃል ብጠቀምም የውስጤን የሚገልፅልኝ አይመስለኝም፡፡ በዚህ ዓለም ከራሱ በላይ ሌላውን ወገን የሚወድ ፍጡር ውሻ ብቻ ነው፡፡ እኔ ግን ይሄንን የሙዚቃ ጀግና ከራሴ በላይ እወደዋለሁ ብዬ ብናገር ቅንጣት አላጋነንኩም፡፡ እንኳንስ በሚዘፍነው ዘፈን በሚናገረው ንግግርም ውስጤን ያሸንፈዋል፡፡ ሙዚቃን በቴዲ አፍሮ አጣጥሜ አውቂያለሁ፡፡ ቴዲ የሙዚቃ የፈጠራ ውጤትን እንዳከብርና እንዳስከብር ብሎም ለሃገራችን አርቲስቶች ክብርን እንድሰጥ አድርጎኛል፡፡ ስለሆነም ቴዲ ሁል ጊዜ እጅግ በጣም የሚገርምና የሚደነቅ ዘፋኝ ነው፡፡ ለዚህች ሀገር ወሳኝ ነው ብዬ በቁጥር አንድ የማስቀምጠው ሰው ቢኖር ቴዲ አፍሮ ነው፡፡ ዜማውን ሰምቼ፣ ግጥሞቹን አድምጬ፣ የአእምሮውን የብስለት መጠን ስገምተው እጅግ በጣም የሚገርም ጭንቅላት አለው ብዬ አስባለሁ፡፡ ፈጣን የሆነ የፈጠራ ችሎታ አለው፡፡ ስለሚያስበው ነገር የመፃፍ ብቃት አለው፡፡››

* * *

‹‹አዲስ አለም እባላለሁ፡፡ የ29 ዓመት ወጣት ነኝ፡፡ በአንድ የስራ ተቋም ውስጥ ተቀጣሪ ነኝ፡፡ ሙዚቃ መስማት የመጀመሪያ ምርጫዬ ነው፡፡ የቴዲን ሁሉንም ዘፈኖቹን በእኩል ስሜት እወዳቸዋለሁ፡፡ በተለይ ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ስላሴ የዘፈነው፣ ለአትሌቶቻችን ያዜመው፣ አብሶ ደግሞ ‹‹ያስተሰርያል›› የሚለው ሙሉ አልበሙ ወደር የማይገኝላቸው ዘፈኖቹ ናቸው፡፡ የግጥሙ

ብስለት የዜማው ውበት እጅግ በጣም የሚማርክ ሐይል አለው። የማይደንቀው እሱን ብቻ ነው። ምክንያቱም መደነቅና መወደስ ስላለበት። እንደሌሎቹ ዘፋኞች የውጭ ሀገርን ኑሮ የማይመኝ ሀገሩንና ወገኑን የሚወድ ነው። መወደዱም አፋዊ ሳይሆን በተግባር ያሳየ የኢትዮጵያ የህዝብ ውድ ልጅ ነው። በአንድ ወቅት ቦብ ማርሊይ እንዲህ ብሎ ነበር። ‹በዓለም ላይ ያለን የዘር መከፋፈል በሽታ በዘፈኔ አክሜ አድነዋለሁ።

ይህን እውነታ ቴዲ እንደሚያደርገውም እምነቴ ነው። ቴዲ አፍሮ ለእኔ የማይዋሽ እውነተኛ ከያኒ ነው። የሚያነሳቸው ሃሳቦች ደስታ ይፈጥሩልኛል። ስለቴዲ ያለኝ ቀና አመለካከት በምሰራው ስራም ላይ ቢሆን ከፍተኛ እገዛ አድርጎልኛል ማለት እችላለሁ። ቴዲ አፍሮ ወደፊት ከሰው አእምሮ በላይ የሆኑ ታሪካዊ ስራዎችን እንደሚሰራ አምናለሁ። ቴዲ ሙስሊምና ክርስትያንን በፍቅር ያጣመረ፣ በመሃከላቸው የጸና የፍቅር ግንብ የገነባ ውድ አርቲስት ነው። በብዙ ነገሮቹ አደንቀዋለሁ።››

## ከቴዲ አፍሮ ቤተሰባዊ ግንኙነት ያለው ወጣት ቴዎድሮስ ግሩም (ቴዲ ፎቶ) ስለ ቴዲ አፍሮ የሰጠው የምስክርነት ቃል

‹‹ወደዚች ምድር ስንመጣ እያንዳንዳችን በልዩ ልዩ ችሎታ የተገነባን ነን። ቴዲም ጥበብን ተሰጥቶታል። ከፈጣሪ የተቸረውን የሙዚቃና የተለያዩ ጥበቦች በሚገባ እየተጠቀመ ይገኛል።

‹‹ለዚህም ነው ቴዲ አፍሮ ከልጅነቱ ጀምሮ የእግዚአብሔር ቃል ከአፉ ተለይቶት የማያውቀው። በችግሩም፣ በጭንቀቱም፣ በደስታውም፣ የፈጠረው ስም ምርኩዝ እንደሆነ ያምናል። በዚህም ይመስለኛል የተሰጠውን መልካም ጥበብ በአግባቡ የሚጠቀም ጥበበኛ የሆነው። ቴዲን ብዙ ሰው የሚያውቀው ጥበብ ባንናጸፈችው ምርጥ ሥራዎቹ ይሆናል። እኔ ግን የሚገርመኝና የማደንቅለት አድማጭነቱን ነው። ለዚህም ጥሩና ብሩህ አእምሮ አድሎታል።





እናም ቴዲ አፍሮ ከመናገር መስማትን የሚመርጥ አስተዋይ ነው። የቴዲ ፀባይ ለማንም ሰው ተስማሚ ሆኖ ነው የተፈጠረው።

‹‹ተንኮልን አይወድም፣ ውሸትን አውግዞ ይጠላል። ማንም ሰው የሰውን ስም ያለአግባብ አንስቶ ሲያማ መስማትን አይፈልግም። እሱ ባለበት ቦታ ሁሉ ስለ ማንም ሰው ክፉ ነገር ከተነሳ ጥሎ ይሄዳል፣ ወይም የሐሜትን መጥፎነት አስረድቶ ዝም እንድትል ይነግርሃል።

‹‹ትዝ ይለኛል፤ አንዴ በግሩፕ ተሰብስበን በመካከላችን የሆነ ሰው መጥፎ ነገር ስላደረገው ጓደኛው ይነግረናል። በዚህ መሃል ቴዲ አፍሮ እንዲህ አለው "አትሳሳት፣ ጥፋተኛው እሱ ሳይሆን እኔ ነኝ ብለህ እመን። በመጀመሪያ ራስህን ጠይቅ ለምን ከእንደዚህ አይነት ሰው ጋር ለመዋል መረጥኩ? አብረሀም መዋል አልነበረብህም። ከዋልክም ከእኔስ ስህተት አለ ወይ ብለህ ራስህን ጠይቅ። ይኸኔ ራስህን ታገኛለህ" አለው። ቴዲ አፍሮ ጠንካራ ሰው ነው።

‹‹መስታወት ጥበብ በሚባለው ክበብ ውስጥ ከጓደኛው ድምፃዊ ጎሳዬ ተስፋዬ ጋር ወደ ሙዚቃ ዓለም ሲገቡ፣ ቴዲ በዚያ ክበብ ውስጥ በነበረው የተፈጥሮ እምቅ ችሎታ፣ ችግሮችን በጾምና በጸሎት፣ በጽናት፣ በትእግስት ተቋቁሞ ማሳለፍ በሚችለው ጠንካራነቱ በአንድ ጊዜ ያደገ ልጅ ነው። ወደ ሙዚቃው አለም ከተቀላቀለ በኋላ ቀላል የማይባል አርቲስት ነው።

‹‹ድሮ ልጅ እያለ ወደ ፊት ለኤፍሬም ታምሩ ዜማ እሰጠዋለሁ እያለ ይመኝ ነበር። ይህንን ቃል በተናገረበት ጊዜ ካለበት ሁኔታ ሲታይ ለማመን ቢከብድም እሱ ግን አድርጎት አይቻለሁ። ለካስ በውስጡ ያለች ጥበብ የእውነትን ትንቢት ትናገር ነበር።

‹‹ብዙ ሰዎች ጊዜና ገንዘብ ሲቀይራቸው ቴዲ ግን እንደ ትላንቱ ዛሬም ያው ነው። ማንም ተነስቶ ቢበድለው፣ ወይም ያለ አግባብ ስሙን ቢያጠፋው አንድ ቀን ‹እገሌ በደል አደረሰብኝ› ብሎ ሲያማርር አይሰማም። ሁሉም ነገር ‹ለበጎ ነው› ብሎ ያልፈዋል።››

*ጥያቄ፡- ስለ ቴዲ አፍሮ መልካምነት ነግረኸኛል። እንዲህ መልካም ሰው ሆኖ ግን እጅግ ብዙ ወዳጆች አሉት ብለህ ታስባለህ?*

‹‹ይህንን ለመገመት ያስቸግረኛል። ነገር ግን እንደሚመስለኝ ወርቅ በእሳት ነው የሚፈተነው። ያሉት እጅግ በጣም ጥቂት ወዳጆች ናቸው። እና እሱ /ቴዲ አፍሮ/ የብዙዎች ወዳጅ ሲሆን ጥቂት ወዳጆች ያሉት ነው የሚመስለኝ። አድናቂዎቹን ግን አይጨምርም። እግዚአብሔርን በመፍራት ጥበብን ስትቀበል በአንተ ላይ ያደረችው ጥበብ የተባረከች ነች። ቴዲም ለዚህ ነው ትልቅ ቦታ ያለው። ከዚህም ሌላ በማህበራዊ ህይወቱ ቸር እና ጥሩ ሰው ነው።

‹‹ለምሳሌ፡- በኪነ ጥበብ መስክ ውስጥ ጀማሪ አርቲስቶች በሀሳብ፣ በሞራልና በገንዘብ እገዛውን ለግሶላቸዋል። ሮሀ በሚባለው ክበብ ውስጥ የእሱን ስራ በማስመሰል የሚጫወት አንድ ወጣት ነበር። ቴዲም ሲዘፍን አየውና "ሚኪ ወደፊት ካሴት ሳይሆን ዘፈን ስራ" በማለት ብዙ ነገሮችን ሲነግረውና ሲመክረውም ሰምቼ ነበር።

‹‹ለበርካታ ዘፋኞች ዜማና ግጥምን በመስጠት ለሀገሩ የሙዚቃ እድገት ትልቅ አስተዋፆኦ አበርክቷል። ቅንነት ከዚህ ይጀምራል። የሰው ልጅ በብዛት ሲፅፍም ሆነ ሲናገር ራሱን ይመስላል። ስለዚህ ቴዲ አፍሮ ማነው? ለሚለው መልሴ አንድና አንድ ነው። ከፍተኛ የሆነ የጥበብ ሰው፣ አስተዋይና ገራገር፣ ብሎም ለወገኑና ለሀገሩ አሳቢና ተቆርቋሪ ፍጡር ነው።››

*ጥያቄ፡- ከቴዲ የምትወድለት አባባል ካለ?*

‹‹ክፉን በመልካም ማሸነፍ ይቻላል" የሚለውን አባባሉን እወድለታለሁ። ይህንን አባባሉን እኛም የህይወት ተሞክሮአችን ብናደርገው ይጠቅመናል እላለሁ።››

*ጥያቄ፡- ስለ ቴዲ አፍሮ ባጭሩ ብትገልፅልኝ?*

‹‹አንድ ነገር በእርግጠኝነት ልነግርህ የምችለው ቴዲ ነገ ለሚወዳት ለዚች ሀገር ተረኛ ባለታሪኳ እንደሆነ ነው።››



-------------------------------- የቴዲ አፍሮ የታላቅነት ምስጢር --------------------------------

*ጥያቄ፡- ከቴዲ ስራዎች በጣም የምትወደው የትኛውን ነው?*

‹‹ከባድ ጥያቄ ነው። የትኛውን ትቼ የትኛውን ልበልህ? ግን ምረጥ ካልከኝ ‹መንገደኛ ነው ልብሽ› የሚለውን መርጫለሁ።››

*ጥያቄ፡- ቴዲ ለእንደዚህ አይነት ክብርና እውቅና የበቃበት ሚስጥሩ ምንድን ነው?*

‹‹ቴዲ ከልጅነቱ ጀምሮ በአእምሮው በእምዬ ማርያም ልጅ በመድሀኒያለም ያምናል። እርሱም በውስጡ አለ። ሚስጥሩ ይህ ነው።››

*ጥያቄ፡- ቴዲን የምትለው ነገር ካለ?*

‹‹ቴዲ አንተ ህያው ነህ። በአፌ ሳይሆን ከልቤ እወድሃለሁ። የሰማኒያ ሚሊዮን ህዝብ ልጅ ነህ። አንተን ያፈራች ማህፀን ምንኛ የተባረከች ናት። የሦስት ሺህ ታሪክ ያላት እናት እውነትም እድለኛ ናት።››

# 16

# ቴዲ አፍሮ ለክብሩ የተቀነቀነለት ብቸኛ አርቲስት

ስለ ሙዚቃ ከተነሳ በሁሉም የለው ልጅ ህሊና የሚታወሰው በመልካም ስሙ፣ በገናና ዝናው፣ በጠንካራነቱ፣ በሚጣፍጠው ዜማውና ልዩነት ባለው መረዋ ድምፁ ለሀገራችን የሙዚቃ እድገት ባበረከተው ወደር-የለሽ አስተዋፅኦ ቴዲ አፍሮ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል። የሚያቀነቅናቸው ዘፈኖች በጠቅላላ ለመንፈስ እርካታ፣ ለህሊና ሰላም፣ ለድብርት መነቃቂያ፣ ለነፍስ ምግብ ናቸው።

በተለይ በቴዲ ጊዜ ሙዚቃ የሁሉም ሰው ምርጫ ሆኗል። ከህፃን እስከ አዋቂ፣ ከከተማ እስከ ገጠር፣ ከሀገር ቤት እስከ ባህር ማዶ፣ በመልካም ስራው የሚነገርለትና በአጭር ጊዜ ውስጥ የለውን ልጅ ፍቅር ለመላበስ የበቃ ጠንካራ አርቲስት ነው።

ቴዲ በሚያቀነቅናቸው ዘፈኖቹ በአንድ የዘፈን ግጥም ውስጥ በርካታ በሳል መልዕክቶችን ማስተላለፍ የቻለና ብቃቱን ያስመሰከረ እንዲሁም ለብዙ ዘፋኞችና ታዳጊ ወጣቶች አብነት የሆነ ነው። በውጪው ዓለም አንድ ግለሰብ አመርቂ ስራ ሰርቶ ወገኑን ከጠቀመ፣



የቴዲ አፍሮ የታላቅነት ምስጢር

ህገሩን ካስጠራና ለህዝቡ አርአያ ከሆነ በሰራው ታላቅ ሥራ ልክ ሽልማት ይበረከትለታል። ስሙ ከትውልድ ትውልድ እንዲዘከርና ህዝቡም ከዚያ ታዋቂው ግለሰብ የህይወት ውጣ ውረድ እንዲማር ታስቦም ፊልም ይሰራለታል። መንገድና ትምህርት ቤት በስሙ ይሰየምለታል።

በአፍሪካ አህጉር በተለይ በእኛ ሀገር ግን የዚህ ዓይነቱ የህዝቡ ጀግኖችን አክብሮ ለክብራቸው መገለጫ የሚሆኑ እንደ መታሰቢያ ያሉ በጎ ተግባራት ተከታትሎ የመፈፀም ባህል እምብዛም አልተለመደም።

በእርግጥ ቴዲ አፍሮ የተወሰኑ ሽልማቶችን ለማግኘት የቻለ አርቲስት ቢሆንም ለህዝቡ ካበረከተው የጥበብ ስራ አኳያ ሲነፃፀር ግን ሽልማቶቹ እዚህ ግባ የሚባሉ አይደሉም። ‹‹ነብይ በህገሩ አይከብርም›› እንደሚባለው ሆኖ እንጂ ለዚህ ታላቅ የሕዝብ ተምሳሌት በህይወት እያለ ሀውልት ሊቆምለት በተገባ ነበር። ለማንኛውም ዋነኛውና ቁጥር አንድ የሆነውን ህዝባዊ ፍቅር መቀናጀት መቻሉ ነው። ከህዝብ ፍቅር የበለጠ ህያው ሽልማት የለምና። ምክንቱም የህዝብ ፍቅር ቀላል አይደለም። አንድ አርቲስት ደግሞ ያለ ህዝብ ፍቅርና ድጋፍ የበረሀ ቅጠል (የአሸዋ ላይ ቤት) ነው።

ቴዲ አፍሮ ለማንም ዘፋኝ ተደርጎ በማይታወቅ ሁኔታ ሌላ ለየት ያለ ሽልማት እንደተበረከተለት ንግስት የምትባል የመዝናኛ መፅሄት በ2000 ዓ.ም እትሟ ላይ አንድ አስደሳች ዜና ለንባብ አብቅታ ነበር። የዚህ ዝነኛ ድምፃዊ ፎቶ በመፅሄቷ ሽፋን ላይ ማይኩን ጨብጦ፣ የአይን ጥቁር መነፅር አድርጎ፣ በአረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ህብረ ቀለማት ያሸበረቀ ልብስ ለብሶ በትልቁ ታትሟል። ከስሩም እንዲህ የሚል ጽሁፍ ሰፍሯል። ‹‹ስቴዲ አፍሮ ‹የሰላም እርግብ› የተሰኘ ነጠላ ዜማ ተሰራ›› ይልና በመቀጠል ‹‹እሱ የሰጠን ብዙ ነገር ነው፣ ነጠላ ዜማ ያንሰዋል›› የሚል የድምፃዊው ቃል በጉልህ ይነበባል። ድምፃዊው አቤል ዘበነ ይሰኛል።

የዘፈነበትንም ምክንያት ሲገልጽ ‹‹ቴዲ አፍሮን በጣም የምወደውና ከማከብረው በላይ ሰፐበብ ጅምሬም መምህሬ ነው፡፡ በሚሰራውም የዘፈን ስራ እጅግ በጣም አድናቂው ነኝ፡፡ ቴዲን የመሰለ አርቲስት ብዙ የሚያስተምር፣ ሀገር ወዳድና ገራገር ሰው ምን አለበት ብዘፍንለት›› ይላል፡፡

በእርግጥ ቴዲ በስራው ባለመዘገበው ገድል ቢዘፈንለት ያንሰዋል እንጂ አይበዛበትም፡፡ ለአርቲስቱ በመዘፈኑ ለብዙዎች ታላቅ የምስራች ሆኖላቸዋል፡፡ ድምፃዊው አቤል ዘበነ ለቴዲ ለመጀመሪያ ጊዜ ‹‹የሰላም እርግብ ነህ›› ብሎ እንደዘፈነ ብዙም ሳይቆይ በዚያን ወቅት ሁሌ በየሳምንቱ ማክሰኞ ለንባብ የምትበቃው ጣዝማ ጋዜጣ ለፊ ማብራሪያ ይዛ ብቅ አለች፡፡

በጋዜጣው ላይ ስለ ቴዲ አፍሮ የዘፈነው አቤል ዘበነና ቴዲ አፍሮ አጠገብ ለአጠገብ የፎቶ ምስላቸው ይታያል፡፡ የዘፈነለት ወጣት ‹‹ለቴዲ አፍሮ በቀላሉ የማይገለፅ ታላቅ አክብሮት አለኝ፡፡ ወደ ሙዚቃ ህይወት እንድገባ ሞዴል የሆነኝም ብርቅዬ ልጅ ስለሆነ ልዘፍንለት ችያለሁ›› በማለት ጥልቅ ስሜቱን ገልጿል፡፡ ጋዜጣዋ በውስጥ ገጿ ለድምፃዊው በርካታ ጥያቄዎችን አቅርባለታለች፡፡

‹‹ቴዲ አፍሮን በማወደስ የመጀመሪያው ዘፋኝ በመሆኔም ደስተኛ ነኝ›› ይላል፡፡ ይህ ‹‹የሰላም እርግብ›› የሚል ርዕስ የተሰጠው ዘፈኑ ምንም እንኳን በሚድያ ተለቆ ብዙሃኑ ህዝብ መስማት ባይታደልም በአንዳንድ የመዝናኛ ቦታዎች በዲጀዎች አማካኝነት ለመለቀቅ ችሏል፡፡ ይህ የሙገሳ ዘፈን ሲለቀቅ ቴዲ አፍሮ በወቅቱ ለሥራ ጉዳይ አሜሪካ ሃገር ነበር፡፡

ሁለተኛው ለዚህ ታላቅ አርቲስት የዘፈነው ቢኒያም አሰፋ የተባለ ወጣት ድምፃዊ ነው፡፡ የዘፈኑ ርዕስ ‹‹ብላቴናው የታል›› የተሰኘ ሲሆን ቴዲ አፍሮ በተሽከርካሪ ሰው መግደል ወንጀል ተከሶ እስር ቤት በገባበት ወቅት ለመታሰቢያነት የተሰራ ዜማ ነው፡፡

‹‹ቴዲ ከሌለ መድረኩ ጭር ይላል፡፡ እሉ ሲጠፋ አይኔን ለው አማረው፡፡ የተሰጠውን አደራ የተወጣ›› የሚሉና ብዙ ሃሳቦችን





ለማካተት የሞከረበት ነጠላ ዜማ ነው፡፡

እውነት ነው ቴዲ ከሌለ መድረኩ መድረክ አይመስልም፡፡ ሙዚቃም ጭር ይላል፡፡ የአድማጭም ጆሮ ይቀንሳል፡፡ ድምፃዊው ቢኒያም በወቅቱ ቴዲ በተጠረጠረበት ወንጀል እስር ቤት ሆኖ ሳለ የአክብሮትና የመውደዱን መጠን በማዜም ገልፆለታል፡፡ ቢንያምም እንደቀድሞው ዘፋኝ የሚዲያ ሽፋን ስላላገኘ ሲዲውን አባዝቶ ለብዙ ዲጀዎች በመስጠት ዘፈኑን ህዝብ እንዲሰማው የበኩሉን ጥረት አድርጓል፡፡

ሶስተኛው ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ ይባላል፡፡ ሻምበል በላይነህ በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ለረጅም አመታት ባህላዊና ዘመናዊ ዘፈኖችን በመጫወት ተወዳጅነትን ለማትረፍ የቻለ አርቲስት ነው፡፡ ማይኩን ጨብጦ መድረኩን ሲረግጥ ለሙዚቃ ያለው ፍቅር ከፍተኛ እንደሆነ ከእንቅስቃሴው መረዳት ይቻላል፡፡

እናም የልቡን ሐሳብ፣ የነፍሱን መሻት እንደግል ሐሳብና ስሜቱ ለወጣቱ ድምጻዊ ቴዲ አፍሮ ‹‹ጀግና የፍቅር ሰው›› ሲል አወድሶታል፡፡ ሻምበል በላይነህ ለቴዲ አፍሮ ባቀነቀነው የዘፈን ግጥም ውስጥ ቁም ነገር ያላቸው መልክቶችን ለማካተት ችሏል፡፡ ሻምበሉ የልቡን ፍቅር የማክበሩን መጠን እሱም እንደሌሎቹ ዘፋኞች ለተወዳጁ ድምጻዊ ለቴዲ አፍሮ ‹‹ጀግና የፍቅር ሰው›› ሲል አዚሟል፡፡ ይህ ዘፈን በተዘፈነበት ወቅት ቴዲ አፍሮ በተሽከርካሪ ሰው መግደል ወንጀል ተጠርጥሮ እስር ቤት ነበር፡፡

ተወዳጁና ዝነኛው ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ገና በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ ታሪክ የሰራ ብርቅዬ አርቲስት በመሆኑ ነው በእነኚህ ሶስት ድምጻዊያን የተቀነቀነለት፡፡ ዘፈኑን የዘፈኑት ሶስቱ ድምጻዊያን ለቴዲ አፍሮ ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት የገለፁ ሲሆን ከእነኝህ ሦስት ድምጻውያን በተጨማሪ ቴዲ በእስር ላይ እያለ በሌሎች ዘፋኞችም ተቀንቅኖለታል፡፡ በዚህም የተነሳ በተደጋጋሚ በስሙ የተዘፈነለት ብቸኛው ኢትዮጵያዊ ሆኗል፡፡

# ቴዲዬ ኑርልኝ

የልብህ ከተማ ቢታይ ተመርምሮ
አያልቅም ተዝቆ ጥበብ ተከምሮ
በዜማ በቅኔ ህዝብን ጥበብ ስታጎርሰው
ብሎ ይጠራሃል ቴዲዬ የፍቅር ሰው

እኔም ነፍሴን ስላስደሰትካት በጥበብ ጣፋጭ ፍሬ
ቃል ባላወጣ ከአፍ ከከንፈሬ
ማወደሴን አልተው አንተን በብዕሬ
ደግሞም
የልቤን የሚገልፅ ሁነኛ ቃል ባጣ
በዝምታዬም አወድስሀለሁ ቃል ከአንደበቴ ሳይወጣ
አንተን ባወድስ ስለ አንተ ባወራ
ዘራፍ ብል ብፎክር ባቅራራ
ማን ነው ተው የሚለኝ
የሚከለክለኝ
እናገራለሁ በአደባባይ
ሐቀኛ ነህ የድል ፀሐይ





አልፈራም አልሸማቀቅም
ከሐሰተኞች አልቀላቀልም።
ኧንተ እውነት ተናጋሪ
ለወገን ተቆርቋሪ
ጥሩ ነገር ተዘካሪ
ይገባሃል ክብር ዝና
ቀማሪ የጥበብ ገናና
ሃሳቡ-ጥሩ ባለ መልካም ሰብዕና
ቸር የዋህ ርህሩህ ልበ-ቀና
ፍቅር የገባህ የህዝብ ጀግና
እናም
ኑር ለዘመናት
ቅኔን ስትቀምራት
ከቃል በላይ ሆኖብኛል የአንተ ሥራ
እንዳከራኽን አንተም ለዘላለም ኩራ
ኑር በክብር ከፉ አይንካብኝ
በሰላም በጤና ቴዲዬ ኑርልኝ።

# 17

# ቴዲ አፍሮ በጥቂት ዘፋኞች ዓይን

**‹‹ምቀኛ ሰው ባለጠጋ ለመሆን ይቸኩላል፡፡››**

**ምሳ 28፣22**

የሙዚቃ ፈርጥ፣ የዜማ ቀማሪ፣ የግጥም ባለአባት፣ ለጥበብ የተፈጠረና ልዩ መልእክተኛ ነው - ቴዲ፡፡ እንኳንስ አዚሞ ንግግሩ ልብን ያቀልጣል፡፡

ዘፈን ከነዘመድ አዝማዱ ጓዙን ጠቅልሎ በልቡ ውስጥ የሚኖር እስኪመስለን ድረስ ጊዜና ወቅት ጠብቀው ለጆሮዋችን የሚደርሱት ምርጥ ዘፈኖቹ ሁሌም እንወዳቸዋለን፡፡ መወደድም አለባቸው፡፡ ቴዲ አፍሮ በሚጣፍጥ ቅላጼው፣ ልዩ መስህብ ባለው የሙዚቃ አሬንጅመንት ከምርጥ ዘፈኖቹ ጋር አስረግጠን





እናውቀዋለን፡፡ ዘፈኖቹ የስሜት ህዋሳት ላሰው ፍጡር ሁሉ አስደሳችና ሞገደኞ፥ናቸው፡፡

ቴዲ አፍሮ ከጥበብ ፈጠራ ጋር የተሰገሰው ማራኪ የተፈጥሮ ችሎታ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ይህ ታላቅ የምድሪቱ ድምፃዊ የላቀ የህዝብ ፍቅር የተጎናፀፈ እውነተኛ የዘፈን አባት ነው፡፡

አርቲስቱ ጠንካራ ነው፡፡ የሚሰራቸው እያንዳንድ ስራዎች ጥንቃቄ የተሞላበት፣ ማስተዋል የታከለበት፣ በዲስትሌሽን እንደ ተጣራ ፈሳሽ ንፁህ እና እንከን አልባ ናቸው፡፡ ቴዲ ዜማም ይሁን ግጥም የመስራት ብቃቱ ሰብዙዎች አስገራሚ ነው፡፡

ይህ የሙዚቃ ብላቴና ራሱ ከሚያቀነቅናቸው ዘፈኖች በተጨማሪ ለብዙ አርቲስቶች የፈጠራ ውጤቱን ያበረከተ ስመጥር አርቲስት ነው፡፡ ቴዲ ወደ ሙዚቃው ዓለም ብቅ ካለበት ጊዜ አንስቶ ለበርካታ ድምፃውያን ስመ ገናና ሆኖ መውጣት አስቻጋሪ ሆኗል፡፡ የዚህ ዋነኛ ምክንያት ደግሞ አርቲስቱ በሚያበረክታቸው የዘፈን ጭብጦች የህዝቡን የልብ ትርታ ማዳመጥ በመቻሉ ነው፡፡ በቴዲ አፍሮ የገዘፈ ስም ተውጠው ማንነታቸው በህዝቡ ዘንድ ነጥሮ ያልወጣላቸው አንዳንድ ዘፋኞች ለቴዲ አፍሮ ጥሩ አመለካከት የላቸውም፡፡ ቴዲ ግን ማንንም ወዳድ ነው፡፡ ቢጠሉትም አይጠላቸውም፡፡ ከማንም ሰው ጋር መቃረንም ሆነ መቀያየም አይፈልግም፡፡ የሚጓዘውም በቀና መንገድ ነው፡፡ ‹‹የሚጠሏችሁን ሁሉ ውደዱ›› የሚለውን የአምላክ ቃል በተግባር የሚያሳይ ነው፡፡ ‹‹ቴዲ መጥፎ ነገርን የሚያስብበት ጊዜ የለውም፡፡›› አሁን ላለበት ትልቅ ደረጃ የደረሰው ጠንክሮ በመስራቱ ነው፡፡ ማንንም ለመብለጥና ተአምር ለመስራት ብሎ ሳይሆን ለሙዚቃ እድገት ሲል ነው፡፡ ሙዚቃን የሚሰራው በሙዚቃ ህይወት ውስጥ ባለ ዝነኝነቱን ማንም ሰው ቢሮጥ ቢንደረደር ሊደርስበት ከማይችልበት ቦታ አንጠልጥሎ ለመስቀል አይደለም፡፡ የአርቲስቱ የሁል ጊዜ ጥረቱ ጥሩ ስራን አምጦና ከሽኖ ለአድናቂዎቹ ማበርከት ነው፡፡

ድምጻዊው ዘፈን የሚሰራው ከፈጣሪው በተሰጠው የጥበብ ችሎታ ወገኑን ለማገልገል እንጂ ዝና ፈልጎ አይደለም። ብዙ ሰዎች እንኳንስ ዝናን ተችረው ትንሽ ዕውቅናን ሲያገኙ ጥጋባቸው አይቻልም። ‹‹ከእኔ በላይ ማንም የለም›› ሲሉ ይሰማሉ። ቴዲ አፍሮ ግን ታዋቂም ዝነኛም ሆኖ ይህ ባህርይ አልታየበትም። አጋጣሚ ሆኖ በስራም ሆነ በተለያዩ አጋጣሚዎች የስራ ባልደረቦቹን ሲያገኛቸው ‹‹እኔ የበላይ ነኝ›› ሳይል በእኩልነት ስሜት ተግባብቶ የሚኖር የብዙዎች ሞዴል ነው። ምቀኝነት ከጤነኛ አዕምሮ የማይመነጭ የእድገት ፀር ነው። በአርቲስቶች ዙሪያ አንዳንድ ችግሮች ቢኖሩም አንዱና ዋናው ግን እርስ በእርስ አለመከባበር ነው። እያንዳንዱ ዘፋኝ አንዱ ለሌላኛው እውነተኛ ፍቅር ቢኖረው ሙዚቃ አሁን ካለችው በላይ አብባ በፈካች ነበር።

በስራ የበለጠንን ሰው ብንመቀኝ በሃሳብ ብናብሰለስል ራሳችንን እንጎዳለን እንጂ ሌላውን አንጎዳም። ሁሉም ነገር የሚሆነው ከእግዚአብሔር ነው። ቴዲ አፍሮ ስለሙዚቃ ተሰጥኦው ሙዚቃ ህይወቴ በሚለው ዘፈኑ የተሰጠኝ ከላይ ሲል እንዳቀነቀነው ሁሉ። አምን ስራን የሚባርክ፣ ጤናን የሚሰጥ ፍቅርን የሚያሰብስ እሱ ነው።

በእርግጥ ዘፋኝ ሁሉ ዘፋኝ አይደለም። ሊባልም አይችልም። ቴዲ አፍሮ ግን ዘፋኝ፣ ደራሲ፣ አዋቂ፣ ብልህ፣ ጥበበኛና አስተዋይ ነው። ከሉ መልካም ባህሪ አንድ እንኳን ሳይኖረን ለምን ተበለጥን ብለን በከንቱ ብንጮህ መልሳችን የገደል ማሚቶ ይሆናል። ዘፈን፣ ዘፈን ነው። ዘፋኝነት ግን የውድድር መድረክ ሲሆን ይችላል። ስለዚህ ማሸነፍና መሸነፍ እንዳለ አምነን እንቀበል።

ማንኛውም ዘፋኝ የራሱ የሆነ የግል ችሎታ አለው። በተፈጥሮ ያገኘውን ችሎታ በግል ጥረቱ አሳድጎ እና አጎልብቶ ለስኬት መብቃት ይችላል። በባዶ ነገር ቴዲ አፍሮን ግን መሆን አይቻልም። አንድ ዘፋኝ ድንገት ተነስቶ ቴዲን ለመሆን ቢፈልግ ሊሆን አይችልም። የቴዲ ፍጥረት ለሙዚቃ ነው። የማይደርሱበትን





ዕቃ ለማውረድ ቆንጠራራት ትርፉ ድካም ነው።

ቴዲ በጣም ልዩ ዘፋኝ ነው። አፁብ ድንቅ፣ ማራኪ፣ መሳጭ፣ በሳልና ጠጣር መልእክቶችን በያዘው የሙዚቃ ሙያ ውስጥ ማስተላለፍ የሚችለው የልጅ አዋቂ የትልቅም ትልቅ፣ የአስተሳሰቡ ብስለት ከእድሜው በእጅጉ ፈጥኖ የሄደ፣ የብዙ ሚሊዮኖችን ቀልብ በፍቅር መግዛት የቻለው፣ በእውነትና በነጻነት መድረክ ላይ እንደ አንበሳ ደቦል የሚንጎማለል ብቸኛ ፍጡር ስለ እውነት ሲል የመከራን ፅዋ ቢጎነጭ መረረኝ የማይል ወደፊት በጀግንነት የሚጓዝ በልቡ ውስጥ ባደረው እውነት የሀሰትን የሾለ ጦር ሰባብሮ ለመጣል የሚንደረደር ልበ ቀና በሙዚቃ ውስጥ እውነትን መስበክና ማስተማር የሚችል ቁም ነገረኛ ነው። መቼም ቢሆን ሊበርድ የማይችል ትኩስ ብረት… ቴዲ አፍሮ የሰውን ልጅ ፍቅር እንካ ተብሎ የተሰጠው እስኪመስል የሁሉ ሰው ምርጫ ነው።

የቴዲን ፋና ወጊነት ገና አንድ ፍሬ ብላቴና እያለ ነበር የተንፀባረቀው። ደግሞም ከሚወደው ሙያ ጋር ጥብቅ ትስስር በመፍጠር በሚሰራው ስራ ትልቅ ተአምር ከመፍጠሩም በላይ ነጋ ጠባ ጥሩና የተሻለ ነገርን ለመስራት ደፋ ቀና በማለት የሚተጋ ጥበባዊ ሠው ነው።

አርቲስቱ ጠንቃቃና ብልሃተኛም ጭምር ነው። አንድን ስራ ሠርቶ ለህዝብ ከማቅረቡ በፊት ደጋግሞ የሥራውን ልኬት የሚመዝን ጥበበኛ ነው።

ቴዲ እንኳንስ በሙያው ቀርቶ በተፈጥሮ ባህሪይውም መልካም ፍጡር ነው። ጥቂቶች እና አንዳንድ ዘፋኞች ቴዲ አፍሮን በጥቁር ዓይን ከማየት ይልቅ የእርሱን የጥበብ እጠቃቀም፣ ዘዴና ብልሃቱን በማጤን እንደሱ መሆን ባይቻል እንኳን ጥሩ ነገር ለመስራት ቢነሳሱ መልካም ነው። ቴዲ እኮ የድምጽ ስራ ለመስራት (ቮካል) ልምምድ ሲያደርግ ጊዜና ሰዓቱን ሳይሰስት በቀን ከአራት እስከ ስምንት ሰዓትና ከዚያ በላይ የሚሰራ ነው። እንደሱ ጠንክረን

ሳንሰራ ቴዲን በሙዚቃ መብለጥ ይከብዳል፡፡ ቴዲ አፍሮ ታላቅ በሆነው የሙዚቃ ውቅያኖስ ውስጥ ዘወትር የሚቀዝፍ የጥበብ ጀልባ ነው፡፡

በተፈጥሮ የተሰገሰው የጥበብ ሞያ ስላለው ሁልጊዜ እንደ ወንዝ ዳር አበባ ያብባል እንጂ እንደበርሃ ቅጠል በቀላሉ አይጠወልግም፡፡ ማንም ሰው በያዘው ሙያ ላይ ጠንክሮ ከሰራ የልፋቱን ውጤት አያጣም፡፡ እናም የቴዲን ውድቀት የሚመኙ አርቲስቶች ይህ ሃሳባቸው ስይጣናዊ ስለሆነ የሚጓዙበትን መንገድ ረጋ ብለው ሊያጤኑትና በጥልቀት ሊያስቡበት ይገባል፡፡

ዛሬም ነገም እስከ መቼም ቴዲ "ቅንነት መልካም ነው" ብሎ የሚያምን ስለሆነ ማንንም አይቀየምም፡፡ ሁል ጊዜ ደግ ነገርን ማድረግ የለመደ አዕምሮው ለተንኮል ቦታ የለውም፡፡ ስለዚህ የበለጠንን ሰው የማክበር ባህል እናዳብር፡፡

በተቃራኒ መንገድ እጅግ በጣም የሚገርሙ አርቲስቶችም አሉ፡፡ የቴዲ አፍሮን የሚደንቅ ችሎታ አምነው በዋለበት መዋልን የሚሹ፣ ባመሸበት ለማምሸት የሚፈልጉ፣ የቴዲን ታላቅነት የሚመስክሩ አሉ፡፡ ሰው፤ ሰው በመሆኑ ብቻ ሊከበር ይገባዋል፡፡ በሚሰራው ስራ በልጦ ከተገኘ ግን የእርሱን ፈለግ በመከተል ለመስራት መነሳሳት ብልህነት ነው፡፡

ለቴዲ አፍሮ ጥቂት ዘፋኞች ጥሩ አመለካከት የላቸውም ተብሎ ቢነገርም ሁሉም አለመሆናቸውን ሊስመርበት ይገባል፡፡ ምናልባት የሚራመድበት የእውነት ጎዳና ያልተመቻቸው እውነትን የጠሉ ሀሰተኞች ካልሆኑ በስተቀር ቴዲ አፍሮ የሁሉም ሰው የአይን ስስት ነው፡፡ ቴዲ አፍሮ ለሙዚቃ ፍቅር ሲል ስቃይና መከራ ያልገደበው አቋመ ፅኑ ስለ መሆኑ ዛሬ ላይ ቆመን ሳይሆን ወደ ኋላ መለስ ብለን በመመርመር መናገር እንችላለን፡፡

ማንም ሰው በፈለገው ጊዜና ሰዓት ካሴት መስራት ይችላል፡፡ ሆኖም መዝፈን ላይሳካለት ይችላል፡፡ ቴዲ አፍሮ ግን ወደ ሙዚቃው





አለም ሲቀላቀል ጀምሮ ዘፈን እንጂ ካሴት ይዞ አልመጣም፡፡ ‹‹ሙዚቃ ድቅድቅ ጭለማን ጥሶ የማለፍ ኃይል አላት፡፡ ሙዚቃ አልወድም የሚል የሰው ፍጡር ካለ ሰው መሆኑ ያጠራጥራል፡፡››

ስለዚህ ምቀኝነት የእድገት ፀር እንደሆነ እንወቅ፡፡ የበለጠንን ሰው በቅናትና በስም ማጥፋት ልንበልጠው አንችልም፡፡ እሱ ራሱን ሆኖ ለዚህ እንደበቃ ሁሉ ሌላውም እራሱን ሆኖ ራሱን ያግኝ፡፡

አንድ ዘፋኝ ክመሬት ተነስቶ ከቴዲ አፍሮ አላንስም ቢል መብቱ ነው፡፡ ማውራት ቀላል ነውና፤ እውነታው ግን እንኳንስ ቴዲ አፍሮን መሆን ለመወዳደር ማሰብም ሊከብድ ይችላል፡፡ ቴዲ በሀገራችን ለሚገኙት ዘፋኞች መከበሪያቸው ነው፡፡ ተወደደም ተጠላ በሙዚቃ ህይወት የበላይ ሆኖ ነጥሮ የወጣ ድንቅ አርቲስት ነው፡፡ መቅናት የሚገባን መንፈሳዊ ቅዱስ ቅናት ነው፡፡

የበለጠንን ልናከብርና የበላያችን እንደሆነ በልባችንና በአንደበታችን ልንመሰክር ይገባናል፡፡ የቴዲን የፈጠራ ስራ ዜማና ግጥሞች እየተቀበልን ‹‹ቴዲ በምንም ነገር አይበልጠንም›› ብሎ በድፍረት መለፍለፍ እጅግ አሳፋሪ ነው፡፡ ቴዲ በታላላቅና አንጋፋ ሰዎች፣ በሙዚቃ ጠበብቶችም ሳይቀር የተመሰከረለት ብቁ አርቲስት ነው፤ ደግሞም ማንም ባይመሰክርለት ገድለኛ ስራዎቹ ራሳቸው አፍ አውጥተው ይናገሩለታል፡፡

## ከዙፋኑ አይወርድም!

በሀሜት በተንኮል

ቢመጡም በሴራ

ከዙፋኑ አይወርድም

ቴዲ ማን ሊፈራ

ምን ቢዶለት ምን ቢወራ

ምን ቢጉነጉን የተንኮል ዳራ

ምን ቢጨፈር ቢረገጥ ዳንኪራ

ምን ቢሰክር በሐሜት ፈጠራ

ከፈጣሪ ከተሾመ

ነገስ በቃ አከተመ።





# 18

# የቴዲ አፍሮና፣ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ምናባዊ ቆይታ

*ዝናን በአግባቡ ለማይዝ ዝነኛ ሰው*
*ዝና የመውደቂያው ጦስ ነች*

እለቱ ሀሙስ ነው። ቀኑ ደስ ይላል። ሰማዩ ጥርት ብሏል። የአየሩ ሁኔታ ለሰው ልጆች ተስማሚ ነው። በአጋጣሚ ከጓደኛዬ ጋር በእግራችን “ወክ እየበላን” ከሰፈራችን ኦሎምፒያ መስቀል አደባባይ ደርሰናል። መስቀል አደባባይ መንገድ ልናቋርጥ የእግረኛ ማቋረጫ ወደ ሆነው የዚብራ ምልክት በመጠጋት ላይ እያለን ከመጣንበት መስመር አካባቢ አንድ ዘመናዊ መኪና አይቼ ቆምኩ። ይች የማላውቃት የቤት መኪና በከፍተኛ ፍጥነት እየከነፈች ትመጣለች። በመስቀል አደባባይ አካባቢ ከወትሮው ለየት ባለ ሁኔታ የሰው ብዛት

ይታያል። የመኪናዋ ዘመናዊነት ገረመኝ።

ልቤ በእልህና ቁጭት ‹‹ይህች መኪና የኔ ብትሆን›› የሚል ስሜት ፈጠረብኝ። ህዝቡ ማፏጨትና ቴዲ፣ ቴዲ የሚል ድምጽ ማሰማት ጀመረ። መንገድ የሚያቋርጠው እግረኛና መኪናዎች በያሉበት ቦታ ቦታቸውን ይዘው ቆሙ። ብዙም ሳይቆይ ነገሩ ገባኝ።

ቴዲ የሚለው ስም አዲስ አልሆነብኝም። ቢሆንም ግን ማረጋገጥ ስለነበረብኝ አብሮኝ የነበረውን ወዳጄን ‹‹ቴዲ ማን ነው?›› አልኩት።

‹‹ቴዲ አንበሳው የኢትዮጵያ ምርጥ ዘፋኝ ነዋ›› አለኝ።

የህዝብ የአድናቆት ጩኸት በረታ። ‹‹ቴዲ እንወድሃለን!››፣ ‹‹የዛሬውና የነገው የኢትዮጵያ የሙዚቃ ተስፋ!›› ሌላም፣ ሌላም የሚገርም ቃል እሰማለሁ።

ያች ዘመናዊ መኪና ከአጠገባችን ደረሰች። ቀይ፣ መልከ መልካም፣ ጠቆር ያለ መነፅር በአይኖቹ ላይ ያጠለቀ ከአንገቱ ጎንበስ በማለት ለአድናቂዎቹ የከበረ ሰላምታን አበረከተላቸው። የለበሰው ልብስ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የሚያንጸባርቅ በሶስት ቀለማት ያሸበረቀ ነው። የልቤ ምት ጨመረ። ግንባሬ ላይ ላብ ችፍ አለ። ይሄንን ታላቅ ሰው ለመከተል አሰብኩኝ። አጋጣሚ ሆኖ ታክሲ አገኘሁ። የታክሲውን ሹፌር ‹‹በእናትህ በፍጥነት ንዳው! ያችን መኪና ተከተላት!›› ብዬ ተማጸንኩት።

የታክሲው ሹፌር “ለምን? ምን ሆነሃል?” ብሎ ጠየቀኝ። ምንም መልስ ሳልሰጠው የቴዲን መኪና መከተል ጀመርን። ወደ ግዮን ሆቴል አመራች። ቴዲ አፍሮን ደረስኩበት።

ያችን ዘመናዊ መኪና ከአንድ የሚያምር አረንጓዴ ዛፍ ስር አቁሞ ወደ አንድ ፀጥ ወዳለ አዳራሽ አመራ። ተከተልኩት። ዞር ብሎም አላየም።



ፊ



ወደ አዳራሹ ለመግባት አመነታሁ። ስገባ የቀድሞው የኢትዮጵያ ንጉስ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ቁጭ ብለዋል። ቴዲን ሲያዩት ከተቀመጡበት ተነሱ። መላ ፊታቸውም በደስታ ተዋበ። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ቴዲ ለአይን የሚማርክ በወርቅ የተለበጠ መቀመጫ ላይ ተቀመጠ።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴም ለድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን ያደረጉለትን አቀባበል ባየሁ ጊዜ ማመን ነበር ያቃተኝ። ‹‹እውነትም ቴዲ ታላቅ ሰው ነው›› አልኩ። ከተራው ሰው ጀምሮ እስከ ትላልቅ ሰዎች የሚሰጡት ክብር ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም ብዬ አሰብኩ።

የውይይታቸውን ምዕራፍ የከፈቱት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ነበሩ። ጣታቸውን ወደ ቴዲ ቀስረው ‹‹አንተ የሀገር ኩራት ለወገንህ ሀሳቢና ተቆርቋሪ የፍቅርና የአንድነት መገለጫ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ነህ። በእናትህ ማህፀን እያለህ ነው እግዚአብሔር የባረከህ። በተለይ የማታውቀውን ነገር ለማወቅ የምታሳየው ያላሰለሰ ጥረት ይደነቅልሃል። ያንተ መፈጠር ለዚህች ምድር ለበጐ ነው። ገና ብዙ ትሰራለህ። የዚህች ሀገርም መልካም ስጦታዋ ነህ። ከፈጣሪ በተሰጠህ የጥበብ ሙያ በሚያምረውና ልብን በሚያቀልጠው ማራኪው ድምፅህ ለሀገርህና ለወገንህ የምታበረክታቸው ህያው ስራዎችህ ያንተን ማንነት ያስረዳሉ።››

ቴዲም በድንገት ከተቀመጠበት በመነሳት "ጃንሆይ ሙዚቃ ለእኔ ህይወቴ ነች። የልቤን እውነት የምሰብክባት በነፃነት ሀሳቤን የምገልፅባት የአምላኬ ልዩ ስጦታዬ ነች። ከፈጣሪ በተሰጠኝም ሙያዬ ሀገሬንና ወገኔን አገለግላለሁ።›› በረጅሙ ተነፈሰ…… ከተነሳበት የሚማርክ ወንበር ላይ መልሶ ተቀመጠና ንግግሩን ቀጠለ፣

‹‹እውነትን ከመናገር ወደኋላ አልልም። ከሀሰት ጋር ህብረትን አላደርግም።››

ቴዲን ‹‹ይኸውልህ ልጄ›› አሉት ጃንሆይ። ‹‹ለበርካታ ጊዜ ልብ ብንለ ተመልክተንሃል። ለያዝከውም የጥበብ ሙያ ልዩ ፍቅር ያለህ ነህ። ቅንነትን የምትወድ፣ በፍቅር የምታምን፣ ሰላምን አብዝተህ የምትሻ፣ ለኢትዮጵያ ከፈጣሪ የተሰጠህ በረከቷ ነህ። አንተ በምታቀነቅናቸው የዘፈን ስራዎች ብዙ ነገሮች ይለወጣሉ።

‹‹ልብ በለኝ ልጄ .... ዝናን በአግባቡ ለማይዝ ዝነኛ ሰው ዝና የመውደቂያው ጦስ ነች። አንተ ግን ወገንህን አብዝተህ የምትወድ፣ ለሀገርህና ለባንዲራህ የምትቆረቆር፣ ታላቅ ዝና አለኝ ብለህ ራስህን በትዕቢት ያልወጠርክ፣ ሀሳብህ ሁሉ ቅን የሆነ፣ ለስኬታማነትህ ቀን ከሌሊት የምትጥር፣ የአንበሶች አንበሳ ነህ። ቅንነት መልካም ነው ብለህ ሁሉን ነገር በበጐ የምትቀበል የፍቅር ሰው ከመሆንህም በላይ ለሠዎች መልካም ተምሳሌት ነህ።››

ቴዲ የቀኝ እጁን ጉንጩ ላይ አስደግፎ የጃንሆይን ንግግር ልብ ብሎ ያዳምጣል። በድንገት ‹‹እግዚአብሔር ታላቅ ነው። ሀይልና ብርታቱም ከማንም በላይ ነው›› አለና ከተቀመጠበት ተነስቶ ፊት ለፊት የተቀመጠውን ባንዲራ አነሳ።

‹‹ጃንሆይ ገና ወደ ፊት የሚገርሙና የሚደንቁ ወርቃማ ስራዎችን እንደምሰራ አምናለሁ። ከልጅነቴም ጀምሮ ትልቅ ትልቁን ነው የምመኘው። የምመኘውንም ነገር ሁሉ እውን ለማድረግ እጥራለሁ። ከሁሉም በላይ በእኔ ልብ የነገሰው ፈጣሪዬ ብርታቴ ስለሆነ ህልሜን እውን ያደርግልኛል።›› ቴዲ ያነሳውንም ባንዲራ ከፍ አድርጐ ‹‹ይህ ባንዲራ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አለበት›› ብሎ በሀሳብ ሲቆዝም፣

ግርማዊ ቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ከተቀመጡበት በወርቅ ከተለበጠው ወንበር ላይ ሆነው የለበሱት ነጭ በነጭ ልብስ ግርማ ሞገስን አከናንባአቸዋል። ብዙ ጊዜ ቴዲን ሲጠሩት "ልጄ" ብለው ነውና ‹‹ልጄ›› አሉት። ቴዲም ‹‹አቤት›› ለማለት ሰከንድ አልፈጀበትም ነበር።





‹‹ለአንተ የበራልህን እውነት ለሌሎችም እንዲበራላቸው ፀልይ።›› በቀኝ ጣታቸውም ወደ ሰማይ ላይ እየጠቆሙ ‹‹እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይወዳታል። ሀገራችን እንዲህ ሆና የምትቀር እንዳይመስልህ። ኢትዮጵያ የአለም ትንሳኤ ከመሆኗም በላይ በአለም ላይ ካሉ ሀገሮች በበለጠ ሁሉ ሰው ለመኖሪያነት ይመርጣታል። እንደ አንተ አይነት ጠንካራ፣ ልባም፣ ብርቱና አስተዋይ ለዚህች ሀገር ይብዛላት። የአንድን ሰው የአዕምሮ ብስለት በአንደበቱ ንግግር መለካት ይቻላል። እስከ አሁን ልብ ብዬ እንደሰማሁህ ከአንደበትህ የሚወጡ ቃላት የአንተ ማንነትና ብስለትህን ያስረዱልሀል።

‹‹ልጄ፣ ሀገርህን አብዝተህ ውደድ። ኢትዮጵያ አይኖቿን ከአንተ ላይ አታነሣም። ባንዲራውም አፍ ቢኖረው ስለአንተ ከመናገር ወደኋላ አይልም ነበር።››

ቴዲ አፍሮ ለበርካታ ህዝብ የሚገርመው ከመናገር ይልቅ አድማጭነቱ ነው። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴም ይህንን ባህሪውን አብዝተው ወደዉታል። ብዙ ሰዎች ከማዳመጥ ይልቅ መናገርን የሚሹ ናቸው። አንድ ሰው አዋቂ ነው ወይንም ነገሮችን በጥልቀት ይመለከታል የሚባለው ብዙ በአወራና በተናገረ ቁጥር ሳይሆን አድምጦ ካገናዘበ በኋላ የሚናገር በመሆኑ ነው።

‹‹በተደጋጋሚ ከልባችን ሆነን በማስተዋል አይተንሃል። ከመናገር ይልቅ መስማትን ታዘወትራለህ። በነገሮች ሁሉ ቅን እንድትሆን የረዳህን እግዚአብሔን አመስግነው። የዚህ አይነት ልብ እንዲኖርህ በምክሩ ለቀረፀህ አባትህ ካሳሁንንም አመስግን።››

የቴዲ ሁለቱም ዓይኖች እምባ አቀረሩ። ቀና ብሎ እንኳን ጃንሆይን ለማየት ጉልበት አነሠው። ‹‹አባቴማ›› አለ። ‹‹ማንም ሊያገኘው የማይችል ውድ አባት ነበር። ግን ከፈጣሪ አልጣላም። እሱ ይሠጣል፣ እሱ ይወስዳል። አውቃለሁ በስጋ ከስሬ ቆሞ ባላየውም ከመንፈስ ግን ለአፍታ እንኳን ከህሊናዬ አይጠፋም። ለእኔ ለልጁ

ሲል ማንም ሊሆን የማይፈልገውን ነገር ሁሉ ሆኖልኛል።›› በአይኖች ከረጢት የተንቆረዘዙት የእንባ እክብሎች ግን ከመፍሰስ ማንም ሳያግዳቸው በጉንጩ ላይ እንደ ግድብ ውሀ በየፊናቸው ተንጠባጠቡ።

ጃንሆይም ከቴዲ አይኖች የሚፈሰውን እንባ ባዩ ጊዜ ድንጋጤ ተሰማቸው። ‹‹ልጄ ምን ነካህ? እሱ እኮ ያለው ያማረ ስፍራ ነው። ቦታው ለዓይን የሚማረክ፣ አየሩ የማይጠገብ፣ ችግር የለ ረሀብ፣ ሁሌ ደስታ፣ ሁሌ ዝማሬ ካለበት ስፍራ ውስጥ ነው ያለው። ይልቁንስ አባትህ የሰጠህን ምክር አስበህ ከአንተ ስር ለሚገኙት ፍሬዎችህ አንተም እንደ ካሣሁን ታሪክን ንገራቸው። ኢትዮጵያን እንዲወዱም አስረዳቸው።

‹‹እንደ አንተ አይነት ሰው ለዚች ሀገር ይብዛላት። ከመኮነን ይልቅ ማስተማርን የሚመርጥ ማንም የለም። አንተ ግን ልዩ ነህ። ያንተ ሀሳብ ላልገባቸው ወገኖች ጊዜ ይነግራቸዋል። ማንም ሠው በበረታ ቁጥር ከፈተና ፈተና ይከተሉታል። ስለሆነም ልብህን አጠንክር።››

ቴዲ አፍሮ የሬጌው አቀንቃኝ ጃማይካዊው ቦብ ማርሌይ እና ሀይለ ስላሴ አፍሪካን አንድ ለማድረግ ያደረጉት ያላሰለሰ ጥረት ሰርክ እንደ አዲስ ይገርመዋል። ይህ እውን ሆኖ ማየት ምኞቱም ጭምር ነው። ኃይለሥላሴና ቦብ ማርሌይ አፍሪካን አንድ ለማድረግ ከፍተኛ መስዋዕትነት እንደከፈሉ በወቅቱ የነበሩ እማኞችና በምስል የተደገፈ ምስሎች አስረጅዎች ናቸው። በእነኚህ ሁለት ታላላቅ ሰዎች የተጀመረው በጎ ሀሳብ ዛሬ ላይ ጥሩ ነገር እያየን ነው።

የኃይለሥላሴን ሀሳብ በሙሉ እምነትና ወኔ የሚጋራው ቦብ ማርሌይ በሔደበትና ባረፈበት ሀገር ሁሉ አፍሪካ አንድ ነች እያለም ይናገር እንደነበር አንዳንድ ምንጮች ዛሬ ላይ ይመሰክሩለታል። በተለይ በሚያቀርበው ማንኛውም ረቂቅ ዜማ ላይ ይህንን ሀሳብ ያንፀባርቅ ነበር። አሁንም ቢሆን የአርቲስቱ አድናቂዎች ለዚህ ቅዱስ አላማ እየታገሉለት ይገኛሉ።





ኃይለሥላሴም ቢሆኑ በዚህ ምግባራቸው የአፍሪካ አባት እስከመባል የደረሱ ታላቅ ንጉስ ነበሩ። የሀገራችን ብርቅዬ የሙዚቃው ፈርጥ ቴዲ አፍሮ ለእነኝህ ታላላቅ ስራን ለሰሩ ሰዎች ለክብራቸው አዚሟል። ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በህይወት እያሉ አፍሪካን አንድ ለማድረግ በቁጥር አንድ የታገሉ ታሪካዊ ንጉስ ናቸው። በህይወት ዘመናቸውም የሰሩት ታላቅ ገድል ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተወራረሰ ለዘለአለም ይኖራል። ታሪክ የማይረሳውን ታሪክ መስራት የስኬት ውጤት ነው።

ቴዲ ከጥቂት ዝምታ በኋላ ‹‹እርሶ ታላቅ ሰው ነዎት።›› ለሀገራችን ኢትዮጵያ ብዙ ነገር አድርገዋል። አፍሪካ አንድ ነች እያሉ እንደታገሉም ታሪክ ይመሰክርልዎታል። ለመሆኑ ስለዚህ ቅዱስ አላማዎ እስኪ ትንሽ ያውጉኝ›› አለ።

ጃንሆይ መሬት መሬት እያዩ ‹‹አሁንም ቢሆን አፍሪካ አንድ ነች። በዘመናችን ሁሉ የማንወደው ነገር ቢኖር በነጮች ተረግጦ መኖርን ነው። ይህንን ሀሳባችንን መላው የሀገራችን ህዝብና አብዛኛው የአፍሪካ ሀገሮች ይጋሩታል። መቼም ቢሆን ከልባችን የማይጠፋው ጃማይካዊ የሬጌ አቀንቃኝ ቦብ ማርሌይ በጥበብ ሙያው የአፍሪካን አንድነት በአለም ላይ እየዞረ ሰብኮልናል።›› በድንገት ከተቀመጥኩበት ተነሱና ‹‹ቴዲ አደራህን በሙዚቃ አፍሪካን አንድ አድርጋት። እግዚአብሔር ደግሞ የበለጠ ይረዳሃል!! በእርግጥ ከፊት ለፊትህ ቀላል የማይባሉ ፈተናዎች አሉ። ቢሆንም በልብህ ተደላድሎ በተቀመጠው ጥንካሬ ታልፈዋለህ›› አሉትና ንግግራቸውን ቀጠሉ።

‹‹እግዚአብሔር ባንተ ላይ አላማ አለው። እስካሁንም ያሰፍካቸው የህይወት ፈተናዎች ያንተን ማንነት ላንተ ትቼልሀለሁ›› ብለው ከተነሱበት መልሰው ተቀመጡ።

‹‹ሀገራችን ኢትዮጵያ ለፈጣሪዋ ቅርብ ነች። ህዝቧም በፀሎት የታጠቀ አማኝ ነው። እኔን ግን ዘወትር የሚያንገበግበኝ ምስኪኑ የሀገሬ ሰው ከችግር መቼ እንደሚላቀቅ ነው›› ብሎ ቴዲ በሀሳብ ሲቆዝም…

ጃንሆይ ‹‹ሀገሩን ከሚወድ፣ ወገኑን ከሚያፈቅርና በንፁህ ልቦናው ቅንነትን አብዝቶ ከሚሻ ሰው ከአንደበቱ የሀገሩና የወገኑ ጉዳይ አይጠፋም። ማርያምን እልሃለሁ የኢትዮጵያ ትንሳኤ እሩቅ አይደለም። አንተ የምትናገራት እያንዳንዱ ቃል ከመሬት ጠብ አትልም። በምትሰራው የዘፈን ስራ ሁሉ የአሁንም ሆነ የወደፊቱን ትውልድ ዘፋኝ ብሎ የሚጠራህ አይኖርም። ትላንት ላይ ቆሞ የወደፊቱን የተናገረ ትንቢተኛ ይሉሀል። የፈጣሪ ቅዱስ ቅባት በአንተ ዘንድ አለ። ነብስህ ሁሉን ነገር በቅንነት ስለምታደርግ እውነት ደግሞ ለማደሪያዋ ትመርጥሃለች። አንተን ያለ መውደድ ከባድ የሚሆንበት ሰዓቱ ደርሷል። ኢትዮጵያም አይኖቿን ሳትጨፍን ዘወትር አንተን ታይሀለች።››

የለበሱትን ነጭ ካባ አውልቀው ቴዲን አለበሱት። በቀኝ እጃቸው የያዙትን የወርቅ ዘንግ ደግመው ሰጡት። የወርቅ ዘንጉ አናት ላይ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ተንጠልጥሎበታል። ቴዲ በነገሩ ግራ የገባው ይመስላል። ይሄኔ ‹‹አንተ ለኢትዮጵያ ህዳሴ ነህ። በምትሰራቸው ውብ ዜማዎችህ ፀበኞች ይታረቃሉ። የተሳለ ሰይፍም ይጣላል። ምህረትና ይቅርታም ይበዛል›› አሉትና ጃንሆይ ከወንበራቸው ስር የነበረውንም መጽሐፍ ቅዱስ ሰጡት። ‹‹ቀሪውን እራሱ የሁሉ ነገር ባለቤት የሆነው ፈጣሪ ይፈፅመዋል›› ብለው የቴዲን ግንባር ሶስት ጊዜ ሳሙት።

ፊታቸውንም ወደ ፀሀይ መውጫ አዙረው ለሶስት ደቂቃ ፀለዩ። ቴዲም ከጃንሆይ የተሠጠውን የአምላክ ቃል መጽሐፍ ቅዱስ አትኩሮ እየውናጎንበስ ብሎ በአክብሮት ሳመው።

በዚያች ቅፅበት ‹‹ከዚህ ሀገር አልፈህ ድንበርና ኬላ ሳይወስንህ ለአፍሪካና ለአውሮፓ ታላቅ ሆነህ ትገለጣለህ። በዚህም ሀገር ካለፈውም ከሚመጣውም መቼም ቢሆን እንዳንተ ያለ አይፈጠርም›› ብለው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተናገሩ።

ቴዲ አይኖቹ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ አልተነቀሉም።





በዚህ ምናባዊ ቆይታ ላይ እንደተረዳሁት ከሆነ ቴዲ ለሀገሩ ያለው ፍቅር እውነተኛ እንደሆነና አርቲስቱ ገና ወደፊት ብዙ ተአምራትን እንደሚያከናውን ነው። እኔም በአጋጣሚ እዚያው ተገኝቼ ይህንን የመሰለ ታሪክ ለማየት በመብቃቴ ደስታዬ ወደር የለውም።

## ኤሴቅ

"ሄልሎሄ እያሉ በፍቅር ማልቀስ

ለእኔ ንግስና ነው ባንዲራ መልበስ"

አለና ቴዲ አፍሮ

ኤሴቅ በሆነበት በሁሉም ከተማ

"እንፋቀር" ሲል አወጀ በግጥም በዜማ

በተሰጠው ጥበብ መቻቻልን አስተምሮ

በርቱዕ አንደበቱ የፍቅርን ኃያልነት መስክሮ

"ለላም ነው ምኞቴ!" አለ ሃዋርያው ቴዲ አፍሮ።

እናም ጥላቻ ተወግዶ - ፍቅር ሰፍኖ

ሽኩቻ ኤሴቅ ታሪክ እንዲሆን ተረስቶ

"ህልም አለኝ" አለ "በሀገሬ ፍቅር ነግሶ"

በዚህ የተነሳ ሰንደቅ ዓላማውን እንደ ልብስ ተጐናጽፎ

ቴዲ አፍሮ ወደቀ በጣም ተሸንፎ

ስለፍቅር ሊሞት ከፊት ተሰልፎ።

### ቴዲ አፍሮ ከሌሎች ዘፈኞች የሚለይባቸው ጥቂት መስፈርቶች

- የሚያቀነቅናቸው ዘፈኖች በሙሉ የዜማና የግጥም ባለቤት እራሱ መሆኑ
- ዘፈኖቹ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሀገራዊ፣ ፍቅርንና ትላልቅ አንጋፋ ሰዎችን የሚያወድሱ በመሆናቸው
- መድረክ ላይ በግርማ ሞገስ የሚንቀሳቀስ፣ በምትሀተኛው ክህሎቱ የሚቆጣጠር፣ ሳቂታና ታዳሚውን ለማስደሰት ከልቡ የሚጥርና በየመሀሉ ምክሮችን የሚያስተጋባ በመሆኑ
- በተለየ አኳኋን ከፍተኛ የህዝብ ፍቅርን በማትረፉና ከሀገር ውጭም የተፈላጊነቱ መጠን በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ
- ከዘፈን ሌላ የልዩ ልዩ ተሰጦኦዎች ባለቤት ጭምር መሆኑ
- በፈጣን የፈጠራ ችሎታውና ከያኒነቱ
- በማንኛውም ሀገራዊና ወገናዊ ችግር ላይ በግንባር ቀደምትነት መሰለፉ
- ብልህ፣ አዋቂና አስተዋይ በመሆኑ. . .





# ክፍል አምስት

# የቴዲ አፍሮ ታላላቅ ፈተናዎች

## ‹‹ለአንበርካኪዎች አልንበረከክም ማለት የብልሆች ልዩ ጥበብ ነው!››

*ጎህ ቀዶ ጽልመቱ እንደሚበራ*

*ደመናው ተገፎ ሰማዩ እንደሚጠራ*

*እያደር የሚገለጥ እያደር የሚያበራ*

*አለው ቅኔ፣ አለው ምስጢር የቴዲ ምጡቅ ሥራ!*

# 19

# ‹‹እግዚአብሔር በክፉ አይፈትንም››

መከራ አይብዛ እንጂ በመከራ ውስጥ ማለፍ መልካም ነው። የጣፋጭን ጣዕም የምንለየው የመረረ ነገርን ቀምሰን ስናጣጥመው ነው። ወርቅም በእሳት ከተፈተነ በኋላ ነው ወርቅነቱ የሚለየው።

በ1993 ዓ.ም. መጨረሻ አካባቢ ምርጥ አልበሙን ለህዝብ ጆሮ ካደረሰ በኋላ ብዙም ውሎ ሳያድር በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ ተቀባይነትን የተቀዳጀውና "ዘመን የፈጠረው ታሪከኛ አርቲስት" ተብሎ የክብር አክሊል የደፋው ታላቁ የጥበብ ሰው ቴዲ አፍሮም ወርቅነቱን በእሳት ተፈትኗል። እንግዲህ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለመዳሰስ የምንሞክረው የአርቲስቱን አንዳንድ ፈተናዎች ይሆናል።

## 1. ጡት ላይ ፈረመ

ወጣቱ ድምጻዊ ቴዲ አፍሮን በመንገድ ላይ፣ በሬስቶራንቶችም ሆነ ሙዚቃውን በሚያቀርብባቸው ኮንሰርቶች ላይ ወረቀትና እስክሪብቶ በመያዝ "ቴዲ እንወድሃለን፣ ፈርምልን" የሚሉ





የአድናቂዎቹ ብዛት ሕልቆ መሳፍርት የለውም። በግንባርና ስልክ በመደወል የፍቅር ጥያቄ የሚያቀርቡለት ወይዛዝርቶችም በርካታ ናቸው። ይሁንና ቴዲ ቆርጦ የተነሳው በሕይወት ዘመኑ ውስጥ ደማቅ ታሪክን ለማስመዝገብና ታላቅ ሥራን ለመስራት ስለሆነ፣ እንዲሁም የዛሬን በማሰብ የነገን የሚያልም የብዙዎች ሞዴልና ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ በመሆኑ ሁሉንም የፍቅር ጥያቄዎች እንዳመጣጣቸው መልሶአቸዋል።

ሐቁ ይህ ሆኖ ሳለ ግን፣ ከብዙ ልፋትና ጥረት በኋላ ስኬታማ የሆኑትን የህዝብ ጀግኖች ለማሸማቀቅና ለመኮርኮም ዕንቅልፍ አጥተው የተንኮል መረብ ሲሸርቡ የዕድሜ ጀንበራቸውን የምትጠልቅባቸው አንዳንድ ከንቱዎች "ጡት ላይ ፈረመ" የሚል የሀሰት ወሬ ያናፍሱበት ጀመር። ይህንን አሳዛኝ ወሬ የሰሙ አድናቂዎቹ ግን ወሬው የምቀኞች ተራ የጥላቻ ወሬ መሆኑን በመገንዘብ ወዲያውኑ "ቴዲ አያደርገውም" ሲሉ ተደምጠዋል።

ቴዲም ስለዚህ ጉዳይ ተጠይቆ እንዲህ በማለት መልስ ሰጥቶ ነበር።

‹‹እኔ የአበሻ ልጅ ነኝ። የሀገሬን ወግና ባህል ጠንቅቄ አውቃለሁ። ይህንን የማደርግ ፍጡር አይደለሁም። አባቴም በስነ ምግባር ቀርጾ ነው ያሳደገኝ። ደግሞም እግዚአብሔርን እፈራለሁ።››

አዎ በወቅቱ ወረቀትና እስክሪብቶ ይዘው ቴዲ ጋ በመሄድ ‹‹እንወድሃለን፣ በስራኸውም ስራ እናደንቅሃለን፣ ፈርምልን›› ለሚሉት አድናቂዎቹ ‹እኔ ማን ነኝ? ምንስ ሰርቼ ነው የምፈርመው። ለእንደዚህ አይነቱ ክብር ገና አልበቃሁም› በማለት እራሱን ዝቅ ያደርግም ነበር። ያም ሆኖ ግን ‹‹የፈጣሪ ክቡር ፍጡር ላይ አልፈረምኩም። የሰው ልጅ ክቡር ነው›› ሲል እውነታውን ተናግሯል።

ቴዲ አንድ ሰው ነው። ማፍቀርም ሆነ ማግባት የሚችለው አንዲት የሀገሩን የሄዋን ዘር ነው። ለዚያውም ከፈጣሪው

የተሰጠችውን እውነተኛ አጥንቱን።

ቴዲ የሚያደርገውን የሚያውቅ ከማድረጉም በፊት ደጋግሞ የሚያስብ ብልህ አእምሮ ያለው አርቲስት ነው። በተጨማሪ መነሻውን የሚያውቅ፣ መድረሻውን የማይረሳ፣ የሀገርና የወገን ኩራት ነው። ቴዲን አልባሌ ቦታ አገኘሁት ማለት እንደ ውሃ ሽታ ይቆጠራል። ቴዲ አፍሮ ፍፁም ነው፤ እያልኩኝ ሳይሆን የሚሰራውን የሚያውቅ ጠንቃቃ ነው።

ቴዲ በቀደሙት ዘመናት በሴቶች ላይ ይደርስ የነበረውን የባህል ተፅዕኖ አጥብቆ የሚቃወም፣ ብሎም ሴት ልጅን ከምንም በላይ የሚያከብር ሰው ነው። ደግሞም የሀገራችን ሴቶች ጠንቃቃ ናቸው። አስተዋይም ጭምር። ለምንም ነገር ቢሆን ለተልካሻ ነገር የማይንበረከኩ ልበ ሙሉ ናቸው። የቴዲ ስም በአንድ ካሴት ሰማይ ጠቀስ ስለሆነባቸው ለምን እንበለጣለን ከሚል ለይጣናዊ ሃሳብ የመነጨ የጥቂቶች የተንኮል ጥንስስ ነበር። ነገር ግን ቴዲ ጡት ላይ እንዳልፈረመ ሲያውቁ የወሬ ሱሰኞች አርፈው ተቀመጡ።

## 2. ቴዲ የሚዘፍናቸውም ሆነ ለስራ ባልደረቦቹ የሚያበረክታቸው ግጥሞች የአባቱ ናቸው

ድምጻዊ ቴዲ አፍሮን በዜማም ሆነ በግጥም ተሰጥኦውን መጠርጠር ትልቅ ስህተት ነው። አንድን ስራ ከሰራው ባለቤት ውጪ እማኝ ሆኖ መቅረብ ለምን አስፈለገ? የቴዲ አፍሮ የግጥም እና የዜማ ተፈጥሯዊ ልገሳ እንደ ምንጭ ውሃ ቢቀዳ የማያልቅ በላይ በላዩ የሚተካ ቋሚ ነው። እግዚአብሔር ሽልሞ የሰጠውን ማን ሊነጥቀው ይችላል? ቴዲ አፍሮ ግጥም የመፃፍ ችሎታ ባይኖረው ኖሮ እንደሌሎች ዘፋኞች ከሌላ የግጥም ፀሀፊ በወሰደ ነበር። ደግሞም ለሌሎች የስራ ባልደረባዎቹ ባላበረከተ ነበር። በጥበብ ህይወት ውስጥ ማሸነፍ ወይም መሸነፍ ያለና የሚኖር ነው። ሽንፈትን ተቀብሎ ለቀጣይ የስራ ስኬት ጥሩ ነገርን ሰርቶ ለመገኘት መጣር ታላቅነት ነው። ‹‹የተንኮል ጉድጓድ አትቆፍር። ብትቆፍርም አታርቅ። ማን





እንደሚገባበት አይታወቅምና›› የሚለውን አባባል በመጋራት ሱፍሏ የፈጠራ ችሎታ እንኳንስ አድማጩ ሳር ቅጠሉ ምስክር ነው። የበለጠንን ሰው አውቀን መበለጣችንን በጸጋ መቀበል ትልቅነት ነው። ቴዲ አፍሮ እየዘፈነ ያለው የአባቱን ግጥም ከሆነ ታዋቂው ጋዜጠኛ ካሳሁን ግርማሞ ወደ ዘላለማዊ አባቱ ከሄደ በኂላ ቴዲ እየሰራ ያለው የማንን የፈጠራ ችሎታ ነው? ይህ ሁሉ በአንድ ወቅት ስለ ግጥም ችሎታው ተጠይቆ በርካታ ግጥሞች እንዳሉት ስለተናገረ በምን ስሙን እናጥፋው ከሚል መጥፎ ሀሳብ የመነጨ በጥቂቶች የተቀነባበረ የሀሜት ጥንስስ ነው።

ስራ ክቡር ነው። ታላቅ ሥራ በሚሰራ ሰው ላይ የነገር ሚዶ ሰክቶ በሀሜት ማበጠር የት ድረስ ያስኬዳል? በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ለጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ የተቀነቀነው የድል ዘፈን በማን የግጥም ችሎታ ተፃፈ? ቴዲ የአባቱን ግጥም ቢያቀነቅን ኖሮ ጊዜና ወቅት ጠብቀው ለህዝብ ጆሮ የሚበቁትን ዜማዎችን ለመስማት ባልታደልን ነበር። የወሬ ሱሰኞችና የስራ ጠላቶች ነገርን እንደ ድርና ማግ በማስማማት በየአካባቢው የሀሜትን ወሬ በመዝራት ለማብቀል የሚሞክሩ አልጠፉም። እውነት አትሞትም። ክውሸት ጋርም አትተባበርም። ቴዲ አፍሮ በተፈጥሮ የተለገሰው የዜማና የግጥም ችሎታ ቢቀዳ የማያልቅ ቢንጠባጠብ የማይነጥፍ ስለመሆኑ በየጊዜው የምንሰማቸው ስራዎቹ ይመሰክሩለታል። የራሱን ማንነት ጠንቅቆ የሚያውቀው ወጣቱ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን ከማውራት ይልቅ በሚሰራቸው የማይሰለቹ ስራዎቹ የሀሜተኞችን አፍ አሲዟል።

## 3. ዜማ ከውጪ አገር ገለበጠ

ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም። የድምፃዊ ቴዲ አፍሮ የገዘፈ ስም በማንነታቸው ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ያሳደረባቸው አንዳንድ አርቲስቶች እንዳሉ ይታወቃል። ዋናውን ፈረስ መሆን ባይችሉም ተጎታቹ ጋሪ መሆን የተሳናቸው፣ ጠንክሮ ከመስራት ወሬንና ስምን

ማጥፋትን የመረጡ ናቸው። ብዙኀኑ ህዝብ ይህንን ሲሰማ ብሶቱን በትዝብትና በመቃወም ነበር የገለፀው። ቴዲ እኮ በሙያው ሊያቀነቅን ምክንያታዊ ነው። ምዕራባዊ አገራትን ለመኖሪያ ያልመረጠ፣ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ፣ የዘመኑ የኩራት መገለጫ ነው።

ለመሆኑ ሙዚቃ የአለም ቋንቋ መሆኑን የዘነጉ አርቲስቶች አሉ እንዴ? የቴዲ ዜማ አንዳንዶቹ ከውጪ አገራት ጋር ይቀራረባሉ በማለት የምላስን ቢላዋ በመሳል ለነገር መሮጥ ተገቢ ነው? ይህ አካሄዳቸው በግልፅ የሚያሳየው ለአርቲስቱ ወይም ለሙዚቃ ያላቸው ጠባብነት ነው። ደግሜ ደጋግሜ መናገርም ሆነ መፃፍ የምፈልገው ተወዳጁ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ የግጥምም ሆነ የዜማ ችግር እንደሌለበት ነው። ምክንያቱም ቴዲ ሲያስፈልገው አንድ ዜማና ግጥም ለመስራት ከ10-15 ደቂቃ ብቻ ቢፈጅበት ነው። ነገሩን በደንብ ላብስለው ካለ ደግሞ ግፋ ቢል 30 ደቂቃ ሊወስድበት ይችላል። ተወዳጁ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ከራሱም አልፎ የፈጠራ ስራውን ለጠየቁት አርቲስቶች ከወርቅ የበለጠ ሚዛን በሚደፋው የፈጠራ ክየና ክህሎቱ አበርክቶላቸው በአንድ ጊዜ አንቱ ለመባል የበቁ አርቲስቶች አሉ።

የሀገራችን የሙዚቃ እድገት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ነው የሚገኘው። ለሙዚቃው እድገት ደግሞ ቴዲ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። ማንኛውም የዜማ ፈጣሪ ነኝ የሚል ዜማ ቀማሪ ሁሉ አንዳንድ ጊዜ እንደመነሻነት ከውጪ ሀገራት ዘፈኖች ዜማ ሊወስድ ይችላል። ነገር ግን የፊልም ደራሲ ነን የሚሉ ግለሰቦች ሙሉ በሙሉ የሰው ሀገርና የሰው እውቀት እስክሪፕት ገልብጠው ሲያበቁ የዋናው የፈጠራ ባለቤት መብት ሳይገልፁ ቋንቋውንና አለባበሱን ለውጠው ፊልም ሰራን ቢሉ ማን ይሰማቸዋል? እውነተኛውን ሰው ውሸታም ብለው መሳደብስ ይችላሉን? ስህተት የሌለበትን ሰው በነገር ከመውጋት መጀመሪያ የራሳችንን ገመና እናስወግድ።

በወቅቱ በቴዲ አፍሮ ላይ በተወራው ዜማ ግልበጣ ተራ ስብከት ቴዲ ምን አለ? ‹‹አነጣጥሮ ተኳሽ በቅድሚያ ኢላማውን





ለይቶ መክበብ አለበት። ከመተኮሱም በፊት ስለ ፈጠራ ባለቤትነት መብት መረጃ መሰብሰብ፣ ጥናት ማካሄድ፣ ባለሙያዎችን ማነጋገር ያስፈልጋል። ኢላማን በትክክል ለመምታት መጀመሪያ ኢላማህንም በቾክ ታከባለህ። ከዚያ በሩቅ ሆነህ ታነጣጥራለህ። ይህ የፈጠራ ስራ በእርግጠኝነት የማን ነው? ከየትስ የመጣ ነው? እንዴትስ ተፈጠረ? ብለህ ታጣራለህ። ለመረጃህም እርግጠኛ ድጋፍ ትሰበስባለህ። ያኔ ኢላማህ ግቡን ይመታል። የዚያን ጊዜ ሃይለኛ ተኳሽ ተብለህ ትደነቃለህ።››

ተወዳጁ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ከአስር ዓመታት ወዲህ የተፈጠረና ከምናያቸው አርቲስቶች በሚሰራው ድንቅ የፈጠራ ስራው ታላቅነትን የተቸረው ምትክ የለሽ አርቲስት ነው።

አሁን ካለበት የገዘፈ ክብር ላይ የደረሰው ጠንክሮ በመስራቱና ስራውን አሳልፎ ለፈጣሪ በመስጠቱ ነው። እግዚአብሔርም ባርኮለታል። በወጣትነት እድሜው ከሌሎች የስራ ባልደረቦቹ ልቆ በመገኘቱ በሚሰራው አመርቂ ስራ የብዙኀኑን የልብ ትርታ ለማዳመጥ ችሏል። በዚህም ለዘመናት በማንም በቀላሉ ሳይተካ በሙዚቃ ህይወት ውስጥ ስሙ እንደነገሰ ከትውልድ እስከ ትውልድ እየተወራረሰ የሚኖር ምርጥ አርቲስት ስለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ቴዲ በዜማ መጠርጠሩ ምንም አይደል። ግን ለመጠርጠር የሚያስብ ማንም ባለሙያ ነኝ ባይ ሰው ጥርጣሬው ከጤነኛ አዕምሮ የመነጨ ወይም በታላቅ ምቀኝነት ግፊት የተነሳሳ አለመሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

ከዙፋኑ ስር የሚያደርስና ወንበሩን ለመረከብ የሚያስችል ይህ ነው የሚባል ውጤት ሳይኖር ዙፋኑን መመኘት የቀን ቅዠት ነው። ስልጣንና ታዋቂነት ለሚፈልጋት ሳይሆን ለሚሸሻት ትቀርባለች።

ቴዲ አፍሮን ዜማ ከውጭ አገር ገለበጠ ተብሎ መሰረት የሌለው ተራ ወሬና አሉባልታ በተወራበት ጊዜ ጥቂት አርቲስቶች፣ ቴዲ ካለበት የክብር ደረጃ የወረደ መስሏቸው በሀሰተኛ ወሬ ለክረው

የመጠጥ ዘር ሁሉ እያወረዱ ሲጠጡና ምግብ በገፍ አቅርበው ቁንጣን እስኪይዛቸው ድረስ እየተመገቡ ያሙትም አልጠፉም ነበር።

የትንኮል ጥንስሳቸው ግን በቀላሉ ተደፋ። ያላግባብ ለማግኘት የተመኙት የማዕረግ ወንበር ወዲያው ተገለበጠ። ቴዲ አበቃለት ብለው የተደሰቱ ግለሰቦችና ጥቂት አርቲስቶች መልሰው ተሸማቀቁ። አርቲስቱ ክበፊቱ የበለጠ ገነነ። ስራዎቹም በህዝብ ዘንድ ያላቸው ክብር ጨመረ። በዘር፣ በፆታ፣ በሃይማኖት ሳይቀር የወጣቱ ድምፃዊ የፈጠራ ስራዎች ተፈላጊነታቸው አደገ። ቴዲ ግን ይህ ሁሉ ሲሆን የማንንም ውድቀት አልተመኘም።

የቴዲ አፍሮ የፈጠራ ችሎታ ጠንቅቀው የሚያውቁ አንዳንድ ግለሰቦች ጥያቄ ውስጥ መግባታቸው ብቻ ሳይሆን አንድ ዜማና ግጥም የመስራት ችሎታ የሌላቸው በሌላው ወገን ትከሻ ላይ ተንጠልጥለው እየኖሩ በፈጠራ ችሎታው ተመስክሮና አስመስክሮ ያለን ውድ አርቲስት መጠጥ እየጠጡ የህሜት ምግብ ማድረጋቸው የማሰብ ችሎታቸው የት ድረስ እንደሆነ በግልጽ ማየት ይቻላል።

የቴዲ አፍሮ የገዘፈ ስም በሀሜተኞች የማይሰረዝ፣ በውሃ የማይሸረሸር፣ እንደበረዶ የማይቀልጥ፣ ቋሚ ሆኖ ለዘላለም ይኖራል። ቴዲ በአንድ የሙዚቃ ኮንሰርት የሚያገኘውን የገንዘብ መጠን ካሴት ሸጠው ማግኘት እንኳን ስለተሳናቸው በጥቂቶች ወይም በአንዳንድ አርቲስት እና ግለሰቦች መንጋጋ ቢገባም ሊታኘክ የማይችል ጠንካራ ነው። የበሰጠንን በማበረታታት የእርሱን ፈለግ ተከትለን ለጥሩ ነገር መሮጥ መልካም ነው። የቴዲ አፍሮን ማንነት ለማወቅ እሩቅ መንገዝ ወይም በአካል አግኝተነው ማየት ብዙም አያስፈልገንም። ምክንያቱም ጊዜ እና ወቅት ጠብቀው የሚወጡ ስራዎቹ የአርቲስቱን ማንነት አበጥረው ያሳዩናልና።

ቴዲ አንድም ቀን ‹እኔ የበላይ ነኝ› ብሎ እራሱን የማይክብ ሁል ጊዜ እራሱን ዝቅ የሚያደርግና በፈጣሪው የሚተማመን ውድ አርቲስት ነው። አርቲስቶቻችን ላንድ ክሮዘር፣ ቢ. ኤም ደብሊው፣





ወዘተ ዘመናዊ መኪኖች ለመያዝ እና ለማሽከርከር የበቁት ቴዲ በቀደደው የገበያ በር ነው። ሌት ተቀን አምጠ የፈጠራቸውን ዜማዎች ተገልብጠው የተሰሩ ናቸው ማለት እውነታው የት ድረስ ነው?

አናውቅም እንዴ? ታሪክስ አይነግረንም? ከዚህ ቀደም የነበሩ ዘፋኞች ስንት ደክመው የለፉበትን የዘፈን ካሴት በብር 100 እና በብር 200 ሲሸጡ እንደነበር? ለመሆኑ ከተራ ብር ዘሎ ለማያውቀውን የካሴት ሽያጭ ማነው ወደ ሚሊዮን ብር እንዲያሻቅብ ያደረገው? ቴዲ አፍሮ አሁን ላሉትና ወደፊት ለሚፈጠሩ ድምፃዊያን ዋና መከበሪያቸው ነው። አለማወቅ ሃጢያት አይደለም።

ለመጠየቅ የምንፈራና የምናፍር ከሆነ አንብበን እንረዳ። ከዚህ ቀደም የነበሩ ዘፋኞች እንኳንስ መኪና አማርጠው ሊይዙ ቀርቶ ለእለት ጉርስና አልባሳትም ስንት ውጣ ውረድ ነበረባቸው። ቴዲ አፍሮ የዚህ ህዝብ ቁንጮ ነው።

ፈጣን በሆነ የፈጠራ ችሎታው እና በአስተዋይነቱ እንዲሁም ትሁት በሆነው ባህሪው ትልቅ ስም የተሰጠው የሁሉም ሰው ምርጫ ነው። ከፈጣሪ የተሰጠውን ፀጋ በወሬ ወይም በምቀኝነት አያጣውም። በአንድ ሴኮንድ ውስጥ አንድ ሺህ ጥፋትና ስህተት መስራታችንን ልባችን ሲያውቀው እራሳችንን ፍፁም እና ንፁህ ለማድረግ መቃበዝ ታላቅ ስህተት ነው።

ወደድንም ጠላንም ቴዲ በዚህ ዘመን የተፈጠረ ልዩ መልዕክተኛ ነው። የፈጠራ ስራውም ለዘመናት ሊደበዝዝ የማይችል የሰላም ሻማ ነው። እንኳንስ በአንድና በሁለት ዜማ ሊጠረጠር ቀርቶ በተፈጥሮ የተሰገሰውን የጥበብ ችሎታ ገና አሟጦ አልተጠቀመበትም። በቴዲ ሞራል ላይ እረማመዳለሁ ማለት ከዚህ ህዝብና ከፈጣሪም መጣላት ነውና የተንኮልን ፍትፍት ለነፍሳችን ስንቅ ባናደርገው መልካም ነው።

የአስተዋይነቱም መጠን ጥልቅ ነው። የፊት የፊቱን

የሚመስከት ግብዝም አይደለም። ቴዲን ከነነብሱ ይዘው ባህር ውስጥ ቢወረውሩት ሳይሰምጥና ሳይሞት በአፉ አሳ ይዞ የሚወጣ ብልሀተኛ ነው። ስወደፊቱ ስለሚሆነው ነገር ሳይሆን ዛሬ እየሆነ ስላለው ነገር እጨነቃለሁ። አርቲስቱ ለማንም አይንበረከክም። ተንበርክኮም አያውቅም። ዘፈኖቹም ቢሆኑ የይድረስ ይድረስ የሚሰሩ ሳይሆኑ ታላቅ የፈጠራ ጥበቡን ተጠቅሞ አሳምሮና ከሽኖ የሚሰራቸው ናቸው። ዝናን በአግባቡ መያዝ የቻለ አካሄዱን የሚያውቅ፣ የዛሬን ብቻ ሳይሆን የነገንም የሚያልም፣ ወገኑን የሚወድ እውነተኛ ነው። የቴዲ አፍሮ የገዘፈ ስም እና መልካም ዝና ጠዋት ታይቶ የሚጠፋ ጤዛ አይደለም። ለአገሩና ለአድናቂው ህዝብ ሁለተኛው የኩራት መገለጫ ሰንደቅ አላማ ነው።

## እውነት አትሞትም!

አዋቂ የሚናቅበት
ወረኛ የሚከበርበት
ደጉን ችላ የሚባልበት
ክፉውን ሞገስ የሚያገኝበት
ሆነና ጊዜው
ጊዜ የሚለውጣቸው
ጥቅም የሚደልላቸው
እነዚያ ጎሊያድ ነን ባዮች
የእውነት ጦር የጥበብ ጠላቶች
እንደገና ሀ ብለው ተነሱበት
የምቀኝነት ጦር ሰብቀው ዘመቱበት።





ከተሰቀለበት ሰገነት ከወጣበት ማማ ሊያወርዱት
የሐሰት ስንቅ ሰንቀው ሰሙን አብጠለጠሉት
እናም ሐሰትና እውነት ተጣልተው ፀብ ከሮ
ለጊዜው ውሸት ያሸነፈች መሰለች - ተመታም ከበሮ
ወድቃ የማትቀረው እውነት ግን ተነስታ
ሐቁን መሰከረች ዕልልታ ሆነ ፌስታ
አዎን፣ መሰከረች ጥበብ በእውነት ፊት ቆማ
ቴዲ ታላቅ ሰው ብላ ዓለም እየሰማ።
ይሄኔ እነዚያ ጎሊያድ ነን ባዮች
የእውነት ጠር የጥበብ ጠላቶች
እንደ ረመጥ እሳት ውስጥ ውስጡን እየጋዩ
እውነት አብባ ሐሰት ስትጠወልግ አዩ።
እንግዲህ ይግረማቸው ይደነቁ
ሀሰትን ወደው ለሰነቁ
ቴዲማ ጥላቻን በፍቅር ደርምሶ
ክፋትን በደግነት ጥሶ
ቂምን በምህረት ጥሶ
ወጣ እንደገና የጥበብን ካባ ለብሶ

አዎን፣ የሰይጣን ከፋት ገልብጦ
ምቀኝነትን በስራ ድል ነስቶ
በጥበብ አሽብርቆ በቅኔ ደምቆ
በሞገስ ላይ ሞገስ ደራርቦ
አልቀረም መውጣቱ ከማንም ልቆ
ኸረ ለመሆኑ ከዚያ ዙፋን ከዚያ መቀመጫው
እሱ ከወረደ ሙዚቃን ማን ሲመራው?
እንግዲያውስ ሰሚ ጆሮ ካላቸው ቅን ልቦና
እውነቱን መስማት ከፈቀዱ በንፁህ ህሊና
እልፍ ሆነው የማይተኩት
ዝናና ሀብት የማይለውጡት
ገድለኛ ነው ቴዲ ተአምረኛ
ሥራው ሁሉ የሆነ ቀጥተኛ
ገና ይፈጥራል ተአምር
ጎልቶ የሚታይ በፍቅር!





# 4. በመኪና ሰው ገጭቶ ገደለ

## *ምድር የፈተና መድረክ ስትሆን ሰዎች ደግሞ ተዋንያን ናቸው*

የሰው ልጅ በዚች አለም ሲኖር ከቀላል ፈተናዎች እስከ አስቸጋሪና ከባድ የህይወት ፈተናዎች ያጋጥሙታል። ማንኛውንም ፈተና በብልሃትና በትእግስት አሸንፎ ለስኬት መብቃት የታላቅነት ባህሪይ ነው። ዓለም ከተፈጠረች ጀምሮ ታላላቅ የፈጠራ ስራ የሰሩም ሆነ ታላላቅ ጀግኖች ተብለው እንደምሳሌነት የሚጠቀሱ ሰዎች በሙሉ የኋላ ህይወታቸው ሲመረመር በመከራ ውስጥ ከማለፋቸው በተጨማሪ የእስር ቤትን ህይወት ቀምሰዋል።

ብልህ ሰው ከመከራ ይማራል እንጂ ለፈተና ተሸንፎ ወድቆ አይገኝም። ደግሞም የአንድ ሰው ጥንካሬ የሚለካው ለምድር ፈተናዎች ባለመሸነፉ ነው። የሰው ልጅ ከባድ ፈተናዬ ነው ብሎ የሚያስበው እስር ቤትን ነው። ስለ እስር ቤት ስናስብ ለሀያ ሰባት አመታት በግፍ የታሰሩትን የደቡብ አፍሪካን የነጻነት ታጋይ ማንዴላን እናስታውሳለን። ማንዴላ ለህልማቸው መሳካት፣ ለልባቸው እውነት ለበርካታ አመታት በእስር ቢያሳልፉም ነፍሳቸው የሰነቀችው ታላቅ ህልምና እውነት መታሰራቸውን አላገዳትም። የሰው ልጅ ከፍጥረታት ሁሉ መከራን የሚችልበት ጠንካራ መንፈስ አለውና።

ኢየሱስ ክርስቶስ በዚች ምድር ላይ ሆኖ ለሰው ልጆች የአምላክን የእውነት ቃል የሆነውን ቅዱስ ቃል በሚሰብክበት ጊዜ በርካታ ምድራዊ ፈተናዎች ገጥመውታል። ለእውነት ሲል በአይሁዶች ታስሮአል፣ ተርቧል፣ ተጠምቷል፣ ተገርፏል... ምድር ለፈተና ቅርብ የሆነች የፍዳ መኖሪያ ነችና። በመሆኑም ይህቺ ምድር እንኳን የሰው ልጆች ቀርቶ ለፈጣሪዋም ያልተመቸች አስቸጋሪ ነች።

አገራችን ካፈራቻቸው በቁጥር አንድ የሚጠቀስ ታላቅ የጥበብ ቀማሪ ወጣቱ ድምጻዊ ቴዲ አፍሮ፣ በወርሀ ጥቅምት ተፈፀመ በተባለ

ወንጀል ምክንያት የዚህ አይነቱ ከባድ ፈተና ከፊቱ ተጋርጦበታል፡፡ ይህ የአገራችን ብርቅዬ ድምፃዊ በተሽከርካሪ ሰው መግደል ወንጀል ተከሶ የእስር ቤት ደጅ ረግጧል፡፡ ለመሆኑ እስር ቤት የዓለምን ታላላቅ ሰዎች ለምን ይሆን በሯን ወለል አድርጋ እየከፈተች የምታገራቸው? ደግነቱ እነዚያ ጀግኖች በመታሰራቸው ሐዘን ሳይገባቸውና ተስፋ ሳይቆርጡ መልሰው ለስኬት የሚበቁ ብርቱዎች ናቸው፡፡ እግዚአብሄር ይመስገን!

ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ "በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው" የሚለው፡፡ የአንድ ሰው እሱነቱ የሚለካው ፈተና በሚገጥመው ሰዓት በሚያሳየው አይበገሬነትና የመንፈስ ጥንካሬ ነው፡፡

ቀኑ ጥቅምት 23 ቀን 1999 ዓ.ም ነው፡፡ ዝነኛው ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ከቦሌ የአየር ማረፊያ ተርሚናል ሻንጣውን አንግቦ ብቅ ሲል ከአለልቹ ረጅም ጉዞ የተነሳ የድካም ስሜት ይታይበት ነበር፡፡ እንደተለመደው ቀለል ያለ ቲሸርት እና ጅንስ ሱሪ ለብሷል፡፡ ምንም እንኳን የድካም ስሜት ፊቱ ላይ ቢነበብም ያ አማላይ ፈገግታው ከብሩህ ፊቱ ላይ አልጠፋም፡፡

ቴዲ አፍሮ በተለያዩ የውጪ አገራት ለሚገኙ የሙዚቃ አድናቂዎቹ የሚጠበቅበትን ነገር ፈፅሞ ካጠናቀቀና የልቡን ካደረሰ በኋላ እዛው መቆየትን አይፈልግም፡፡ "መንፈሴ የሚያርፈው ልቤ የሚረጋጋው እና ነፍሴን ደስ የሚላት በአገሬ ምድር ላይ ነው፤" የሚለው ቴዲ ከሚወዳት አገሩ ከኢትዮጵያ ተለይቶ እረጅም ጊዜ መቆየትን አይመርጥም፡፡

በእለቱ ከነበረው የስራ ጫና አንፃር ይሁን ካደረገው አድካሚ ረጅም የአየር በረራ የድካም ስሜት ቢጫጫነውም ሀገሩ እንደገባ ቀጥታ ለእረፍት ወደ ቤቱ አላመራም፡፡ በጣም ከሚወዳቸው የቅርብ ጓደኞቹ ጋር በመሆን ልብስ ሲገዛ፣ ፀጉሩን ሲሰራ ብሎም በተለያዩ ናይት ክለቦች በመዟዟር ወጣት ድምፃዊያንን የሀሳብና የሞራል ድጋፍ በመስጠት ሲያበረታታ ነበር ያመሸው፡፡





ቴዲ አፍሮ ‹‹ከሌሊቱ 7:10 ሰዓት ሲሆን ቢ ኤም ደብሊው ዘመናዊ አውቶሞቢል እያሽከረከረ ሲጓዝ፤ በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 14 ልዩ ቦታው ፊት በር በተባለው አካባቢ ከግራ ወደቀኝ በማቋረጥ ላይ የነበረውን ሟች ቅድሚያ በመከልከል ገድሏል›› የሚል ክስ ቀረበበት፡፡

ቴዲ እንደተናገረው ከሆነ ግን በወቅቱ ከውጪ አገር ወደ አገሩ በተመለሰበት ቀን ሌሊት ላይ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲ ኤም ሲ አካባቢ ሲደርስ በነበረበት የጉዞ ድካምና የእንቅልፍ ሰዓት መዛባት የተነሳ የሚያሽከረክራት መኪናው ከግዑዝ አካል ጋር ተጋጭታ በእሱና ንብረቱ በሆነችው ዘመናዊ መኪናው ላይ የተወሰነ ጉዳት ደርሶባቸው ነበር፡፡

ቴዲ በመኪናው ሰው ገደለ የሚለው ወሬ በተለያዩ የሀገሪቷ መዲናዎች ውስጥ መናፈስ ሲጀምር አድናቂዎቹ "ቴዲ ሰው አይገልም፤ እንደውም ቴዲ መኪና ሲያሽከረክር የትራፊክን ህግና መመሪያ በመከተል ለእግረኞች ቅድሚያ ይሰጣል፣ በስራውም ሆነ በተግባሩ በግንባር ቀደምትነት አርአያ የሆነ መልካም ሰው ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ መኪና ሲያሽከረክር ሞባይል ያጠፋል፡፡ ሀሳቡን ይሰበስባል፡፡ በተገቢ ፍጥነት ረጋ ብሎ የሚያሽከረክር ብቁ ባለሙያ ነው" ሲሉ ተደምጧል፡፡ አክለውም "ቴዲ አፍሮ ሰው ቢገጭ ለዜጎቹ ካለው ፍቅርና ከምንም በላይ እግዚአብሔርን ስለሚፈራ ሰው ገጨሁ ብሎ ይፋ የሚናገር ሃቀኛ አርቲስት ነው፡፡ ምክንያቱም በሚያከብረው ህዝብ ላይ እንዲህ አይነት የጭካኔ ስራ አይሰራም" ሲሉ የአርቲስቱ አድናቂዎች ደግመው ደጋግመው እሱነቱን በልበ ሙሉነት መስክረውለታል፡፡

አድናቂዎቹ ይህ ለማለት ያበቃቸው ሁነኛ ምክንያት ምንድነው? ምክንያቱማ ተወዳጁና ዝነኛው ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ለወገኑ ያለው ፍቅር ወሰንና ገደብ የሌለው ሀያል እንደሆነ አብጠርጥረው ስለሚያውቁ ነው፡፡ ቴዲ ራሱ ‹‹ለእኔ እዚህ ደረጃ መድረስ መሰረቴ የአገሬ ህዝብ ነው›› ሲል ዘወትር ሲናገር

ተስምቷል፡፡ በተለይም ለጎዳና ተዳዳሪ ልጆች ልዩ ፍቅር አለው፡፡

ቴዲ አፍሮ ማንም ሰው ተቸግሮ ማየትን አይፈልግም፡፡ ልቡ የዋህ ነው፡፡ ለወገኑ ካለው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ የተቸገረን ሰው አይቶ እንደ ማንም ሰው ከንፈሩን በመምጠጥ ማለፍን አይፈልግም፡፡ ያለውን በመስጠትና በማካፈል ወገናዊ ፍቅሩን ይገልፃል፡፡ ከሃብታሞች ጋር ሳይሆን ከዝቅተኛው ማህበረሰብ ጋር መሆንን ይመርጣል፡፡ ያለውን ተካፍሎ በመብላት ይደሰታል፡፡ "የሰው ልጅ ክቡር ስለሆነ ያለው ለሌለው በመስጠት ወገናዊ ፍቅሩን መግለፅ አለበት" የሚለው ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ወደፊት ለጎዳና ልጆች የስራ ዕድል የሚፈጥሩ ተቋማት የመክፈት ወይም ሌሎች ብዙ የበጎ አድራጎት ሥራዎች የመስራት ሀሳብ እንዳለው አበክሮ ይናገር ነበር፡፡ ለዚህም ነው ከአርቲስትነቱ ባሻገር ብዙ የደግነት መንገዶችን አጥብቆ ለመያዝ የበቃው፡፡ የቴዲን ገራገርነት ከእሱ ሳይሆን ውለታ ከዋለላቸው ወገኖች ለምቶ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

የሆኖ ሆኖ ወንጀሉ ተፈጸመ ከተባለ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ቆይታ በኂላ ክሱ ተንቀሳቅሷል ተብሎ ተወራና ወረቀትና ሞኝ የያዘውን አይለቅም እንዲሉ ተወዳጁ ድምጻዊው ቴዲ አፍሮ እሮብ ሚያዚያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ቃሊቲ ወዳለው እስር ቤት ተወስዶ በዚያ ሆኖ ጉዳዩን እንዲከታተል ተደረገ፡፡ ቴዲ ታሰረ የሚለው ዜና በሚዲያ ሲነገር አድናቂዎቹ በከፍተኛ ሀዘን ተመቱ፡፡ እንባቸውን እየረጩ፣ "ቴዲ ይፈታ" በማለት በጩኸት ማስተጋባት ጀመሩ፡፡ ‹‹የድምፃዊው ቴዲ አፍሮ ጉዳይ የእኛም ጉዳይ ነው›› በማለት ከየአቅጣጫው ምሬታቸውን ገለፁ፡፡ ይህ አሳዛኝ ክስተት በዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ሳይቀር ከፍተኛ ሽፋን ተሰጥቶት በአሜሪካ የሚገኙ የስራ ባልደረቦቹ፣ አድናቂዎቹና የሀገሩ ልጆች "ቴዲ ይፈታ" በሚል መሪ ቃል አሜሪካ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኢምባሲ በር ላይ የተቃውሞ ድምፃቸውን አሰሙ፡፡

የድምጻዊው ቴዲ አፍሮ ጠያቂ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው ቢባል ይሻላል፡፡ በየቀኑ እሱን ለመጠየቅ ለማፅናናትና አይዞህ ከጎንህ





ነን ብለው ያላቸውን ፍቅር ለመግለፅ ከመዲናችን አዲስ አበባ ውጪ የብዙ ክፍለ አገራት ህዝብ ቴዲ ወዳለበት እስር ቤት ይጎርፍ ጀመር፡፡ ቴዲም ቢሆን "እውነት አትሞትም! ከውሸተኞች ጋር ህብረት የላትም! ተስፋዬ እግዚአብሔር ነው፡፡ አይዟችሁ!" በማለት አድናቂዎቹን አጽናንቷል፡፡

በቀጠሮው ቀን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅጥር ግቢ በአድናቂዎቹ ጢም ብሎ መፈናፈኛ ታጣ፡፡ አድናቂዎቹ የቴዲ ምስል ያለበትን እና ‹‹ጊዜ ለኩሉ›› የሚል ፅሁፍ የሰፈረበትን በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያሸበረቀውን ቲ ሸርት ለብሰው ታዩ፡፡

ሁሉም አድናቂዎቹ ‹‹ቴዲ ንጹህ ስለሆነ ይፈታ፤ ቴዲ ሰው ገድሎ ያመለጠ ወንጀለኛ አይደለም፤ የሰውን ነፍስ አላጠፋም፤›› እያሉ የውስጣቸውን ስሜት በእንባ፣ በፉጨትና በጩኸት ሲገልፁ ተስተውለዋል፡፡ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ተሳፍሮ ከመጣበት መኪና ወርዶ ወደ ችሎቱ ሲያመራ እንደማዕበል ከአራቱም አቅጣጫዎች የጎረፈው ህዝብ በለቅሶና በጩኸት ተቃውሞውን ገልጿል፡፡ ቴዲ ከህዝቡ በግምት ከ5 እስከ 10 ሜትር ቢርቅም እጁን በማውለብለብና አንገቱን ዝቅ በማድረግ በአክብሮት አጸፋዊ ሰላምታ ሲያቀርብ ተስተውሏል፡፡

ይህን መሰል ክፉ ነገር ደርሶበት የማያውቀው ቴዲ አፍሮ እስር ቤትን ለመልመድ አስቸጋሪ ቢሆንበትም ባለው የውስጥ ጥንካሬ ለጊዜው እንደጊዜው ሆኗል፡፡ ቴዲን እስር ቤት እየሄደ የሚጠይቀው ሰው ቁጥር እጅግ በጣም በርካታ ነው፡፡ ከሃገር ቤት አልፎ ከባህር ማዶ እየመጡ "አይዞህ ሁሉም ነገር ለበጎ ነው፡፡ ቸር ወሬ ያሰማን" የሚሉት የውጪ ዜጎች ወይም ፈረንጆች እንኳን ብዙ ናቸው፡፡ የቴዲ አፍሮ አድናቂዎች ምንም እንኳን ልባቸው በሃዘን ቢመታም ቴዲ በተጠረጠረበት ወንጀል ነፃ እንደሚወጣ እምነታቸው የፀና ነበር፡፡ በተለይ ከምንም በላይ የሆነው የንጹሀን አምላክ ኃያሉ እግዚአብሔር፣ የቴዲንና የአድናቂዎቹን ኃይለኛ ተስፋ ስለሆነ፤ ቴዲን ካለበት አስቸጋሪና ውጣ ውረድ ከበዛበት ካልታሰበ የችግር አዘቅት ነፃ እንደሚያወጣው ጥርጥር አልነበረውም፡፡ ቴዲም ቢሆን

በተደጋጋሚ ‹‹የእኔን ነፃነት የፈጠረኝ ስለሚያውቀው ተስፋዬን እውን ያደርግልኛል›› ሲል ተደምጧል፡፡

## ከሳሽ ዐቃቢ ሕግ በቴዲ አፍሮ ላይ ያቀረበው የክስ ዝርዝር

- ከሳሽ፡- የፌዴራል ከፍተኛ ዐ/ህግ
- ተከሳሽ፡- ቴዎድሮስ ካሳሁን ግርማሞ
- ዕድሜ፡- 30
- ስራ፡- ሙዚቀኛ
- አድራሻ፡- አ/አ አዲስ ከተማ ክ/ከ ቀበሌ 27 የቤት ቁ 238

## 1ኛ ክስ

## ወንጀል

በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 543/3 እና የትራንስፖርት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 279/1956 5/4 ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ

## የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሽ ተሽርካሪ ለማሽከርከር የሚያስችል ሊኖረው እንደሚገባ የሚያዘውን ግልፅ የሆነ ደንብ በመተላለፍ መንጃ ፍቃድ ሳይኖረው ጥቅምት 23 ቀን 1994 ዓ.ም ከሌሊቱ 7፡00 ሠዓት ከ10 ደቂቃ ሲሆን የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2/59869 አ.አ የሆነ ቢ.ኤም. ደብሊው አውቶሞቢል እያሽከረከረ ሲጓዝ በአራዳ ክፍለ ከተማ ቦሌ 19 ልዩ ቦታው ፊት በር ከተባለ አካባቢ ሲደርስ መንገድን ከቀኝ ወደ





ግራ በማቋረጥ ላይ የነበረው ሟች ደጉ ይበልጣል የተባለውን ግለሰብ ቅድሚያ በመኪናከል ገጭቶ በመግደሉ በፈጸመው በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሷል፡፡

## 2ኛ ክስ

## ወንጀሉ

በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 575/2 ሀ የተመለከተውን በመተላለፍ

## የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሽ በላይ በአንደኛው ክስ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2/59869 አ/አ የሆነ ቢ.ኤም ደብሊው አውቶሞቢሉን እያሽከረከረ ሲጓዝ ሟች ደጉ ይበልጣል ይባል የነበረው ከገጨው በኋላ ተገጪው ህይወቱ ከባድ አደጋ ላይ መሆኑን እያወቀ እርዳታ ሳያደርግለት ጥሎት በመሸሹ በፈጸመው በአደጋ ላይ የሚገኝን ሠው ያለመርዳት ወንጀል ተከሷል፡፡

## ማስረጃ

1. ኮ/ል ---------------- አድራሻ ---------------- ክ/ከ/------------ ቀበሌ----------------የቤት ቁጥር--------------
2. ኮ/ል ---------------- አድራሻ ---------------- ክ/ከ/------------ ቀበሌ----------------የቤት ቁጥር--------------
3. ኮ/ል ---------------- አድራሻ ---------------- ክ/ከ/------------ ቀበሌ----------------የቤት ቁጥር--------------
4. ኮ/ል ---------------- አድራሻ ---------------- ክ/ከ/------------ ቀበሌ----------------የቤት ቁጥር-------------

### ሰ. የጽሁፍ ማስረጃ

1. ሟች ላይ የደረሰውን አደጋ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ አንድ ገጽ፡፡
2. ሟች የተገጨበት ቢ.ኤም ደብሊው የሠ.ቁ.2.59869 አ/አ አውቶሞቢልን የሚያሳይ ፎቶግራፍ አንድ ገጽ፡፡
3. ከዳግማዊ ምኒልክ የተሰጠ የአስክሬን ምርመራ ውጤት አንድ ገጽ፡፡
4. አደጋው የደረሰበትን ቦታ የሚያሳይ የትራፊክ የፕላን ሁለት ገጽ፡፡
5. የአውቶሞቢሉ የቴክኒክ ምርመራ ውጤት አንድ ገጽ፡፡

#### መግለጫ

ይህ ክስ በወ/ክስ በወ/መህ/ሥ/ሥ/ቁ 119 መሠረት ተሻሽሎ የቀረበ ክስ ነው፡፡

* * *

በቴዲ ጉዳይ ላይ ከሳሽ አቃቢ ህግ ጉዳዩን ያውቁልኛል ያላቸውን ምስክሮች ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ላይ የምስክርነት ቃላቸውን አሰማ፡፡ ክቡር ፍርድ ቤቱም ሆነ የድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ጠበቃ አቶ ሚሲዮን የተለያዩ መስቀለኛ ጥያቄዎችን አቀረቡ፡፡ ቴዲም ቢሆን የህግ የበላይነትን የሚቀበል ማንም ሰው ከህግ በታች መሆኑን የሚያምን መሆኑን ከገለጸ በኋላ ለክቡር ፍ/ቤቱ ሰው አለመግደሉን አበክሮ በአንደበቱና በጠበቃው አማካኝነት ገልጿል፡፡ ‹‹ልብ በሉ! እኔ ሰውን ያህል ታላቅ ፍጡር አልገደልኩም! የሰውንም ደም በከንቱ አላፈሰስኩም፡፡ ጨካኝም አይደለሁም! የሞተው ግለሰብ ተነስቶ መናገር ቢችል ማን ገጭቶ እንደገደለው ይናገር ነበር፡፡ ሁሉም ኃይል ከእግዚአብሔር በታች ነው፡፡ ሀያሉ እግዚአብሔር ብቻ ነው! እኔ ሰው አለመግደሌን የገጨው ሟችና እግዚአብሔር ምስክሬ ናቸው!›› ብሏል፡፡

ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ከታሰረ በኋላ በተለይ ወጣት ሴትና ወንዶች የአርቲስቱን ምስል የያዘ ቲ ሸርት መልበስ የዘወትር ተግባር አደረጉት፡፡ አርባ ብር ሲሸጥ የነበረው ቲ ሸርት በአንድ ጊዜ ሁለት መቶ ብር ለመሸጥም በቅቷል፡፡ እንኳንስ የመግዛት አቅም ያላቸው ግለሰቦች አቅም የሌላቸው የጎዳና ልጆችም ሳይቀሩ ለብሰውት ታይተዋል፡፡ ይሄ ደግሞ የሚያመለክተው ቴዲ ለዚህ ህዝብ መሰረታዊ ጥያቄ መሆኑ ነው፡፡

ቴዲ እስር ቤት እያለ ከተናፈሱ ወሬዎች መሀል ‹‹በአእምሮ ጭንቀት ታሞ በህክምና ላይ ነው›› የሚል ነበር፡፡ ቴዲ እጅግ በጣም ጠንካራ፣ ሞራሉ የማይላሽቅ፣ ለብዙዎች የሚገርም አርቲስት ነው፡፡ ይህ ወሬ ካለምንም መረጃ ሆነ ብሎ የተወራ ተራ ወሬ መሆኑን ለቴዲ ቅርበት ያላቸው ጓደኞቹና ቤተሰቦቹ በወቅቱ ለአድናቂዎቹ ገልጸውላቸዋል፡፡

አዎን፣ ዝነኛው ድምፃዊው ቴዲ አፍሮ ከታሰረበት ሚያዚያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ጊዜ ቀጠሮዎች በሙሉ እየተመላለሰ በተከሰሰበት ወንጀል ሲከራከር የተወሰኑ ቀናት አዝኖ ቢታይም አንድም ቀን ያ ወኔው፣ ያ ልበ ሙሉነቱ፣ ያ ፈገግታውና ሳቂታነቱ ከገጽታው አልተለየውም፡፡

ቴዲ ብዙ ጊዜ በራሱ አንደበት ለክቡር ፍ/ቤቱ አቤቱታ አላሰማም፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ለመናገር ከተገደደባቸው ቀናቶች ግን መስከረም 29 ቀን 2001 ዓ.ም ላይ ‹‹በወንጀል የተከሰስኩበት በሌለሁበት ነው፡፡ ሟች የሞተው በ22/2/1999 ዓ/ም እንደሆነ የህክምና ማስረጃው ይናገራል፡፡ እኔ ደግሞ ከካናዳ ሀገሬ የገባሁት በ23/2/1999 ዓ.ም እንደሆነ የፓስፖርቴ ቪዛ ያስረዳል፡፡ ስለሆነም ሰው አልገደልኩም፡፡ ስለዚህ ክቡር የሆነው ፍርድ ቤት ጉዳዩን

በጥልቀት ይመርምርልኝ›› ሲል ፍርድ ቤቱን ተማጽኗል፡፡

የዚህ የቀን ጉዳይ ስህተት የተፈጠረው በሆስፒታል ውስጥ በነበሩት የህክምና ባለሙያ ናቸው ሲል ፍርድ ቤቱ አብራርቶአል፡፡ የቴዲ አድናቂዎች በተከሰሰበት በመኪና ሰው መግደል ወንጀል በነፃ እንዲለናበት ሁሉም በየሐይማኖቱ ተቋማት ሳያሰልስ የጾምና የፀሎት ፕሮግራሞችን አድርገውለታል፡፡

ቴዲ አፍሮም ‹‹በጣም የማዝነው በእኔ መታሰር ሳይሆን በአድናቂዎቼ መንገላታት ነው›› ሲል ተናግሯል፡፡ የቴዲ አፍሮ አድናቂዎች ሲቸገር የሚቸገሩ፣ ሲያዝን የሚያዝኑ፣ ሲያነባ አብረው የሚያነቡ ጊዜ የማይለውጣቸው ናቸው፡፡

ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ጉዳዩን እስር ቤት ሆኖ በሚከታተልበት ጊዜ ሞራሉ ሳይነካ፣ መንፈሱ ሳይረበሽ፣ በጠንካራ ሞራል ተገንብቶ እሱን ለመጠየቅ የሚመጡ ዘመድ አዝማድና ባልደረቦቹ በአጠቃላይ አድናቂዎቹን ሲያፅናና ታይቷል፡፡ ቴዲ በአሰበት ቦታ ሁሉ የፈጣሪው ጥበቃ አይለየውም፡፡

በአመርቂ የጥበብ ስራው ክብር የተቸረውና በቅርቡ ከዝነኝነት ድልድይ በመሻገር የልዕልና ክብር የተጎናጸፈው የዚህ ታላቅ ሰው እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ላይ የእግዚአብሔር እጅ አሰበት፡፡ ስለሆነም የሚወደው አምላኩ ለክፉ ነገር አሳልፎ አይሰጠውም፡፡ ወጣቱ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ በእስር ቤት ቆይታው ‹‹አስቸጋሪ ነገሮች ይበልጥ ያጠነክሩኛል፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ሁሌም ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ስለዚህ ፍርሃትና ሽብር ከእኔ ዘንድ የሉም፡፡ እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርግ ደግሞ አያፍርም›› ብሏል፡፡

* * *

ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም ከሳሽ አቃቤ ህግ ባቀረበው የፅሁፍ ማስረጃ ላይ፣ ሟች የተገጨበትን ቢ ኤም ደብሊው መኪና የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ እንዲሁም የምኒሊክ ሆስፒታል የሟችን





አስከሬንና ሟች ሰውነቱ ውስጥ ደም መፍሰሱን የሚያሳዩ የፎቶ ግራፍ መረጃዎች አቅርቧል፡፡ በቀረቡት መረጃዎች ላይ የቴዲ ጠበቃ አቶ ሚሊዮን አሰፋ ለፍርድ ቤቱ በሰጡት አስተያየት የመኪናው ፎቶ ግራፍ አደጋው ደረሰ በተባለበት ሰዓት ስለድርጊቱ የሚያስረዳው ምንም ጭብጥ እንደሌለ፣ የምኒሊክ ሆስፒታል የአስከሬን ምርመራ ውጤትም የመረመሩት ዶ/ር ስምና ፊርማ ብሎም ቲተር የሌለው መሆኑን፣ ሟች የቅጥቀጣ ድርጊት የደረሰበት እንጂ የመኪና አደጋ ለመድረሱ የሚያስረዳ አለመሆኑን ገልፀው ብዙ አይነት ቅጥቀጣ ስላለ ይህ ማስረጃ ክሱን የማስረዳት ብቃት የሰውምና የተከበረው ፍርድ ቤት ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት ደንበኛዬን በነፃ ያሰናብትልኝ ሲሉ ተማፅነዋል፡፡ በዚህ ዕለት አቶ ሚሊዮን ባሳዩት የጥብቅና ክርክር ብቃት ተከሳሽ ቴዲ አፍሮ ከፊቱ ገፅታ የደስታ መንፈስ ይነበብበት ነበር፡፡

የተከበሩ ዳኛ የግራና ቀኝ ክርክሩን ካዳመጡ በኋላ ለሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ.ም ቴዲን ለብይን ቀጠሩት፡፡ በዚህ ቅፅበት የቴዲ እናት እንባቸው ፈሰሰ፡፡ ‹‹ልጄ ሆዴ! ምን ልሁንልህ?›› እያሉ በአሳዛኝ ድምፅ ያለማቋረጥ ሲያለቅሱ በድንገት ቴዲ አያቸው፡፡ እሱም የእናቱ ማዘንና የአድናቂዎቹ መጉላላት ስላሳዘነው እንደ እናቱ እንባውን አፈሰሰ፡፡ ጉዳዩን ሲከታተሉ የመጡ አድናቂዎቹ፣ ጋዜጠኞችና አንዳንድ ቤተሰቦቹ ሳይቀሩ ሁሉም እንባ እየተራጩ ፍቅራቸውን ገለፁ፡፡

ቴዲ እንደቀልድ ወደ እስር ቤት ቢገባም ከእስር ቤት ቶሎ ይለቀቃል የሚል እምነት የሁሉም ነበር፡፡ ይሁንና ዛሬ ነገ ይፈታል ሲባል ወራቶችን በእስር ቤት አስቆጥሮ ነበር፡፡ ሐምሌ 7 ቀን 2000 ዓ.ም የ32ተኛ የልደት በዓሉን በእስር ላይ ሆኖ ሰማክበር ተገዷል፡፡

* * *

ህዳር 26 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ደግሞ ክቡር ፍርድ ቤቱ የግራና የቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በሁለቱም የክስ

ወንጀሎች በስድስት ዓመት እስራትና በ18 ሺህ ብር የቅጣት ውሳኔ አስተላለፈበት።

በቴዲ ላይ የተወሰነውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ለአድናቂዎቹ ከባድና መሪር ሀዘን ሆኖ ታይቷል። በወቅቱ በርካታ አድናቂዎቹ፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ጋዜጠኞች በችሎቱ ተገኝተው ነበር። ይህ የቅጣት ውሳኔ በአፍሪካና በአውሮፓ የዜና ማዕከናትም ተዘግቦ ከመቶ በላይ በሆኑ የዜና አውታሮች ተሰራጭቶአል።

ከውሳኔው በኋላ በርካታ የቴዲ አፍሮ አድናቂዎች እሱ ወዳሰበት እስር ቤት በመሄድ ‹‹አይዞህ በርታ እግዚአብሔር ያስፈታህ›› በማለት ፍቅራቸውን ገልጸውለታል። ይህን ጊዜ ወጣቱን የሙዚቃ አብዮተኛ ቴዲ አፍሮን ለመጠየቅ ከመቼውም ጊዜ በላይ እስር ቤቱ እንደ ማዕበል በሚጎርፍ ሕዝብ ተጥለቅልቆ ይታይ ነበር።

ከሁሉም በላይ ግን ለባዕድ ወገኖች አግራሞትን የፈጠረ ምርኩዝ የተደገፉ አረጋውያን፣ ማየት የተሳናቸው፣ አካል ጉዳተኞች፣ የውጪ ዜጎች፣ ጨቅላ ሕፃናቶች ሳይቀሩ ወላጆቻቸውን አስከትለው ቴዲን ለመጠየቅና ለእሱ ያላቸውን ሐይለኛ ፍቅር ለመግለጽ ስንቁን ኬላ ጥሰው ሐገርና ድንበር አቋርጠው በቃሊቲ ግቢ መገኘታቸው ነው። ቴዲ እርሱን ሊጠይቁት የመጡትን በሙሉ ከፊቱ ላይ ሁሌ የማይጠፋውን ፈገግታ እንደ አንፀባራቂ ዕንቅ እየተንቦለቦለ ፍቅርና ታላቅ ትህትና የተላበሰ ኢትዮጵያዊ ጨዋ ባህሪ እየለገሳቸው በማረሚያ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙትን የስስላሳ መጠጥ ዓይነቶችን እየጋበዛቸው የልቡን ይጫወት ነበር። አንዳንድ አስቂኝ ቀልዶችን ጣል እያደረገ ጠያቂዎቹን ያዝናናም ነበር።

* * *

ብዙም ሳይቆይ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘው ተከሳሽ ቴዲ አፍሮ የተጣለበትን የቅጣት ውሳኔ በመቃወም ባቆማቸው ጠበቆቹ አማካኝነት ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ





ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተፈጸሙብን ያሉትን የህግ ስህተቶች በሙሉ አንድ በአንድ በመዘርዘር የይግባኝ ጥያቄያቸውን አቀረቡ። ይግባኝ ሰሚውን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን አጽድቆ መዝገቡን መርምሮ ለተከሳሽ ውሳኔ ለማሰማት ለየካቲት 11/6/2001 ዓ.ም ጊዜ ቀጠሮ ሠጠ። ብዙዎች ቴዲ በይግባኙ መሰረት ይፈታል የሚል ትልቅ ተስፋ ነበራቸው።

ቀኑ ደረሰና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የወንጀሉን ዝርዝር በንባብ ካሰማ በኋላ ቴዲ አፍሮን ‹‹የወንጀሉን ድርጊት እንደፈጸምከው ተመስክሮብሃል። ነገር ግን ሟች የወንጀሉ ድርጊት እንዲፈጸም ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ምክንያቱም መሀል አስፋልት ላይ ያለአግባብ በስካር መንፈስ ሲንቀሳቀስ ነበር›› በማለት በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተወሰነውን የስድስት ዓመት የእስራት ጊዜ ወደ ሁለት ዓመት የእስራት ጊዜ፣ የገንዘብ ቅጣቱ ደግሞ ከብር አስራ ስምንት ሺህ ወደ አስራ አንድ ሺህ ብር ዝቅ እንዲል ውሳኔ ማስተላለፉን አሳወቀ። በዚህ ዕለት የችሎቱን ሂደት ለመከታተል በ/ፍ/ቤቱ የተገኙ የቴዲ አድናቂዎች በእንባ ሲራጩ ተስተውለዋል።

ነገር ግን አሁንም ቢሆን ከሳሽ ዐቃቢ ህግ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘቱ ለሰበር ሰሚው ክቡር ፍርድ ቤት የቅሬታ ነጥቦቹን በመዘርዘር ይግባኝ አለ።

ይግባኝ ሰሚውም ሰበር ፍ/ቤት የሁለቱን ተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ ቅሬታ ለመስማት ለሚያዝያ 14, 2001 ዓ.ም ቀጠሮ ያዘ። በተያዘውም ቀነ ቀጠሮ መሰረት ችሎቱ በሦስት ዳኞች ተሰይሞ የቴዲ አፍሮ በርካታ አድናቂዎችና ጋዜጠኞች በተገኙበት ተጀመረ። የተከበረውም ይግባኝ ሰሚ ሰበር ፍ/ቤት የቅሬታን ሐሳብ ለመስማት በመጀመሪያ ከሳሽ ለሆኑት ዐቃቢ ሕግ እድል ሰጠ። ዐቃቤ ህጉም ተፈጸመብኝ ያሉትን የህግ ስህተትና ጉድለት አንድ በአንድ እየጠቀሱ ለፍ/ቤቱ አቀረቡ።

የአቃቤ ህግ የቅሬታ ነጥብ የነበረው፣ «ከፍተኛ ፍ/ቤት

የተከሳሽን ጥፋተኝነት አረጋግጦ በስድስት ዓመትና በአስራ ስምንት ሺህ ብር እንዲቀጣ የወሰነውን የቅጣት ውሳኔ ተከሳሽ የቅጣት ማቅለያ ሐሳብ ባላቀረበበት - ያውም ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎ ይግባኝ በጠየቀበት - ሁኔታ፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በራሱ ጊዜ የራሱን ማቃለያ ሐሳብ አቅርቦ ቅጣቱን ሊያቀልለት አይገባም›› የሚል ነበር። በመቀጠልም «ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ማቅለል ቢፈልግ እንኳን ሁለቱን ተከራካሪዎች በሚጠቅም መልኩ መጀመሪያ ቅጣቱን አክብዶ ከዚያ ወደ ቅጣት ማቅለያ ውሳኔ ይሄዳል እንጂ ቅጣቱ ከመነሻው ዝቅ ተደርጎ መወሰን አልነበረበትም። ምክንያቱም ተከሳሽ ተደራራቢ ወንጀል ፈጽመው ሳለ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ቅጣቱ ከመነሻው ዝቅ አድርጎ ነው የወሰነው። ስለዚህ አሁን ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት ቅጣቱን ያቀለለው ያለአግባብ ነው ተብሎ ከፍተኛው ፍ/ቤት የወሰነውን የመጀመሪያ ውሳኔ እንዲጸና እጠይቃለሁ›› በማለት ለሰበር ሰሚው ክቡር ፍ/ቤት ተቃውሞአቸውን አሰምቷል።

በመቀጠል ለሰበር ቅሬታ ሰሚው ክቡር ፍ/ቤት አቤቱታቸውን ያሰሙት የተከሳሽ አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን ጠበቃ አቶ ሚሊዮን አሰፋ ነበሩ። «ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረብናቸው አስራ ሦስት የይግባኝ ቅሬታ ነጥቦች በዝምታ በማለፍ አንቀጽ 26/6 የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 181፣185 እና 195 ድንጋጌዎችን በግልጽ በሚቃረን መልኩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞብናል። ዐቃቤ ህግ ባቀረበብን የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ ተከሳሽ ቴዎድሮስ ካሳሁን እያሽከረከረ ሲገጭ አየሁ የሚል ምስክር ሳይቀርብብን አደጋውን ያደረሰው እርሱ ነው ብሎ መወሰን ከፍትህ ስርዓት ውጪ ከመሆኑም በላይ ወሳኝ ሰብዓዊ መብት የጣሰ ውሳኔ ነው›› ካሉ በኋላ «ስለ አደጋው አፈጻጸም የዐቃቤ ሕግ ምስክር አንደኛው ሟች በወደቀበት መኪናው በእግሩ ላይ ሄደበት ሲል ሁለተኛው ምስክር ደግሞ ሟች ከጓደኛው ጋር እየተጎተቱ ወደቀና የመኪናው የፊት አካል መታው የሚል ነው። እናም የምስክሮቹ የምስክርነት ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭ ሆኖ ሳለ ተቀባይነት ማግኘቱ ትክክል አይደለም። ሟች የሞተበት ቀንና ደንበኛዬ ለስራ ከሄደበት ውጪ





ሃገር ተመልሶ ʻአ.አ. የገባበት ቀን የተለያዩ በመሆናቸው ፍ/ቤቱ እነኚህ ጉዳዮች በጥልቀት አይቶልን በህጉ የተጠቀሱትን የማቅለያ ነጥቦች ተጠቅሞ ደንበኛዬን በነፃ እንዲያሰናብትልኝ፣ ይህ ካልሆነ እስካሁን የታሰረው እንደ በቂ ተቆጥሮ እንዲለቀቅልኝ እጠይቃለሁ›› በማለት ችሎቱን ጠየቁ።

ከሳሽ ዐቃቤ ሕግ ካቀረባቸው የቅሬታ ነጥቦች መካከል በሰበር ሰሚው ክቡር ፍ/ቤት ተቀባይነት ያገኘለት ‹‹ተከሳሽ ተደራራቢ ወንጀል ፈጽመው እያለ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቅጣቱን ከመነሻው ዝቅ በማድረግ እንዲፈጸም አድርጓል›› የሚለው የቅሬታ ነጥብ ነበር።

በሌላ በኩል የተከሳሽ ቴዲ አፍሮ ጠበቆች ለሰበር ሰሚው ክቡር ፍ/ቤት ካቀረቡዋቸው ወደ አስራ ሦስት ገደማ የቅሬታ ነጥቦች መሀል አንዱም እንኳን ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶአል። ከነዚህ የቅሬታ ነጥቦች መካከል የምስክሮች ቃል እርስ በእርስ መጋጨት፣ ሟች የሞተበትና ተከሳሽ ቴዎድሮስ ካሳሁን ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ቀን የተለያየ መሆን፣ የዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የህክምና ማስረጃ አለመጣጣም፣ ተከሳሽ ቴዎድሮስ ካሳሁን በመኪና ሰው ሲገጭ አይቼዋለሁ የሚል የዓይን ምስክር አለመኖር. . . የሚሉና ሌሎች አቤቱታዎች ይገኙባቸዋል።

ስበር ሰሚው ፍ/ቤት በዕለቱ የቴዲ አፍሮ ጠበቆች ያቀረቧቸውን የቅሬታ ነጥቦች «ማስረጃ ምዘናን በሚመስል መልኩ የቀረቡ ናቸው» እንዲሁም «በቀን ልዩነቱ ላይ ሃሰተኛ ሰነድ ማቅረብ እና ስህተት ያለበትን ሰነድ አስተካክሎ ማቅረብ ልዩነት አለው›› ብሎ መልስ ከሰጠ በኋላ «ለሰኔ 11 ቀን 2001 ዓ.ም ቀጠሮ ይዘናል። በዚያ ዕለት ይህ መዝገብ አምስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ስለሚታይ ከሳሽ ዐቃቢ ሕግም ሆነ የተከሳሽ ጠበቆች ያሏቸውን የመከራከሪያ ሐሳቦች በማቅረብ መከራከር ይችላሉ» በማለት አብራርቶ የዕለቱ ችሎት አብቅቷል።

የሴከንዶች ፍጥነት፣ የደቂቃዎች ሩጫ፣ የሰዓታት እንደ አውሎ ነፋስ መክነፍ - ቀናቶች በሳምንታት፣ ሳምንታት በወራት እየተተኩ መቼ ይሆን ቀኑ የሚደርሰው ብሎ በጉጉትና በተስፋ የናፈቀው የቴዲ አድናቂ የራቀው ቀን አይደርስ የለ ደርሶ ቀኑ ደረሰ።

የዚህ ታላቅ ድምጻዊ መታሰር ለቤተሰቡ፣ ለጓደኞቹና ለአድናቂዎቹ የፈጠረባቸው የሀዘንና የትካዜ ድባብ የከፋ ህመም ከመሆኑም በላይ የእግር እሳት ሆኖ ሲሰበልባቸው ታይቷል። በዚች አለም ላይ የሚወዱትን ሰው እንደማጣትና የሚያደንቁትን ግለሰብ ክፉ ነገር እንደመስማት የሚያሳዝን፣ የሚረብሽ፣ የሚያናድድ፣ የሚስለቅስ፣ ነፍስን ለላም የሚነሳ ምን ነገር አለ? የወጣቱ ድምጻዊ ቴዲ አፍሮ አድናቂዎች እውነተኛ ከመሆናቸውም በላይ ለአርቲስቱ ያላቸው ፍቅርና ክብር ከማንም በላይ የላቀ ነው።

በዚህ ታላቅ የሀገሪቱ ድምጻዊ ላይ በከፍተኛው ፍ/ቤት የተላለፈውን የቅጣት ውሳኔ ማለትም ከስድስት ዓመት የእስራት ጊዜ ወደ ሁለት ዓመት የእስራት ጊዜ እና ከአስራ ስምንት ሺህ ብር ወደ አስራ አንድ ሺህ ብር ቅጣቱ መሻሻሉ አግባብ ነው ወይስ አግባብ አይደለም? የሚለውን ነጥብ መርምሮ ውሳኔ ለማስተላለፍ የተያዘው ይህ የዛሬው ቀጠሮ ቀን ተከሳሹ ቴዎድሮስ ካሳሁን ካለበት ማረሚያ ቤት ካለመቅረቡ የተነሳ ክቡር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ቀጠሮውን ወደ ሰኔ 14, 2001 ዓ.ም አዛውሮታል።

በዚህም መሰረት ሰኔ 14, 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከሳሽ ዐቃቢ ህጉ ተፈፅሟል ያሉትን የሕግ ስህተት ለይግባኝ ሰሚው ሰበር ፍ/ቤት በዝርዝር አሰምተዋል። በተመሳሳይ መልኩም የተከሳሽ ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁንም ጠበቆች የቅሬታ ነጥቦቻቸውን አንድ በአንድ ለፍ/ቤቱ አብራርተዋል። ሰበር ሰሚው ፍ/ቤት የግራና የቀኝ ክርክሩን ካደመጠ በኋላ ቅጣቱ መሻሻሉ አግባብ ነው ወይስ አግባብ አይደለም? በሚለው ላይ ውሳኔን ለመስጠት ለሰኔ 25/2001 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቶ የእለቱ ችሎት ተነስቷል።





ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን ከችሎቱ በፖሊሶች ታጅቦ ሲወጣ የእለቱን ችሎታ ሲከታተሉ የመጡ አድናቂዎች ስሙን አወድሰው በመጥራት «.... ቴዲዬ.... እንወድሀለን። አይዞህ!! እግዚአብሔር ያውቃል» ሲሉ ፍቅራቸውን ገልጠውለታል።

አዎን የወጣቱ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን መታሰር በቤተሰቦቹና በአድናቂዎቹ ላይ የፈጠረው ሀዘንና ትካዜ ስር የሰደደ ቢሆንም ሁሉም ያን የሚናፍቁትን፣ የሚወዱትን፣ የሚሳሱለትንና የሚንገበገቡለትን ቴዲ አፍሮን ከእስር እንደሚያስፈታው ተስፋቸውን የጣሉት በዚያ የተስፋ አባት በሆነው እግዚአብሔራቸው ላይ ነው።

በትልቅ ተስፋና ጉጉት ሲጠበቅ የነበረው ሰኔ 25/ 2001ዓ.ም መድረሱ አልቀረም ደረሰ። በዚህ እለት ይግባኝ ሰሚው ሰበር ፍ/ቤት ውሳኔ ይሰጣል ተብሎ በመጠበቁ ምክኒያት የድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ቤተሰቦች፣ አድናቂዎች፣ ጋዜጠኞችና የውጭ ዜጎች ችሎቱን አጣበውት ነበር።

ሆኖም ይግባኝ ሰሚው ሰበር ፍ/ቤት ‹‹መዝገቡ ተመርምሮ ስላላለቀ በዚህ ቀን መወሰን ያስቸግራል። በዚህ የተነሳ አንድ ቀጠሮ ያስፈልጋል›› በማለት ለሀምሌ 9/2001 ዓ.ም ቀነ ቀጠሮ ተያዘ። በበርካታ ህዝብ ዘንድ በተስፋና በጉጉት የተጠበቀው ሰኔ 25/2001 ዓ.ም ሀምሌ 9/2001 ዓ.ምን የጭንቀት ቀን አርግዞ አለፈ። በዚህ ቀን ቴዲ አፍሮ ከችሎት ጠባቂዎቹ አማካኝነት ታጅቦ ሲወጣ አድናቂዎቹ በእንባ ጅረት ታጥበው ሲንሰቀሰቁ ተስተውለዋል። ሀምሌ 9/2001 ዓ.ም ምን ይዞ ይመጣ ይሆን? ለብዙዎቹ የምጥ ቀን እንደሚሆን ቅንጣት ታክል ጥርጥር አልነበረውም። ከእያንዳንዱ የቴዲ አድናቂ ይወጣ የነበረው የጭንቀት እስትንፋስ ከጋለ ብረት ባልተናነሰ መልኩ ወላፈኑ ይጋረፍ ነበር።

* * *

ሀምሌ 9/2001 ዓ/ም ለውሳኔ በተያዘው ቀጠሮ መሠረት ዐቃቤ ህግ ያቀረባቸውን ሀሳቦች ሳይቀበል ቀርቶ «ተከሳሽን ከሁለት አመት የእስር ጊዜ በላይ የሚያስቀጣው ሆኖ አሳገኘነውም፡፡ በገንዘብ መቀጮው በኩል ግን ከመጀመሪያው ቅጣት ለምን እንደተቀነሰ መዝገቡ ላይ በዝርዝር ስላልተጠቀሰ በነበረበት በ18ሺህ ብር እንዲጸና ውሳኔው አስተላልፈናል» በማለት ውሳኔውን አሳወቀ፡፡ ይህ ውሳኔ በተሰማበት እስት ስድስት ኪሎ በሚገኘው ሰበር ፍ/ቤት ተገኝተው የነበሩ የድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ቤተሰቦች እንዲሁም በርካታ አድናቂዎቹና ጋዜጠኞች በተሰጠው ውሳኔ ፈንጥዘው ችሎቱን በእልልታ አናወጡት፡፡ ከፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ውጭም አድናቂዎቹ የቴዲ ምስል ያለበትን ቲሸርት በማውለብለብ ጭፈራውን አቀለጡት፡፡ ስሙንም አብዝተው እያነሱ አወደሱት፡፡ «ዛሬ የኛ ቀን ነው፡፡ እግዚአብሔር ፈረደልን» ሲሉም ተደምጠዋል፡፡ በቴዲ አፍሮ መታሰር ተፈጥሮ የነበረው ሀዘን፣ ትካዜና ብስጭት በአንዴ እንደ ጉም የተነነ መስሎ ታየ፡፡ የቤተሰቦቹና የአድናቂዎቹ የደስታ ዕንባ ገደብ አጥቶ እንደ ሰማይ ዝናብ ተንጀረጀረ፡፡

ወጣቱ የጥበብ ከያኒና ምርጥ የዜማና የግጥም ደራሲ እንዲሁም ድምፀ መረዋው መልከ መልካሙ ድምጻዊው ቴዎድሮስ ካሣሁን በይግባኝ ሰሚው ሰበር ፍ/ቤት የተላለፈበትን የሁለት ዓመት የእስራት ቅጣት ውሳኔ ነሐሴ 7/2001 ዓ.ም ከምሽቱ 12:00 ሰዓት ገደማ አጠናቆ በመጨረሱ ከእስር ቤት የወጣበት ልዩ የደስታና የፈንጠዝያ ቀን ሆነች፡፡

ቴዲ ከሚያዝያ 8/2001 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 7 ቀን 2001 ዓ.ም በጥቅሉ የአንድ አመት ከአራት ወራት ጊዜ እስር ላይ ሆኖ አሳልፏል፡፡ በዚህ የእስር ቆይታው ከህግ ታራሚዎችና ከማረሚያ ቤቱ የጥበቃ ኃላፊዎች ጋር መልካምና የጠበቀ ግንኙነት የነበረው ቴዲ አፍሮ በተፈጥሮ ከተቸረው በርካታ ነገሮች አንዱና ዋናው መልካም ስብዕናው በእስር ላይም እያለ በይፋ ታይቶለት ተወዳጅነትን አትርፎለታል፡፡





በርካታ ‹‹እሱ በተፈታና እኔ በታሰርኩለት›› በማለት እንባቸውን እያፈሰሱ እራሳቸውን ለመስዋዕትነት እስከማዘጋጀት የደረሱና ‹‹ቴዲ እኮ የፍቅር ተምሳሌት፣ የሰላም አርማ ነው›› ብለው ያሚያሞካሹት እነዚህ አድናቂዎቹ ከመፈታቱ ሁለት ቀናት አስቀድመው ነበር የቃሊቲን ማረሚያ ቤት ደጅ መጥናት የጀመሩት፡፡ በተፈታበትም ሐሙስ ቀን እርስ በእርስ ተቃቅፈው በመሳሳም የደስታን እንባ እያነቡ ፈጣሪያቸውን ሲያመሰግኑና ሲጨፍሩ ነበር፡፡ የታላቁ ድምጻዊ ቴዲ አፍሮ የመፈታት ብስራተ ዜና ከሀገሩ መገናኛ ብዙኃን አልፎ በርካታ የአለም የዜና አውታሮች ዘግበውለታል፡፡ ኢትዮጵያዊ የኮከቦች ሁሉ ኮከብ ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን ከእስር ተፈታ በማለት አሞካሽተው ስለጀግንነቱም መስክረውለታል፡፡

# 20

# በቴዲ መታሰር ያጋጠመ ታላቅ ክፍተት!!

በያዘው የሙዚቃ ስራ ላይ ማንም ሊነቅለው የማይችል ታላቅ የጥበብ ስራ የሰራ፣ ጊዜና ወቅት ጠብቀው ለህዝብ ጆሮ በሚያደርሳቸው ጣፋጭና መሳጭ የሙዚቃ ስራዎቹ ከታሪክም የዘለለ ዘመን ተሻጋሪ ዘለአለማዊ ታሪክ የሰራ ወጣቱ ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን አሁን የሀገራችን የዘፋኞች ቁንጮ ሆኖ የወጣ ምርጥ ከያኒ ነው። የጥቂቶች ብቻ ሳይሆን የሚሊዮኖች ምርጫም ሆኗል።

ቴዲ አፍሮ የሀሳብ ባለፀጋ፣ የዜማ ባለህብት፣ የግጥሞም አምራች፣ የመልካም ባህሪ ተምሳሌት፣ አስተዋይ፣ ተጫዋችና ጥንቁቅ ከመሆኑም በላይ በፍቅርና በመግባባት፣ በመደጋገፍና በመቻቻል የሚያምን ድንቅ አርቲስት ነው። ብዙዎች የፈጠራ ስራዎቹን እያዳመጡ ደስታን ሲሸምቱ ቆይተዋል። እሱም አቡጊዳን ለህዝብ ጆሮ ካደረሰበት 1993 ዓ.ም አንስቶ በተሽከርካሪ ለው ገድሎ በማምለጥ ወንጀል ተከሶ ሚያዚያ 8, 2000 ዓ.ም ለእስር እስከተዳረገበት ቀንና ሰዓት ድረስ ከሀገሩ ምድር ኢትዮጵያ አልፎ እስከ ባህር ማዶ ሀገራት ድረስ በመዟዟር ታከተኝ ሳይል የሙዚቃ





ስራዎችን በፍቅር ሲያቀርብ ቆይቷል።

ያች የብዙዎችን እንባ ያፈሰሰች የቀን ጎዶሎ ስንቶችን ለሀዘንና ትካዜ ዳርጋለች? ያች ክፉ ቀን ሚያዚያ 8, 2000 ዓ.ም ቴዲን ለእፎር ዳረገች። ወጣቱ ከያኔ ቴዎድሮስ ካሳሁን ሲታሰር ሙዚቃም አብራ የታሰረች መሰለች። የዘፈን መድረኮችን ፅልመት ጋረዳቸው። የሙዚቃ አፍቃሪያን በሙሉ ዘፈንን ለመስማት ጆሮቻችንን አንሰጥም አሉ። ለምን ከተባለ ከቴዲ አፍሮ ሌላ በዘፈን የልባችንን ማን ያውቅልናል? የሚገርም አዲስ ፈጠራስ ከማን እናገኛለን? ያለን አማራጭ የቴዲን የራሱን ዘፈኖች ደግመን ደጋግመን እየሰማን ለቸሩ ፈጣሪያችንን ቴዲ እንዲፈታለን ዘወትር የልመና ፀሎት እናቀርባለን ሲሉ ተደምጠዋል።

አርግጥ ነው ቴዲ ለእስር ከተዳረገበት ጊዜ አንስቶ ቀድሞ የነበረው የዘፈን የደራ እንቅስቃሴ በአንዴ ነበር የተገታው። ይህ ደግሞ የሚያመለክተው ለሙዚቃው ኢንዱስትሪ አንዱና ዋናው አንቀሳቃሽ ሞተር ቴዲ እንደሆነ ነው። ቴዲ ከታሰረ በኋላ የሙዚቃው እንቅስቃሴ በከፊል ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ ሞቶ ነበር ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል። ምክንያቱም ቴዲ አፍሮ ለዚህ ትውልድ የሚስማማ ከያኔ ከመሆኑም በላይ በሚያቀነቅናቸው ዘፈኖች አፍቃሪውን ህዝብ ከማስደሰት አልፎ የአገርን ክብርና ኩራት የሚቀሰቅስ አርቲስት በመሆኑ ነው።

በዚህ የተነሳ በቴዲ መታሰር ምክንያት ሙዚቃን ያያችሁ? የት ገባች እባካችሁ? እየተባሉ የሙዚቃ አፍቃሪና አድማጮች በትካዜ ያወጉ ነበር። ነገሩ በእንዲህ ሁኔታ እያለ ወጣቱ ድምፃዊም የህይወት ፈተናን፣ የእስራትን ጉዳት እየተጋፈጠ ባለበት ጊዜ የቴዲ ሁለት ነጠላ ስራዎች ህዝቡ ዘንድ ደረሱ። “አይን አፋር ነኝ” የሚልና ያለምንም አጃቢ ሙዚቃ በደረቅ ድምፅ የተቀረፀ “ላምባዲና” የተሠኙ ሁለት ዘፈኖች ሀያ አራት ለአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በመላው ሀገሪቱ ተዳረሱ። በየመኖሪያ ቤቱ፣ በየመዝናኛው ስፍራው፣ በየታክሲዎች ውስጥ የቴዲ ድምፅ ከፍ ብሎ ተሰማ። “አይን አፋር ነኝ” የሚለው

ነጠላ ዜማ የቴዲ አፍሮን ታላቅ ከያኒነት እንደገና ያስመሰከረ ምርጥ ሥራ ከመሆኑም ባሻገር በወቅቱ ሞቶ የነበረውን የሙዚቃ እንቅስቃሴ እንዲነቃቃ አደረገ።

ይህ ስራ ከየትኛው የሙዚቃ እስቱዲዮ እንደተሰቀቀ ለጊዜው ባይታወቅም ህዝብ ግን በደስታ የፈነጠዘበት ዜማ ነበር። ይህን ያልተጠናቀቀ ጅምር ሥራ፣ ምናልባትም ያሰባሰቤቱ ፍቃድ የተለቀቀ ዜማ አጣጥሞ ያደመጠ ሁሉ የቴዲ ጭንቅላት የዜማ ምንጭ አፍላቂ እና ተፈጥሮ ፀጋዋን አብዝታ የቸረችው እንደሆነም በአግራሞት ከመመስከር ወደ ኋላ አይልም።

ሌላው "ላምባዲና" የተሰኘ በደረቅ ድምፅ የተቀረፀን ሥራ ያደመጡ በሙሉ "ቴዲን በዘፈን መግታት አይቻልም፣ ጥልቅ የሆነ የዜማ፣ የግጥምና የሃሳብ ተስጥኦ ያለው ነው" ሲሉ አወድሰውታል።

እነኚህ ሁለት ነጠላ ዜማዎች ያለ ቴዲ ፍቃድ ለህዝብ ቢቸበቸቡም፣ ቴዲም ካለበት የህግ ጥላ ስር ሆኖ ቅር ቢለኝም፣ ህዝብ በዘፈኖቹ እንደተደሰተባቸው ሲነገረው በፈጠራ ስራዎቹ ያለፍቃድ መለቀቅ ብዙም አልከፋውም። ምክንያቱም ቴዲ የሰዎችን ደስተኛ መሆን ስለሚያስደስተው። ለበርካታ ህዝብ ግን አግራሞትን የፈጠረው እኔ ጎበዝ ዘፋኝ ነኝ፣ ከማንም አላንስም ብለው ለሚፎክሩ አንዳንድ ዘፋኞች የሙዚቃ ስራዎቻቸውን ለህዝብ ቢያደርሱም ከህዝብ ያገኙት ምላሽ ከዘፋኝነት ይልቅ ሌላ ሙያን እንዲሰሩ የሚያሳስባቸው መሆኑ ነው።

አንድ ካሴት ሰርቶ "ተጠንቅቄና ተጠብቤ የሰራሁት ነው" እያለ በየሚዲያው ደስክሮ ሲያበቃ ግን ደግሞ ሥራዎቹ ተቀባይነት አጥተው ህዝብ ጆሮ የነሳው ማንም ዘፋኝ፣ የቴዲ ስራዎች ለምን ሊወደዱ ቻሉ? በማለት ራሱን መጠየቅ አለበት። ምክንያቱም ሙዚቃ የነፍስ ቋንቋ፣ የሥጋ እርካታ፣ የመንፈስ ምግብ፣ ደስታና ሀሴት ስለሆነች የሚጠበቧት ጥበበኞችን ትፈልጋለች። የጥበብ ከያኔ የመሆን ታላቅነትም ማንም በቀላሉ አይታደለውም። ነው። "ጥበብ ዝም ብላ





የምትቀዳ የወንዝ ውሃ አይደለችም።" በተፈጥሮ የምትለገስ በግል ጥረት ተኮትኩታ የምታድግ ታላቅ በረከት እንጂ።

ቴዲ አፍሮን በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የሰው ልጆች ካለምንም ነገር ስሙን እያወደሱ ሊወዱት አልቻሉም። በየጊዜው እንደማዕበል የሚጎርፈው የአድናቂዎቹ ቁጥር የጨመረውና በከፍተኛ ሁኔታ የሰው ልጆችን ፍቅር ያገኘው በገንዘብ ገዝቶት ሳይሆን ከፈጣሪ በተሰጠው ክህሎቱ ነው። በሌላ አባባል ጥበብ ለቴዲ አፍሮ አድልታለት ሳይሆን ፈጣሪ ጥበበኛ አድርጎ ስለፈጠረውና ጥበብን እንዴት እንደሚጠቀምባት በሚገባ ያወቀ ምርጥ ከያኒ በመሆኑ ነው።

ቴዲ አፈጣጠሩ የሚገርም ሥራዎቹ ብዙዎቹን የሚማርኩ፣ የእልፎችን ልብ የሚኮረኩሩ፣ የሚሊዮኖችን ጆሮ የሚገዙ፣ የማይሰለቹ፣ ሁልጊዜ አዲስና ህያው ናቸው።

ቴዲ ዜማም ይሁን ግጥምን ለመቀመርና ለመድረስ አይጨነቅም። ምክንያቱም በውስጡ ያለና የታደለው ክህሎት ስለሆነ። ያለውን ነገር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተና እያሳደገ የፈጠራ ሙያውን ከፍ በማድረግ ላይ ያለ ታላቅ ጥበበኛ ነው። ጥበብ ለቴዲ ውድ ስጦታው ነች። የቴዲ የፈጠራ ሙያ አያልቅም። ሁልጊዜ እንደ ምንጭ ውሃ የሚፈልቅ ነው። ለራሱም ሆነ ለስራ ባልደራቦቹ የተጠቀመውና እያበረከተው ካለው ላይ ገና እጅግ በጣም ጥቂቱን የፈጠራ ስራውን ነው ማለት ይቻላል።

ቴዲ አፍሮ ምን ጊዜም ቢሆን ለሚወደው የሙዚቃ ህይወቱ ወደ ኋላ የማይል፣ በቁርጠኝነት የተነሳ የጥበበኛ ልጅ ጥበበኛ ሰው ነው። አርቲስቱ የተፈጠረው ለጥበብ ስራ ነው። እንደሌላው አርቲስት በስሜት ተገፍቶ ሮጦና ተንደርድሮ ወደ ሙዚቃ አለም አልገባም።

ቴዲ ዘፈን የሚሰራው በደመ ነብስ ወይም በይሆናል ግምታዊ መንፈስ ሳይሆን ተፈጥሮ በለገሰችው እውነተኛ ጥበባዊነቱ ነው። ደግሞም የቱ ዜማ ከየቱ ግጥም ጋር አብሮ መቀናጀት እንዳለበት ጠንቅቆ የሚያውቅ ጥበበኛ ነው።

ቴዲ አፍሮ ባይኖር ኖሮ የሀገራችን የሙዚቃ እድገትና የሙዚቃ ሰዎች ንዋያዊ ጥቅም ሆነ መንፈሳዊ እርካታ እዚህ ይደርሳል ተብሎ አይታሰብም። እንዲያውም ሙዚቃ ድሮ እንደነበረው ጠመዝማዛና የፅልመት መጋረጃ የተነጠፈበት አሰልቺ የህይወት ጉዞ ይሆን ነበር።

በቴዲ አፍሮ የተከሰተውን ለውጥና እድገት ሳንዋሽ ከልብ በቀናነት እውነቱን ከተናገርን ቴዲ ዛሬም ነገም እስከ ወዲያኛውም ዘመን በሙዚቃው ኢንዱስትሪ ውስጥ የለውጥ ሀዋርያ መሆኑን ነው። ስለሆነም ቴዲ አፍሮ ለሙዚቃው ኢንዱስትሪ የማይዋሽና ሊካድ የማይቻል ወሳኝ እርቲስት እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል!





21

## ቴዲ አፍሮ የማን ነው?

በህበሻነት መኩራት ድንቅ ስጦታ ነው። ኢትዮጵያ አምላኳ ከሰገሳት ብርቅዬ የተፈጥሮ መስህቦችና ሀብቶች በላይ ህዝቦቿም ልዩ፣ ተፈላጊና ማራኪ ናቸው። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በየተሰማራበት ሙያ ራሱንና ወገኑን ለመጥቀም የሚሯሯጥ፣ ሀገሩን አሳድጐ ከባለጸጐች ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ በየፊናው ጐንበስ ቀና የሚል ጨዋ፣ ታታሪና ብርቱ ህዝብ ነው።

ከአምላክ ስጦታዎች ሁሉ የላቀ ድንቅ ስጦታ ጥበብ እንደመሆኑም መጠን ይህንን ውድ የጥበብ ስጦታ ከታደሉ ጥቂት ሀገራት ውስጥ ኢትዮጵያ ቀደምት ተጠቃሽ ናት። የሰው ልጅ መገኛ ከመሆኗም በላይ አባቶቻችን የዛሬ ሦስት ሺ ዓመት የተጠበቡት ጥበብና ያቆዩልን ቅርስ ለዝንተ ዓለም የሚያኮራና የሚያስከብረን ታላቅ ታሪክ ነው።

አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያውያን አምላካቸው በቸራቸው ድንቅ የጥበብ ተክህሎ አማካይነት ታሪክ በመስራት ላይ ይገኛሉ:: ለወደፊቱም መስራታቸውን ይቀጥላሉ::

ዛሬ ላይ ሆነን - በተለይ ስለ ሙዚቃ ጥበብ ካነሳን - ከማንም በላይ ጉልቶና ደምቆ የሚታወስን ወጣቱ የሙዚቃ ንጉሥ ቴዲ አፍሮ ነው:: ብዙዎች በመልካም ባህሪውም ሆነ በሙዚቃ ፈጠራ ክህሎቱ ዘወትር የሚያደንቁት፣ ለሙዚቃ ዕድገት ፈር ቀዳጅ የሆነው ቴዎድሮስ ካሳሁን ለሀገሩ ኢትዮጵያ ያበረከተው መልካም ሥራና ያስመዘገበው ወደር-የለሽ ውጤት ዘወትር በብዙሃኑ ህዝብ በቁጥር አንድ የጥበብ ቁንጮ ላይ የሚያስቀምጠው ነው::

እቺ በየክፍለ ዘመኑ ጀግና መፍጠር የማይታክታት ታሪካዊት ሃገራችን ቴዲን አፍሮን የመሰለ ረቂቅ የክህሎት ባለቤትና የብዙዎች ሞዴል የሆነ ታላቅ ሰው በመፍጠር በሙዚቃ ጥበብ አማካኝነት ስንደቅ ዓላማዋን ከፍ አድርጋ ለማውለብለብ በቅታለች:: በተለይ በምስራቅ አፍሪካና በተለያዩ የዓለም ክፍላተ - ሀገራት ዘንድ በሙዚቃ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከፍተኛ የሙዚቃ ማዕበልን ያስነሳል ብለው ብዙዎቹ የሚናገሩለት ይህንን የመሰለ ብርቅ ሰው የኢትዮጵያ ልጅ በመሆኑ ለሀገሩና ለወገኑ የኩራት ምንጭ ሆነዋል:: "እንኳን ኢትዮጵያዊ ሆኖ ተፈጠረ!" በማለት ፈጣሪያቸውን ሌት ተቀን የሚያመሰግኑ ኢትዮጵያዊያን ቁጥር በአሁኑ ሰዓት ቀላል አይደለም:: ይህም ቴዲ አፍሮ በአሁኑ ሰዓት የመላው ኢትዮጵያ የህዝብ ልጅ ለመሆን የበቃ ታላቅ ሰው እንደሆነ ያስነገዘበናል::

ለዚህ ታላቅ ክብር የበቃው ደግሞ ለህዝቡ ካበረከተው ህያው ሥራ፣ ለወገኑና ለሀገሩ ካለው እውነተኛ ፍቅር፣ ከቅንነቱና ከበጐ አሳቢነቱ የተነሳ ነው::

በዚህ ሰዓት ስለቴዲ አፍሮ ከቤተሰቡ በላይ ስሙን በየቀኑ በማንሳት የሚያሞካሽውና "እሱን ጠብቅልን" የሚል አደራውን ለፈጣሪው አሳልፎ ሲሰጥ የሚሰማው እንዲሁም በደረሰበት ድንገተኛ





አሳዛኝ አጋጣሚ ቀን ከሌሊት ተግቶ በፀሎት ሲማፀን የነበረው ይህ ህዝብ ነው:: ለምን ቢባል አርቲስቱ የህዝብ ልጅ ሆኗልና::

ማንም ሰው - ምቀኝነት የተጠናወተው ካልሆነ በስተቀር - ቴዲ አፍሮን በሙዚቃ ሥራዎቹና በኢትዮጵያዊ ጨዋ ባህሪይው በፍጹም በክፉ አያነሳውም:: ለሰው ልጅ አስፈላጊ ከሚባሉ ምግብ፣ መጠለያና ልብስ በተጨማሪ የቴዲ አፍሮ ህዝብ ልጆች የአርቲስቱን ህልውና፣ የዕለት ተዕለት ክዋኔና አኗኗሩን፣ ያለበትን ሁኔታ፣ ሰላሙንና ጤንነቱን... በአጠቃላይ ስለ አርቲስቱ እያንዳንዷ እንቅስቃሴ ከተቻለ በየቀኑ አንዴም እንኳን ቢሆን መስማት ይመርጣሉ::

በዚህ የተነሳ ከልጅ እስከ አዋቂ፣ ከወጣቱ እስከ ሽማግሌው ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ስለ አርቲስቱ ያለው ግንዛቤ ጥልቅ ነው:: የሀገሩ ህዝብ በጠቅላላ ይወደዋል ማለት ይቻላል:: በጥበብ ሥራዎቹ የተከበረውና የተወደደው ይህ ብርቅዬ አርቲስትም ለዚህ ህዝብ ያለው ጥልቅ ፍቅር በቃላት ማስቀመጥ ይከብዳል::

ወገኑ ክፉውን ማየት እንደማይመኝ ሁሉ እሱም በሚወደው ህዝብ ላይ ምንም ዓይነት ክፉ ነገር መስማትን አይሻም:: ለወገኑ ያለው ፅኑ ፍቅርና ልባዊ አክብሮት በአንደበቱ ተናግሮ የሚረካ አይደለም:: ቴዲ አፍሮ በርካታ ህልሞች ቢኖሩትም የመጀመሪያውና ዋነኛው ህልሙ ግን የሚወደው ህዝብ ተቸግሮ አለማየትን ነው::

በአሁኑ ሰዓት የብዙዎች የመነጋገሪያ አጀንዳ የሆነው፣ ሁሉም በእኩል ፍቅር የሚወደው ይህ ኢትዮጵያዊው የክፍለ ዘመኑ ታሪካዊ ጀግና ወጣቱ የሙዚቃ አቀንቃኝ ቴዎድሮስ ካሳሁን፣ ይህን የሰው ልጆች ፍቅር የተጐናጸፈው በገንዘብ ገዝቶት ሳይሆን ከፈጣሪ በተሰጠው ክህሎቱ ነው:: ከዚህ ሌላ እውነትን የሚሰብክ የጥበብ አርበኛ፣ ላመነበት ነገር ወደኋላ የማይል ሀቀኛ እና በፈጣሪውም አምኖና ተማምኖ ለሥራው መቃናት ደፋ ቀና የሚል ብርቱ ሰው ስለሆነ ነው:: የህይወቱን አቅጣጫ በእውነት ላይ ተመስርቶ

የሚመራ፣ በፈጣሪው የሚተማመን፣ ብቃቱንና ሙያውን በንቃተ ህሊናው ያዳበረ፣ ለወገኖቹ ያለበትን ኃላፊነት በሚገባ እየተወጣ ያለ ታላቅ ሰው በመሆኑ ነው የህዝቡ የኩራት መገለጫ ለመሆን የበቃው።

ሞገስ ማለት በህዝብ ዘንድ ተፈላጊ ሆኖ መገኘትና በክብር ጐልቶ መታየት ነውና ጥበበኛው ቴዲ አፍሮም በፈጣሪም በህዝቡም ዘንድ ይህን ዓይነቱን የክብር ሞገስ የተቀዳጀ ነው። ይህ ከፈጣሪው የተቸረው ሞገስ ማንም ተነስቶ ሊነጥቀው አይችልም።

ምክንያቱም ቴዲ አፍሮ የሰው ልጆች በሙሉ በአድናቆት የሚገረሙበት፣ በሚሊዮኖች የሚከበር፣ በዕልፎች ዓይን በስስት የሚታይ፣ ህገሩን ወዳድ፣ ወገኑን አክባሪ፣ አንድነትና ፍቅር ሰባኪ፣ ለብዙዎች አሳቢና ተቆርቋሪ፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረበት፣ ሙያውን አክብሮ የሚያስከብር፣ ብርቱና ጠንካራ አርቲስት ነው። በሙያው ከራሱ ውስጥ ስሜትም አልፎ የሀገሩንና የወገኑን የልብ ትርታ ማዳመጥ ስለቻለ ነው የህዝብ ልጅ፣ የጀግኖች ጀግና ለመሰኘት የበቃው።

ይሁንና አንዳንድ ማመዛዘንና አዙሮ ማየት የተሳናቸው ጥቂት ግለሰቦች ቴዲን የሚያክል ህገር በቀል ታላቅ አርቲስት የግላቸው እንደሆነ አድርገው ማሰብ ከጀመሩ ውለው አድረዋል። ማንም ይሁን ማን ደግሞ ደጋግሞ ሊያስብበት የሚገባ አብይ ቁምነገር ግን ቴዲ አፍሮ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጉዳይ እንጂ የጥቂቶች ወይንም የተወሰኑ ግለሰቦች ብቻ አለመሆኑ ነው።

ቴዲ አፍሮ እንኳን የነዚያ የጥቂቶች የግላቸው ሊሆን ቀርቶ በዚች አሁን ባለንባት ሰዓት የቤተሰቦቹ ብቻ እንኳን አይደለም። በቃ አንዴ ምርጥ የህዝብ ልጅ ሆኗል! ህዝቡም ለዚህ ወጣት ኢትዮጵያዊ ጀግና ምን ጊዜም ደጀን ሆኖ ይቆምለታል!





# የሀገር ቅርስ - የህዝብ ሀብት!

ቢወሰድ ከራዬ - ሆነ ተዐምረኛ

ቴዲ የህዝብ ልጅ ልዩ መልዕክተኛ

እንደ ዐይኑ ብሌን ለህዝቡ የሚሳሳ

ሆነን አርአያ ዝንተ ዓለም የማይረሳ

ኢትዮጵያን አኩርቶ ሀዘኗን ሊያስረሳ

ለክብሯ ለዕድገቷ ባንዲራዋን ያነሳ

አይደለም ወይ እሱ - ዘመን የፈጠረው አንበሳ?

ቴዲ አፍሮ የማነው እስኪ ተጠየቁ?

የህዝብ አይደለም ወይ የሆነን ወርቅ ዕንቁ

ቴዲ አይደለም ወይ ታሪክ የሰራ በምድሩ

ከዳር እስከ ዳር የናኘ ዝና ክብሩ

በፈጣን የፈጠራ ሥራው በድንቅ ብቃቱ

በተሰጠው ፀጋ በጥልቅ ምናቡ

ፍጥረታትን ባስገረመው በእምቅ ክህሎቱ

በማይሰለቸው ስርክ አዲስ ህያው ጥበቡ

ዝንተ ዓለም የሚታወስ

ቴዲ አይደለም ወይ የሀገር ክብር የወገን ቅርስ?

እንዲህ እያልኩ ስጠይቅ አድናቂዎቹ ሰምተው

“ይሄ ቴዲ አፍሮ የሚባለው

ከፍ አድርጐ ባንዲራችን ያውለበለበው

ኮርቶ ሀገሩን ያኮራው

አዎን ቅርስ ነው የህዝብ ባለውለታ

ዘመን የማይሽረው የጥበብ አለኝታ”

አሉኝ።

እናም

ከማንም በላይ ታሪክ ሰሪነቱን መዝኜ

አገር ወዳድነቱን በተግባር አይቼ አምኜ

“ይህ አርቲስት የህዝብ ነው” አልኩኝ ህዝባዊነቱን ተማምኜ





# ማጠቃለያ

## ቴዲ ነገም ሌላ ድንቅ ታሪክ ያስመዘግል

ቴዲ አፍሮ በሙዚቃ ሕይወት ላይ እያስመዘገበው ያለው ታሪክ በቀላሉ የሚታይና የሚገመት አይደለም። እስካሁን ለህዝብ ጆሮና ልብ ያደረሳቸው የሙዚቃ ስራዎቹ አንድም እንከን የማይወጣላቸው፣ እያደር የሚገለጡ ጥልቀትና ምጥቀት ያላቸው ሚስጥራዊ መልዕክቶችን የሚያስተላልፉና ጊዜ አይሽሬ ቁጥር አንድ ጥበባዊ ሥራዎች በመሆናቸው የባለሙያዎች ጥልቅ ጥናትና ምርምር ያሻቸዋል።

የቴዲ ዘፈኖች በዚህ ትውልድ ብቻ ሳይሆን በቀጣዩም ትውልድ የተሰሚነትና የተቀባይነታቸው መጠን ይበልጥ አስገራሚ ሊሆን እንደሚችል በርካቶች ከወዲሁ አስረግጠው በመናገር ላይ ይገኛሉ።

የጥበብን ፈጠራ ያወቀ፣ አዲስ ነገርን በመስራት የተካነ ኢትዮጵያዊው የሙዚቃ ንጉሥ ቴዲ አፍሮ ከዘፈን ባሻገር ገና ለሀገሩ የሚሰራው ታላቅ ታሪክ ሳይኖር አይቀርም። ምክኒያቱም ከዘመን ቀድሞ የተመነጠቀ አስገራሚ ጭንቅላት የታደለ፣ ሁልጊዜ አዲስ ነገርን የሚፈጥርና ለመፍጠር የሚተጋ ብልህተኛና የልዕልና ክብር የተቀዳጀ ምርጥ ከያኒ በመሆኑ ነው። በዚያ ላይ ገና ወጣት ነው። እናም “ከዘፈን ሌላ አንድ ያልታሰበ ድንቅ ሥራ ሰርቶ ህዝብን

እንደሚያስገርምና ለራሱና ለሀገሩ የሚጠቅም ዘመን ተሻጋሪ ታሪክ እንደሚያስመዘግብ በሙሉ ልብ ርግጠኞች ሆነን እንጠብቃለን" የሚሉ ወገኖች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡

በተለይም በጥበብ ስራ ላይ ለሚሰማራ ለአሁኑም ሆነ ለቀጣዩ ትውልድ የቴዲ ጠንካራነት፣ ትሁትነት፣ መልካምነትና ለሙያው ያለው ፍቅርና አክብሮት ትልቅ አርአያ ሆኖ የሚያነሳሳው እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡





# የክብር አክሊል

የአለም የስልጣኔ ምንጭ - የጥበብ ሃዋርያ

የሰው ልጅ መገኛ - የጥበበኞች ማፍለቂያ

የረዥም ዘመን ታሪክ ባለቤት - ቅድሲቷ ኢትዮጵያ

ዛሬም ጀግና ፈጠረች - ኮርቶ እሷን የሚያኮራ

የጥበበኞች ቁንጮ - የሊቆች ሁሉ አውራ፡፡

እናም ይሄ ምርጥ ሰው - ይሄ የዘመኑ ጀግና

የታላቆች ታላቅ - ስመጥር ስመ ገናና

እንደጠቢቡ ቅዱስ ያሬድ ዛሬም በጥበብ ምንጭ አጠመቃት

ታላቅነቷን እየመሰከረ - በዜማ ቅኔ ዳግም ክፍ አረጋት፡፡

ምድርም ይህን አይታ

ዕልል አለች በደስታ

ልጄ ክብሬ ብላ እያወደሰችው

በክብር ለገነት ላይ አኖረችው፡፡

እሱም ለጥበብ ትንሳኤ መፈጠሩን አውቆ

በቁርጠኝነት ተነስቷል መልካም ራዕይ ሰንቆ

ክብሯን ሊያድስ ከራሱ ጋር ለራሱ ቃል ገብቶ፡፡

እንግዲህ በቃ - ቴዲና ኢትዮጵያ ዝምድናቸው ጠንክሯል

ማንም አይለያቸው - አንድ ሆነው ተጣምረዋል፡፡

ስለዚህ

ይህ ድንቅ ሰው ሰወደፊቱም የረቀቀ ድንቅ ሥራ ሰርቶ

በማያልቀው የጥበብ ምንጩ ይበልጥ ከፍ ብሎ ወጥቶ

ለትውልድ ይሻገራል ለዝንተ ዓለም የክብር አክሊል ደፍቶ፡፡

ገና ወገን የሚያኮራ ተአምር ይፈጥራል

በደማቅ የተጻፈ ህያው ታሪክ ያስመዘግባል

የትንቢት ቃሉ ተፈፅሞ ፍጥረታቱ ሁሉ ጉድ ይላል

ዳግም የእኛን ክብር ዓለም አይቶ ይመሰክራል፡፡

ህገሩን የሚወድ - ይወደዋልና ጌታ

በመጪውም ትውልድ ይሆናል የጥበብ የኔታ!

## «ይህ ሁሉ ባፍቅርና በቅንነት ሆነ»

# ተፈፀመ